# አማርኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ

# 10ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ ትምህርት ቢሮ የተስማማ


## አስማምቶ አዘጋጆች

ግሩም ጥበቡ

ታምሩ ገለታ

## ገምጋሚዎች

በላይነሽ ደነቀ (ዶ/ር)

ታሪኩ ነገሰ (ዶ/ር)

## ጥራት ተቆጣጣሪ

ይልፋሸዋ ጥላሁን

## ግራፊክስ

ታደሰ ድንቁ

©ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014/2022

ይህ መፅሐፍ በ2015 ዓ.ም. በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2015 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ መብት በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የቅጂ መብቶችን ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ


መቅድም ....................................................iv

መግቢያ ....................................................v

ምዕራፍአንድ፡-ቋንቋና ማህበረሰብ......................................1

ምዕራፍ ሁለት፡- ባህላዊ ጋብቻ......................................17

ምዕራፍ ሶስት፡-ሴቶች እና ልማት.....................................39

ምዕራፍ አራት...................................................58

በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት.........................................58

ምዕራፍ አምስት፡- ቋንቋዊ ለዛ.......................................79

ምዕራፍ ስድስት፡-የታላላቆች ሚና...................................100

ምዕራፍ ሰባት፡-ረጅም ልቦለድ.......................................118

ምዕራፍ ስምንት................................................136

ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን..........................................136

ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ሥራ ፈጠራ.......................................156

ዋቢ ጽሑፎች...................................................173

ሙዳየ ቃላት...................................................175

# መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለው ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" በሚል ትኩረት ሰጥቶ አዲስ ሥርዓተትምህርት ቀርጾ አቅርቧል። በዚህም መሠረት ቀድሞ በነበረው ሥርዓተትምህርት ላይ ታይተው የነበሩ ክፍተቶችን ለመሙላት ምርምር ተደርጓል። ከምርምሩም የተገኙ አቅጣጫዎች የተማሪዎቹን ደረጃ አለመመጠን፣ የትምህርቱ አንኳር ጽንሰሀሳቦች ግልጽ አለመሆን፣ ከይዘቱ መታጨቅ የተነሳ ለዓመቱ ከተመደበለት ክፍለጊዜ ጋር አለመመጣጠን እና ከተጓዳኝ ሥርዓተትምህርቶች አማራጭ ግብዓቶችን አለመጠቀም ናቸው። ስለሆነም ስርዓተትምህርቱ የቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል፣ በአውድ የተደገፈ ለማድረግ እና በተግባራዊ መማር ላይ የተመሠረተ የመማር ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ተቀርጿል።

ሥርዓተትምህርቱን መሠረት በማድረግም የትምህርት መሣሪያዎች ተዘጋጅተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንዱ ነው። ስለሆነም ይህ መጽሐፍ በአዲስአበባ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀውን መጽሀፍ በኦሮሚያ አማርኛን እንደመጀመሪያ ቋንቋ ከሚማሩ ተማሪዎች ነባራዊ፣ ስነልቦናዊና የቋንቋ ችሎታ ሁኔታዎች አንጻር በማስማማትና በከፍተኛ ደረጃ በማሻሻል ተዘጋጅቷል። መጽሐፉም ተማሪዎች ቢያንስ መጎናጸፍ ያለባቸውን ብቃት (Minimum Learning Competency) እና የሚጠበቁ የመማር ውጤቶችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

# መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ ዘጠኝ ምእራፎችን ይዟል። እያንዳንዱ ምእራፍ ደግሞ በሥሩ ስድስት ንኡሳን የትምህርት ይዘቶችን አካቷል። እነርሱም ትምህርት አንድ ማዳመጥ፣ ትምህርት ሁለት መናገር፣ ትምህርት ሶስት ማንበብ፣ ትምህርት አራት መጻፍ፣ ትምህርት አምስት ቃላት እና ትምህርት ስድስት ሰዋስው ናቸው። እያንዳንዱ ትምህርት በመርሃትምህርቱ በተደለደለው መሠረት መመሪያዎችን፣ ትዕዛዛትን፣ መልመጃዎችን እና ተግባራትን አካቷል። ከዚህ አኳያ የቋንቋ ክሂሎች የተደራጁት በቅድመ ተግባር፣ በጊዜ ተግባር እና በድህረ ተግባር ሂደታዊ አቀራረብ ሲሆን የቋንቋ እውቀት ዘርፎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብን ተከትለዋል። በተጨማሪም የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር እንዲሆን ጥረት ተደርጓል።

# ምዕራፍ አንድ

## ቋንቋና ማህበረሰብ

### የሚጠበቁ ውጤቶች፦

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- መረጃዎችን በማዳመጥ ትወያያላችሁ።
- ውይይት በማድረግ የተገኘውን ውጤት በቃል ታንፀባርቃላችሁ።
- ሰፊ ርዕሰ-ጉዳይን የያዘ ጽሁፍ በማንበብ ተደራሲያንን ትለያላችሁ።
- ገላጭ ቃላትን ለይታችሁ ታመለክታላችሁ
- በጽሁፋችሁ ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ትጠቀማላችሁ።
- ድርሰት ትጽፋላችሁ።
- ጥምር ቃላት በመመስረት በዓረፍተነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ።

# ክፍል አንድ፡ ማዳመጥ

## ቋንቋ እና ጽሕፈት

በዚህ የማዳመጥ ክፍል መምህራችሁ ቋንቋና ጽሕፈት የሚል ምንባብ ያነቡላችኋል። ያዳመጣችሁትን ጽሑፉ መሰረት አድርጋችሁ የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዙ መሰረት ትሰራላችሁ።

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ቃላት ተስማሚ ፍች ስጡ።

   ሀ. አንደበታዊ　　ለ. መላምት　　ሐ. አዝጋሚ　　መ. ጉልህ

2. ቋንቋና ጽሕፈት ስላላቸው ግንኙነት ግምታችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

### የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎች

መምህራችሁ ‹‹ቋንቋ እና ጽህፈት›› በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል። ሲነበብ በጥሞና እያዳመጣችሁ ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ የሚገኙ ባዶ ቦታዎችን አሟሉ።

1. ሰብአዊ የሆነ ፍጡር ሁሉ ሊግባባበት የሚችል መሳሪያ _______________ ነው።

2. የቋንቋ የት መጣነት መላምቶች_______ እና _______ ናቸው።

3. ለመማር ከባድ፣ ለመጠቀም ውስብስብ የሆነ የአፃፃፍ ስርዓት __________ ነው።

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ቀጥሎ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል:: ጥያቄዎቹን በየግላችሁ ከመለሳችኋቸው በኋላ በቡድን ተወያዩባቸው::

1. ቋንቋ ምንድን ነው?
2. የጽህፈት ዓይነቶች የሚባሉት እነማን ናቸው?
3. አማርኛ ቋንቋ የሚከተለው የጽህፈት ስርዓት የትኛውን ነው?
4. በስዕላዊ የአጻጻፍ ስርዓትና በፊደላዊ የአጻጻፍ ስርዓት መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ።
5. ቁስ አካላውያን ስለ ቋንቋ አጀማመር የሚሰነዝሩትን መላምት ተገቢ ይመስላችኋል? ለምን?

ለ. የሥርዓተ ጽሕፈት የሽግግር ደረጃዎችን በጊዜ በቅደም ተከተል አስቀምጧቸው፡፡ (ቃላዊ ሥርዓተ ጽህፈት፣ ስዕላዊ ሥርዓተ ጽህፈት፣ ፊደላዊ ሥርዓተ ጽህፈት፣ ቀለማዊ ሥርዓተ ጽህፈት)

1ኛ. __________ 2ኛ. __________ 3ኛ. __________ 4ኛ. __________

# ክፍል ሁለት፡ መናገር

በመናገር ትምህርት ክፍል ንግግርን እንድትለማመዱ የሚያስችሉ ተግባራት ቀርበዋል። ትዕዛዛቱን ተከትላችሁ ስሯቸው።

### ተግባር አንድ

ሀ. ሀገር ልትበለፅግ የምትችለው እኛ ዜጎች ምን ስናደርግ ነው?

ለ. ሀገር በቀል እውቀቶቻችንን አሟጠን እንዳንጠቀምባቸው ያደረጉን ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?።

## የውይይት አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ

### ውይይት ምንድን ነው?

ውይይት ማለት በማንኛውም አጋጣሚ የተፈጠረን ችግር ለመፍታት ወይም ደግሞ በአንድ አሰራር ላይ የነበረን መርህ ለመቀስቀስ እንዲሁም አዲስ ሃሳብ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ሲባል ጊዜና ቦታ ተዘጋጅቶለት፣ ርዕስ ተነድፎለት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚከወን የሃሳብ ልውውጥ ነው። ውይይትን ከጭውውት እና ክርክር የተለየ የሚያደርገው ችግርን መፍታት ተቀዳሚ ዓላማው በማድረጉ ነው። አንድ ውይይት ስኬታማ እንዲሆን የሚከተሉትን ቅድመ ዝግጅትና አቀራረብ ሊከተል ይገባል።

### የውይይት ዝግጅት

- አድማጮቻችንን አስቀድመን መለየት (ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ጾታ የህይወት ፍልስፍናቸውን ወዘተ...)
- ርዕሰ ጉዳዩን ጠንቅቆ መረዳትና መወሰን
- መረጃ ማሰባሰብና መለየት (ከባለሙያ፣ ከቤተ-መጽሐፍ፣ ከመገናኛ ብዙኀን)

### የውይይት አቀራረብ

- በውይይት በምንሳተፍበት ጊዜ ልንከተላቸው የሚገቡን መመሪያዎች የሚከተሉት ናቸው።
- የውይይቱን አላማና ርዕስ ማስተዋወቅ
- የሌሎችን ሰዎች ሃሳብ ማክበር
- ማስታወሻ መያዝ
- ተራን ጠብቆ ማቅረብ
- ጊዜን በአግባቡ መጠቀም
- ሃሳብን በግልፅና በማስረጃ ማቅረብ
- የእኔ ሃሳብ ብቻ ይሁን አለማለት
- ተሳታፊዎችን ማመስገን ወዘተ... የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

### ተግባር ሁለት

ቃላዊ ዘገባ የሚለውን አጭር ማስታወሻ ካነበባችሁ በኃላ ከመገናኛ ብዙሃን በወቅታዊ የልማት ጉዳዮች ዙሪያ የተደረገ ንግግርን በመከታተል የንግግሩን ፍሬ ሀሳቦች ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

**ቃላዊ ዘገባ**

ቃላዊ ዘገባ ያየነውን፣ ያነበብነውን እና ያዳመጥነውን ጉዳይ በራሳችን የቃላት አጠቃቀምና አቀራረብ ችሎታ በንግግር የምናቀርብበት ነው። ይህን ተግባር በምንከውንበት ጊዜ፡-

- በቂ የሆነ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፣
- አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን (የሰው፣ የቦታ፣ ስሞችን፣ ቀንና ሰዓቶችን፣ ቁጥሮች ወዘተ...) በማስታወሻ በመያዝ በቃል ማቅረብ፣
- አድማጭ ጥያቄ እንዲጠይቅ እድል መስጠት የሚሉት የተለመዱ የቃል ንግግር አቀራረብ መመሪያዎች ናቸው::

(በድሉ ዋቅጅራ (2007፡95) በሥነ-ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር)

# ክፍል ሦስት፡ ማንበብ

በማንበብ ትምህርት ክፍል 'ቋንቋና ሰው' በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል:: ስለሆነም ምንባቡን በጥንቃቄ አንብቡና ተያይዘው የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስሩ::

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ቋንቋ እና ሰው ምን አይነት ግንኙነት ያላቸው ይመስላችኋል?
2. ቋንቋ ባይኖር የሰው ልጅ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል?
3. የሚከተሉት ቃላትና ሃረጋት ስለ ቋንቋ እና ሰው የሚያትቱ

ናቸው። ፍቻቸውን ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ግለጹላቸው።

ሀ. ቋንቋ ለ. ምርምር ሐ. አንደበት መ. ቃል አልባ ተግባቦት

## ቋንቋ እና ሰው

ቋንቋን ከሰው፣ ሰውንም ከቋንቋ፣ አንዱን ከአንዱ ለይቶ ለመናገርም ሆነ ለማሰብ በፍጹም አዳጋች ይሆናል። ስለ ስብእናው፣ ስለ ማህበራዊ ግንኙነቱ፣ ስለአመለካከቱ፣ ስለ ባህሉ ወዘተ... ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ ለመከራከርም ሆነ ‹‹ለመስበክ›› የቋንቋው መኖር ግድ ነው። የቋንቋው መኖር በግዴታ መፈረጁም ለሰው ልጅ ህልውና እጅግ አስፈላጊ በመሆኑም ጭምር ነው:: ‹‹የሰው ልጅ የመግባቢያ ቋንቋ ባይኖረውስ? ያለ ቋንቋ መኖር አይቻለውም?›› ይህ ጥያቄ በዘመናት ውስጥ አከራካሪ መሆን ብቻ ሳይሆን እስከ ዛሬ ምርምርእየተደረገበት ያለ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ጥያቄው ሁሉንም ሰው በጋራ የሚያግባባ ዓለምአቀፋዊ ምላሽ ያልተገኘለት ‹‹ድፍን እንቁላል›› ይሉት ዓይነት የምርምር አጀንዳ እንደሆነ መቀጠሉም ለዚህ ነው። የሰው ልጅ ግን በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ‹‹አጉራ ጠናኝ›› ብሎ ሳይረታ ዛሬም ድረስ ምርምሩን በስፋት እያከናወነ ይገኛል። የሰው ልጅና የቋንቋን ቁርኝነት በተመለከተ ሁለት ማሳያ የሆኑ ታሪኮችን እናንሳ።

## ታሪክ አንድ

‘የቅድስቷ ሮማ ንጉሰ ነግስት’ እየተባለ የሚጠራውና የዘውዳዊ አገዛዝ ስርወ መንግስት መሪ የነበረው ዳግማዊ ፍሬዴሪክ በመካከለኛው ዘመን (ከ1194 - 1250 እ.ኤ.አ) ቋንቋን አስመልክቶ በሰው ልጅ ስልጣኔ ታሪክ ውስጥ አሻራ ያሳረፈ ያልተጠበቀ ግኝት አበርክቷል። ይህም በወቅቱ የቋንቋ ነጠቃ ወይም ቋንቋ ክልከላ ሙከራዊ ጥናት ተሰኝቷል።

በ13ኛው መቶ ክፍለዘመን ፍሬድሪክ የሰው ልጆች የቀደመ ወይም ተፈጥሯዊ ቋንቋ ምን ነበር የሚለውን ለማወቅ ፍላጎት አደረበት። ጥያቄዎቹ ምላሽ ያገኙ ዘንድም ሙከራዊ ጥናት ለማድረግ ወሰነ።

በዚህም አምስት አፍ ያልፈቱ ህጻናትን ለይቶ በመውሰድ ከህጻናቱ ጋር ምንም አይነት ንግግርና ምልልስ በማይደረግበት ሁኔታ ውስጥ እንዲቆዩ አደረገ። ከዚህም ፍሬድሪክ የሰው ልጆችን ተፈጥሯዊ ቋንቋ አገኛለሁ የሚል ተስፋ ሰንቆ ነበር።

በሂደቱም ህጻናቱ በአሳዳጊ እናት እና በተንከባካቢ ነርሶች ክትትል ስር እንዲሆኑ፣ ንጽህናቸው እንዲጠበቅና በአግባቡ እንዲመገቡ ተደርገዋል፤ ምንም አይነት ተግባቦታዊ እንቅስቃሴ ግን ፈጽሞ አይፈቀድም ነበር፤

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

**ተማሪዎች ንባባችሁን ገታ አድርጋችሁ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ።**

ሀ. እስካሁን ካነበባችሁት የጽሑፍ ክፍል ምን ምን ተረዳችሁ?

ለ. ‘የቋንቋ ነጠቃ’ ሙከራዊ ጥናት ለማካሄድ የተነሳው ማነው? አላማውስ ምን ነበር?

ንክኪ ተገድቧል፣ ንግግር የለም፤ እንዲሁም ስሜት አንጸባራቂ ተግባራት በሙሉ ታግደዋል። ፍሬድሪክ በዚህም ቋንቋ በፈጣሪ ለአዳምና ሄዋን የተቸረ ነው የሚለውን ለማረጋገጥ ቋምጧል።

ከሦስት አመታት ሙከራ በኋላ ግን አስደንጋጭ የሆነ ውጤት ተመዘገበ!

ሁሉም ህጻናት ሞተው ተገኙ። ፍሬድሪክም ሙከራዊ ጥናቱ ባለመሳካቱ እጅግ ተበሳጨ። የዚህ የጥናት አለመሳካት የሚያሳየን የሰው ልጆች በተፈጥሯዊ ስሪት የሚቆሙ ብቻ ሳይሆኑ ማህበራዊ ማንነትም እንደሚያስፈልጋቸው ነው። የሰው ልጆች ያለ ተግባቦታዊ መስተጋብር ዘላቂነት ያለው ህይወት ሊመሩ አይቻላቸውም። የጨቅላ ህጻናቱ ሞት ይህንን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው። በነገራችን ላይ ባለንበት ወቅት የሰው ልጆችን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውም ጥናት በጥብቅ የተከለከለ ነው። በዚህም የተነሳ ጥናቶች አስቀድመው ለሰው ልጆች ቀረቤታ ባላቸው እንስሳት ላይ እንዲደረጉ ይመከራል።

## ታሪክ ሁለት

አምስት ሰዎች ሽልማት ለሚያስገኝ የዝምታ ውድድር ተመርጠው ጸጥታ በሰፈነበት ክፍል ውስጥ አብረው እንዲቆዩ ተዘጋባቸው። በቆይታው ወቅት እርስ በርስም ሆነ አንዱ ከሌላው ጋር በምንም ሁኔታ እንዳይነጋገሩና በየትኛውም ዓይነት የቃል አልባ ግንኙነት(ኢ-ልሳናዊ)እንዳይግባቡጥብቅ ትዕዛዝ ተላልፏል።

አንደኛ የወጣው ሰው በዝምታ እንደጸና ሳይናገር የቆየው ለስምንት ቀናት ብቻ ሲሆን ሦስቱ ያለ ንግግር የቆዩት ለሁለት ቀናት ነበር። ሌላኛው ሰው የቆየው ለአንድ ሰዓት ያህል ብቻ ነው። የእነዚህ ሁለት ተጠቃሽ ታሪኮች አንድምታ የሚያስረዳን ጤናማ ሰው ከብጤው የሰው ልጅ ጋር ወይንም ከፈጣሪው ጋር፣ አልያም ከየትኛውም ፍጡር ጋር በንግግርም ሆነ በቃል አልባ ግንኙነት ከመግባባት ቢታቀብ ህልውናው ስጋት ውስጥ የሚገባ መሆኑን ነው።

(ጌታቸው በለጠ የጥበባት ጉባኤ 2004 ፤ 4-7 በመጠኑ ተሻሽሎ የቀረበ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ።

1. ዳግማዊ ፍሬድሪክ በሙከራ ጥናቱ ለማረጋገጥ የሞከረው ምንን ነበር?
2. የሰው ልጅ ያለ ቋንቋ ህልውናው ሊቀጥል የማይችልባቸውን ምክንያቶች አስረዱ?
3. ንጉስ ፍሬድሪክ የሙከራ ጥናቱን ለማካሄድ የተከተላቸውን ቅደም ተከተሎች ዘርዝሩ።
4. በታሪክ አንድና ሁለት መካከል ያለው የሃሳብ አንድነት እና ልዩነት ምንድን ነው?

5. ከላይ ያነበባችሁትን ምንባብ አጠቃላይ ፍሬ ሃሳብ (ጭብጥ) በአጭሩ ግለጹ።

ለ. የሚከተሉት ቃላትና ሃረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። ጥንድ ጥንድ በመሆን ዓውዳዊ ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።

ምሳሌ፡ በሰፈነበት

ፀጥታ የሰፈነበት ቦታ ለማንበብ ምቹ ነው፡፡

ሀ. ስልጣኔ　ለ. ግኝት　ሐ. አፍ ያልፈቱ

መ. የተቸረ　ሠ. ተገድቧል　ረ. ተስፋ ሰንቆ

ሰ. ፍንትው　ሸ. ተጠቃሽ

ቀ. አጉራህ ጠናኝ　በ. ድፍን እንቁላል

# ክፍል አራት፡ መፃፍ

በዚህ ትምህርት ክፍል አንድ መልመጃና አንድ ተግባር ቀርበዋል። ትዕዛዛቱን ተከትላችሁ ስሩ።

## መልመጃ ሦስት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መመሪያዎቹን ተከትላችሁ ስሯቸው።

ሀ. ቋንቋ እና ሰው ከሚለው ጽሁፍ የተረዳችሁትን በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ:: በምትጽፉበት ጊዜ ተገቢ አያያዥ ቃላትን፣ ሥርዓተ ነጥቦችን እና የሃሳብ ፍሰት ቅድም ተከተል መጠበቃችሁን ልብ በሉ::

ለ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች የአንድ አንቀጽ አካላት ናቸው። ነገር ግን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው አልተቀመጡም፤ አስተካክሏቸውና አንቀጽ መስርቱባቸው::

1. ጽሕፈት ለሰው ልጅ የቀደሙ አባቶቹን ውርስ፣ የራሱን ቅርስና ጥበብ ለተተኪው ለማስተላለፍና ለገዛ ህልውናው ልማት መሠረት ለመጣል ብሎም በተፈጥሮ ላይ ለመሰልጠንም አግዞታል።
2. ሰው ይህንን የንግግሩን ውስንነት ለማስወገድና ታሪኩን፣ ባህሉንና ትውፊቱን ቀርጸ ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲሁም ሩቅ ቦታ ለሚኖር መሰሉ ሐሳቡንና ተግባሩን፣ ምኞቱንና ተስፋውን ለማድረስ ሲል፣ የጽሕፈት ጥበብን እንደፈጠረ ይገመታል።
3. የዚህ ስልት መፈጠርም ራሱንና በዙሪያው ያለውን አለም የበለጠ እንዲገነዘብ ረድቶታል።
4. የሰው ልጅ ለብዙ ሚሊዮን አመታት ቃላዊ በሆነው ቋንቋው ተግባብቶ ተፈጥሮን እየለወጠ ህልውናውን ጠብቆ መቆየት ቢችልም፣ በንግግር የሚለዋወጠው መልዕክት በጊዜና የቦታ የተገደበ ነበር።

## ተግባር ሦስት

ከላይ የተሰጣችሁን የመጻፍ ሂደት ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ቀጥለው የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሰረት ስሩ።

1. ገላጭ ቃላትን እና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በመጠቀም ‹‹ሰፈሬ›› በሚል ርዕስ የመጣችሁበትን ሰፈር የሚያስተዋውቅ ሁለት አንቀጽ ያለው አጭር ድርሰት ጻፉ።
2. ‹‹ኮረና›› በሚል ርዕስ ከተለያዩ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ያገኛችኋቸውን መረጃዎች በመጠቀም አንድ ድርሰት ጻፉ። (ምንነቱን፣ መተላለፊያ መንገዶቹንና መከላከያ ዘዴዎቹን የሚገልጽ ድርሰት)

# ክፍል አምስት: ቃላት

በዚህ ትምህርት ክፍል የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍቺና ጥምር ቃላትን የተመለከተ ይዘት ቀርቧል። ከይዘቱ ጋር በተያያዘ የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዛቱ መሰረት ስሩ።

## ጥምር ቃላት

ጥምር ቃላት ሁለት ሊጣመሩ የሚችሉ የተለያዩ ቃላት ናቸው። እነዚህ ቃላት በተናጠል የተለያየ ፍቺ ከሚሰጡት በተጨማሪ ሌላ አዲስ ፍቺ ወይም የነበረውን የተናጠል ፍቺ የበለጠ የሚያጠናክሩ ቃላት ናቸው።

ለምሳሌ፡ ሀ. ቤት + መጽሐፍ = ቤተ-መጽሐፍ

ለ. ህግ + መንግስት = ህገ-መንግስት

ሐ. ወጥቶ + አደር = ወታደር

መ. ወዝ + አደር = ወዛደር

ጥምር ቃላት አንዳንድ ጊዜ በንዑስ ጭረት (ንዑስ ሰረዝ) አንዳንዴ ደግሞ ያለ ስርዓተ ነጠብ የሚጣመሩበት ጊዜ አለ። ከዚህም በተጨማሪ ሁለት የተለያዩ ተጣማሪ ቃላት ሲጣመሩ ጥምርነታቸውን ረስተው አንድ ቃል የሚመስሉበት አጋጣሚም አለ። ከላይ በምሳሌ ‹‹ሐ›› እና ‹‹መ›› የቀረቡት ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ጥምር ቃላት የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን ለመመስረት ጉልህ ሚና አላቸው።

ለምሳሌ፡ ሀ. ኢትዮጵያ የራሷን ህገ-መንግስት ቀርጻ መተዳደር ከጀመረች በርካታ ዓመታትን አስቆጥራለች።

ለ. ወዛደር ለሀገር ግንባታ የራሱ የሆነ ሚና አለው።

## መልመጃ አራት

1. በሚከተለው ሳጥን ውስጥ ተጣማሪ ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት ተሰጥተዋል። ተቀባይነት ያለው ፍቺ ሊያስገኙ የሚችሉትን በማዛመድ ጥምር ቃል መስርቱ። ለምሳሌ፡ ልብ ወለድ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወፍ | አቀፍ | ምድር | ሥርዓት |
| ዓመት | ወዶ | ገዝ | ዘራሽ |
| መልክዓ | ራስ | ገብ | ምህረት |
| አየር | ዓለም | ሥነ | ወለድ |
| ላብ | ገመና | አደር | ከታች |

2. ከላይ በመሰረታችኋቸው ጥምር ቃላት አንድ አንድ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው::

ለምሳሌ፡ ዓለምዓቀፍ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ ዓለምአቀፍ ዲፕሎማቶች መቀመጫ ናት።

## መልመጃ አምስት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ከመዝገበ ቃላት በመፈለግ ጻፉ።

ሀ. ቁርሾ

ለ. መረን

ሐ. ነቁጥ

መ. ህቡዕ

ሠ. ጨረፍታ

ረ. ዚቀኛ

ሰ. ሀመልማል

ሸ. ምንዝር

ቀ. ነጸብራቅ

በ. እንቦቀቅላ

# ክፍል ስድስት፡ ሰዋስው

በሰዋስው ትምህርት ክፍል ገላጭ ቃላትን የተመለከተ ማስታወሻና መልመጃ ቀርቦላችኋል:: ማስታወሻውን መሰረት በማድረግ የቀረበውን መልመጃ ስሩ::

1. ቀጥሎ ገላጭ ቃላት የሚል ማስታወሻ ቀርቧል:: ማስታወሻውን ከማንበባችሁ በፊት በአዕምሯችሁ የተከሰቱ አስር ቃላትን ደብተራችሁ ላይ ጻፉ::

## ገላጭ ቃላት

ገላጭ ቃላት አንድን ነገር ወይም ሁነት ይበልጥ እንድንረዳው የሚያስችል መረጃ የሚሰጡን ሲሆኑ፣ ነገሮችን ለስሜት ህዋሶቻችን የቀረቡ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። ገላጭ ቃላት ቅጽሎች ወይም ተውሳከ ግሶች ሊሆኑ ይችላሉ፤

ቅጽሎች የስም ገላጮች ሲሆኑ ስምን ከቀለም (አይነት)፣ ከመጠን ወይም ከባህሪ አንጻር ሊገልጹት ይችላሉ። ለምሳሌ ቀይ፣ ሰፊ፣ ብልህ

ተውሳከ ግሶች በገላጭነት ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚገልጹት ግሱን ሲሆን፣ በግሱ የተገለጸው ድርጊት ወይም ሁነት እንዴት፣ መቼና ስንት ጊዜ እንደተፈጸመ ይነግሩናል።

ለምሳሌ ቶሎ ቶሎ ተራመደች፤ ገና አልመጣም፤ ሁለት ጊዜ ወደቀ

በነገራችን ላይ የገላጭነቱን ተግባር ስሞችና ግሶችም ሊወጡት ይችላሉ። ለምሳሌ፡-

ስም ገላጭ ሆኖ- የአቶ መገርሳ ልጅ ተሊሌ የለበሰችው ቀሚስ፣ ቁመናዋና አረማመዷ ማራኪ አድርገዋታል።

ግስ ገላጭ ሆኖ- ደኑ ውስጥ ብቻዬን መሆኔ አስደሰተኝ ፤

እያሳቀና እያዝናና ጥሩ ጊዜ እንድሳልፍ አደረገኝ።

2. ከላይ ማስታወሻውን ከማንበባችሁ በፊት ከጻፋችኋቸው አስር ቃላት ውስጥ ገላጭ የሆኑትን ለይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

3. በሚከተለው አጭር ጽሁፍ ውስጥ ሃሳብን የበለጠ ሊገልፁ የሚችሉ ቃላት ተካተዋል። በመሆኑም ገላጭ ቃላት የምትሏቸውን ለይታችሁ አውጡ።

... ዶ/ር ደስታ ይባላል። ቀጥ ብሎ የተሰደረ አፍንጫውና ጎላጎላ ያሉ ዓይኖቹ ቀይዳማ ፊቱ ግርማን አላብሰውታል። ተክለ ሰውነቱ ረዘም ያለና ደልዳላ ነው። የእጅና የእግር ጡንቻዎቹ በትክክል መስመራቸውን ይዘው የፈረጠሙ ናቸው። ከደረቱ ወጣ ያለ ሆኖ፤ ሆዱ ከጀርባው ሊጣበቅ ትንሽ ነው የሚቀረው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ቋንቋና ሰው ያላቸውን መስተጋብር የተመለከታችሁ ሲሆን፣ የሰው ልጅ ያለመግባቢያና ቋንቋ የመኖር ህልውናው አደጋ ውስጥ እንደሚገባ አመላካች የሆኑ የተለያዩ ሁለት አስተማሪ ታሪኮችንም አንብባችኋል። ቋንቋ የሰው ልጅ ስሜቱን፣ ሃዘኑንና ደስታውን፣ ማህበራዊ ግንኙነቱን፣ ሰዋዊነቱን፣ አስተሳሰቡን፣ ባህሉን ወዘተ... ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ ለመከራከርም ሆነ ለማስተማር የሚጠቀምበት መሆኑን ተገንዝባችኋል።

እንዲሁም ስለ ቃላት ሚና በተለይም ደግሞ ቃላት በድርሰት ውስጥ ስላላቸው አገልግሎት ተመልክታችኋል። በዚህም በድርሰት ውስጥ ገላጭ ቃላትን ተጠቅመን መልካዓ ምድርን፣ መልክና ቁመናን፣ ሀሳብንና ማንኛውንም የሚገለጹ ነገሮች መግለጽ እንደምንችል ተረድታችሁ በተግባርም ድርሰት በመጻፍ አሳይታችኋል።

በተጨማሪም ስለጥምር ቃላት አመሰራረትና ሲመሰረቱ ምን እንደሚመስሉ ተገንዝባችኋል። ጥምር ቃላት በንዑስ ጭረት ወይም ያለ ንዑስ ጭረት ሊመሰረቱ እንደሚችሉም አውቃችኋል። በእነዚህም ቃላት ዓረፍተ ነገር እንዴት እንደሚመሰረት ተረድታችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ቋንቋ በሰው ልጆች ወይስ የሰው ልጆች በቋንቋ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ? የራሳችሁን ግላዊ አመለካከት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡
2. ቃል አልባ መግባቢያ መንገዶች የሚባሉትን በመዘርዘር ለመምህራችሁ ግለጹ፡
3. ከሚከተሉት ሁለት የድርሰት መጻፊያ ርዕሶች አንዱን በመምረጥ ገላጭ ቃላትን በመጠቀም ባለ ሁለት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ፡፡

   ሀ. ወደፊት መሆን የምፈልገው　　ለ. ለምለሚቷ ሀገሬ

4. የሚከተሉትን ጥምር ቃላት በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

   ሀ. በትረ መንግስት　　ለ. አመለቢስ

   ሐ. ቀዶ ጥገና　　መ. ሥነ-ዘዴ

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ ስር የቀረበላችሁን ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✔)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | |
|---|---|---|
| 1. | ስለቋንቋ እና ሰው ግንኙነት በቃል እና በጽሁፍ መግለፅ እችላለሁ። | |
| 2. | የውይይት አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን መሰረት በማድረግ መወያየት እችላለሁ። | |
| 3. | የቃል ዘገባ አቀራረብን መመሪያ ተከትዬ ያነበብኩትንና የተወያየሁበትን በቃል ማቅረብ እችላለሁ። | |
| 4. | ቋንቋ እና ሰው ያላቸውን መስተጋብር ለጓደኞቼ በቃል መግለጽ እችላለሁ። | |
| 5. | ለቃላት ዓውዳዊ እና መዝገበ ቃላዊ ፍች መስጠት እችላለሁ። | |
| 6. | የቃላትን ሚና በመረዳት ገላጭ ቃላትን ተጠቅሜ አንድን ነገር መግለጽ እችላለሁ። | |
| 7. | ጥምር ቃላትን በመለየት በዓረፍተ ነገር ምስረታ ወቅት ልጠቀምባቸው እችላለሁ። | |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዱ ቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ሁለት

# ባህላዊ ጋብቻ

## የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የሌሎችን ንግግር በማዳመጥ ግብረ መልስ ትሰጣላችሁ፤
- ክርክር ታደርጋላችሁ፤
- የጽሁፍን ሀሳብ አገናዝባችሁ ታነባላችሁ፤
- የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ሀሳባችሁን በፅሁፍ ትገልጻላችሁ፤
- ትምህርታዊ እና ቴክኒካዊ ቃላትን በጽሁፍ እና በንግግር ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤
- አስረጅ፣ መጠይቃዊ እና ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮችን በጽሁፋችሁ ውስጥ ትገለገላላችሁ፤

# ክፍል አንድ፡ ማዳመጥ

በማዳመጥ ትምህርት ክፍል የጋብቻ ምንነትን የተመለከተ ምንባብ ቀርቦላችኋል፡፡ ምንባቡን መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በጥሞና አዳምጡና ተያዘው የተሰጡ ጥያቄዎችን ስሩ፡፡

## ጋብቻ

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን እየተወያያችሁ የደረሳችሁበትን ሃሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ::

1. ጋብቻ ማለት ምን ማለት ነው? ስለጋብቻ ወይም ትዳር የምታውቁትን ተናገሩ፡፡
2. በሀገራችን ያለፍላጎት በጠለፋ የሚፈጸም ጋብቻ ወንጀል ነው፡፡ በዚህ መንገድ የሚፈጸም ጋብቻ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ተወያዩና ሃሳቦቻችሁን ለሌሎች አጋሩ፡፡
3. የሚከተሉት ቃላት በምታዳምጡት ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ ፍቻቸውን ገምቱ፡፡

ሀ. መረዳዳት ለ. ውህደት ሐ. አጋር መ. ቃል ኪዳን

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

የአዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ‹‹ጋብቻ›› በሚል ርዕስ የተነበበላችሁን ምንባብ አጠቃላይ መልዕክት በቡድን ከተነጋገራችሁበት በኋላ ምላሻችሁን በቃል አቅርቡ፡፡
2. ወጣቶች ለጋብቻ ሰፊ አሰሳ የሚያደርጉት ለምንድ ነው?
3. “እህል ውሃ አጣጩ” ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው፡፡

4. 'ከጭቅጭቅ የጸዳና ዘላቂ ሆኖ የመቀጠል እድሉ አናሳ' የሆነው ምን አይነቱ ጋብቻ ነው? ለምን?

5. የሚከተሉት ቃላትና ሃረጋት ከተደመጠው ምንባብ የወጡ ናቸው። ፍቻቸውን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

| | | |
|---|---|---|
| እውቂያ | የምስክር ወረቀት | ተቀናጅተው |
| እማኞች | ልማድ | እልህ አስጨራሽ |

# ክፍል ሁለት: መናገር

**በዚህ ትምህርት ክፍል ክርክርን የተመለከተ ማስታወሻና ተግባራት ቀርበውላችኋል:: ትዕዛዛቱን ተከትላችሁ ተግባራቱን ስሩ:**

## ክርክር

ክርክር በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተለያየ አቋምን በማራመድ የሚደረግ ሥርዓት ያለው እስጥ አገባ ወይም የሃሳብ ሙግት ነው። ክርክር በተለያየ አጋጣሚ ሊከወን ይችላል። ለአብነት ያክል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

- ተማሪዎች በትምህርት ቤት
- ከሳሽና ተከሳሽ ፍትህ ለማግኘት በፍርድ ቤት
- ፖለቲከኞች ለመመረጥና ሃገር ለመምራት በመድረክ ወዘተ...

በማንኛውም ሁኔታ የሚከናወን መደበኛ ክርክር ቅድመዝግጅት ማድረግን ይጠይቃል። ስለሆነም በክርክር አዘገጃጀት እና አቀራረብ ጊዜ የሚነሱ ነጥቦችን ማወቁ ጠቃሚ ነው።

### 1 የክርክር ዝግጅት

- በርዕሰ ጉዳያችን ዙሪያ መረጃ መሰብሰብ (ከመጽሐፍት፣ ከድረገጽ ከባለሙያ...)
- መረጃዎችን በቅደም ተከተል ማደራጀት፣

- ክርክሩን ከማቅረባችን በፊት ልምምድ ማድረግ፣
- ወደክርክር ከመቅረባችን በፊት አለባበሳችንን ማሳመር፣ ንጽህናችንን መጠበቅ፣ እንዲሁም የአሸናፊነት ሥነ-ልቦናን መላበስ አለብን።

## 2 የክርክር አቀራረብ

- አድማጭን በማመስገን የመከራከሪያ ርዕሳችንን ማስተዋወቅ፣
- ሃሳባችንን በግልጽና በተረጋጋ መንፈስ በልበ ሙሉነት በቅደም ተከተል ማቅረብ፣
- ክርክራችንን በተገቢው የአካል እንቅስቃሴ እያጀቡ ማቅረብ፣
- የሞጋቾቻችንን ሃሳብ በጽሞና ማዳመጥና ማስታወሻ መያዝ፣
- የምናቀርበው መረጃ የተከራካሪዎችን አቅም /ችሎታ/ ያገናዘበ መሆን
- ለክርክር የተሰጠን ጊዜ ማክበር እና በአግባቡ መጠቀም፣
- ከርዕሳችን እንዳንወጣ መጠንቀቅ፣
- በመጨረሻም አመስግነን ሃሳባችንን መቋጨት መቻል አለብን፡

## ተግባር አንድ

ከላይ የክርክር አካሄድን በተመለከተ የቀረበላችሁን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ከታች በተሰጣችሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ዝግጅት አድርጋችሁ በክፍል ውስጥ ክርክር አቅርቡ።

## ተግባር ሁለት

| |
|---|
| የመከራከሪያ ርዕስ |
| ባህላዊ ጋብቻ ከዘመናዊ ጋብቻ ይሻላል? |

## ተግባር ሁለት

ባህላዊ ጋብቻን በተመለከተ ቤተሰቦቻችሁን ወይም የአካባቢያችሁን ሰዎች ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

# ክፍል ሶስት: ማንበብ

በዚህ ትምህርት ክፍል የቦረና ባህላዊ ጋብቻ የሚል ምንባብ ቀርቧል። ምንባቡን በትኩረት አንብባችሁ መልመጃዎችን ስሩ።

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በቃል ስጡ።

1. የምታውቋቸውን የጋብቻ ዓይነቶች በስም ጥቀሱ።
2. በቅርቡ ጋብቻ ሲካሄድ አይታችኋል? ጋብቻው እንዴት ሲካሄድ እደነበር ለጓደኞቻችሁ ግለጹላቸው።
3. እነዚህ ቃላትና ሐረጋት የያዙትን ፍቺ ስጡ።

   ሀ. መተጫጨት  ለ. እልፍኝ  ሐ. ሰይመው  መ. ቀን ተቆረጠ

4. የቦረና ባህላዊ ጋብቻ ምንባብ ምን ምን ጉዳዮችን የሚያነሳ ይመስላችኋል?

## የቦረና ባህላዊ ጋብቻ

በዚህ ጽሑፍ በቦረና ዞን በምትገኘው ያቤሎ አካባቢ ከሚከናወኑ ባህላዊ ጋብቻዎች መካከል አንዱ የሆነውንና የወንድ ቤተሰቦች የሴቷን ቤተሰቦች ልጃችሁን ለልጄ በማለት የሚጠይቁበትን ስርዓት አካሄድ እንመለከታለን።

በዚህ የጋብቻ ጥያቄ ሂደት የጋብቻ ጠያቂው ቤተሰቦች አስቀድመው ለጋብቻ ስለታሰበችው ልጅ ከተለያዩ ምንጮች መረጃ ይሰበስባሉ። መረጃውን መሰረት አድርገው ውሳኔ ላይ ከደረሱ በኋላ በአካባቢው ተሰሚነት ያላቸው ሽማግሌዎች ሰይመው ወደ ልጅቷ ቤት እንዲሄዱ ያደረጋሉ። ሽማግሌዎቹ ወደ ልጅቷ ቤት ሲሄዱም በስጦታነት ትንባሆ እና ጨው ወይም ትንባሆና ቡና ይይዛሉ። ያዘጋጁትን ስጦታም በሴቷ ቤተሰብ ወላጆች ፊት ቀርበው ስጦታችንን ተቀበሉን በማለት በትህትና ይጠይቃሉ። ሆኖም የሙሽሪት ቤተሰብ ስለጋብቻ ጠያቂው ልጅ ቅሬታ ያላቸው ከሆነ ጉዳዩን በማንሳት ቅሬታችን ካልተፈታ ጥያቄውን አንቀበልም ሊሉ ይችላሉ። የጥያቃ ሂደቱ በመግባባት ከተጠናቀቀና መተጫጨቱ

ተቀባይነት ካገኘ ግን ልጅቱ ተያዘች ማለት ይሆናል። የወንዱን ወላጆች ወክሎ የሄደው የሽማግሌ ቡድንም እሺታውን ከሰጠው የሴቷ ወገን ድፍን ቡና ተቆልቶ በቅቤ /ቡን ቀላ/ ይቀርብለታል።

ቀጣዩ ተግባር የጋብቻ ቀን እንዲቆረጥ መጠየቅ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት ጋብቻ ጠያቂው ቡን ደጌቲ ማረጋገጫ ስጦታ ቡና፣ ቅቤና ማር ያቀርብና የጋብቻውን ቀን ወስኑልኝ ሲል ይጠይቃል። የጋብቻው ቀንና ወርም በሴቷ ቤተሰቦችና በሽማግሌዎች መካከል ምክክር ከተካሄደ በኋላ ይቆረጣል። ቀኑ ሲቆረጥ ግን የሴት ሙሽራዋ እናት ካገባችበት ቀን ላይ እንዲውል አይደረግም።

የተቆረጠው ቀን ደርሶ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጎ ጋብቻው ሲፈፀም ከወንዱ ወገን ሁለት ጊደር አንድ ኩታ /በዶ/ አሊያም ሶስት ከብት፣ ለልጅቷ በስጦታነት ተይዞ የሚኬድ ይሆናል። በተመሳሳይም በልጅቱ ቤተሰብ በኩልም “ኡዋ” ወይም ከለፋ ቆዳ የተሰፋ አልባስና ጎርፎ መታጠቂያ ከፍየል ቆዳ የሚሰራ፣ ጪሙ ቢዮ ከቅል የሚሰራ ቡቹማ/ ቡቄ/፤ ማግባቷዋን የሚያሳይ በትር (ሲቄ)፣ ሚዶ/ፊላ/ እንዲሁም የቅቤ መያዣ በስጦታነት አዘጋጅተው ይጠብቃሉ።

በሰርጓ እለት ሙሽሪት ከእንጨት ለቀማ ከሄደችበት ከጓደኞቿ ጋር ከ9 ወይም 10 ሰአት ገደማ ስትመለስም ቤተሰቦቼ የባህል ልብስ ለብሰው በረት ውስጥ ሆነው ይጠብቋትና  ስትደርስ ጭናቸው ላይ አስቀምጠው መሀል አናቷ ላይ ፀጉሮዋን በስለት ትንሽ ላጨት በማድረግ ይመርቋታል። የከብቶቹን መግባት ተከትሎም ሙሽራው ከከብቶቹ ጋር የያዘውን ስጦታ በጎደኞቹ/ሚዜዎቹ/ አስይዞ ይመጣል፤ ወደተዘጋጀላቸው ጓዳም ከሙሽሪት ጋር ይዘልቃሉ።

በዕለቱም አራቱም ጡቶቹዋ የሚያፈሱ ላም ተመርጣ ትታለብና ቡና ቀለ፤ በልጅታ ቤተሰብ ቁጥር ፍሬ ድፍን ቡናም ይጠበስና የታለበው ወተት ውስጥ ተጨምሮ ቤተዘመድ በእድሜ ቅደም ተከተል ከታላቅ ጀምሮ እንዲቃመሱ ይደረጋል። ጎረቤት ዘመድ አዝማድ በተሰበሰበበትም ቤተዘመዳዊ መመካከር ይከናወናል። ሙሽራው ባህሉን እንዲያከብር ሚስቱ ላይም ጥቃት እንዳያደርስ እሷም ባሏን እንድታከብር፣ ቢጋጩ

እንኳን ችግራቸውን ለሽማግሌ እንዲያቀርቡና በእርቅ እንዲፈቱ ይመከራሉ። ለሙሽራውም ሞጋሳ /የዳቦ ስም እንደሚባለው/ የሚሰጠው ሲሆን፣ የሙሽሪት ቤተሰብ ለልጃቸው አውጥተውላት የነበረውን ስምም ያስተዋውቂታል።

### የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

ሀ. ለጋብቻ የመጠያየቅ ሂደቱ በመግባባት ከተጠናቀቀ ቀጣዩ ተግባር የጋብቻ ____________ ነው።

ለ. ሙሽሪት ከእንጨት ለቀማ የምትመለሰው ከማን ጋር ነው?

ሐ. 'መረጃውን…' ሲል (አንቀፅ 2) የቱን መረጃ ማለቱን ነው?

በትውውቁ ምሽት ከብት የሚታረድ ሲሆን እየተበላና እየተጠጣ እዚያው ሙሽሪት ቤት ይታደራል። ለሊት ላይም የሙሽሪት እናት ሙሽሪትን አናቷ ላይ ቅቤ ቀብተው፣ ጸጉሯን ሰርተውና ያዘጋጁላትን የባህል ልብስ አልብሰው ያዘጋጂታል። ሲነጋም ሙሽሪትና ሙሽራው እናቷ ያለቡትን ወተት በጮጮ ጠጥተው ሙሽረትን መሃል በማድረግ በአባቷ ዋና በር በኩል ወጥታ በበር መዝጊያው እንጨት /ጉቱሜ/ ላይ የወንድ ሙሽራው ልብስ ላይ እንድትቀመጥ ይደረጋል፤ ሙሽራዉም ሱሪውን አውልቆ ትከሻዋ ላይ ጣል ያደርገዋል። የሱሪው መውለቅ ያለውን ጥንካሬ፣ ክብሩን ሁሉ አሳልፎ ለሷ መስጠቱን ማሳያ ሲሆን ሙሽሪት አልባሳት ላይ መቀመጧ ደግሞ አክብሮትን ለማሳየት የሚከናወን ልማድ ነው። ይህንን ስርአት ካከናወኑ በኋላ እሱ ከፊት እሷ ከኋላ በመካከል ሰው እንዳያልፍ ሆነው ወደልጁ ቤተሰብ ቤት መጓዝ ይጀምራሉ። ባል ከፊት ከፊት የሚሆነው እንዳትደነግጥ ለመጠበቅና መከታ መሆኑን ለማሳየትም ጭምር ነው። በመንገድ ላይ ሲሄዱ ሙሽሮች መሆናቸውን ያወቁ መንገደኞች ሁሉ በክብር እያሳለፉ ይሸኟቸዋል።

የወንዱ ቤተሰብ ቤት እንደደረሱም በስጦታ የተሰጡአቸውን ከብቶች ይዘው የከብት በረት መዝጊያ ጭራሮ /ጉቱሜ/ን ለሶስት ጊዜ በመዞር ይቀመጡና የወንድ ሙሽራ እናት ያቀረበችላቸውን ወተት ይጠጣሉ። ወደ በረቱ ዘልቀውም አረፍ እንዲሉ ይደረጋል። እዚህም በግ የሚታረድ

ሲሆን ከበጉ ብልት አንዱ ተወስዶ በሙሽሪት አንገት ላይ እንዲንጠለጠል ይደረጋል፡፡ ከታረደው በግ እግር አካባቢም ቆዳው በቀጭኑ ይተለተልና በወንድ ሙሽራና በቅርብ ዘመድ እጅ ላይ ይጠለቃል፡፡ በመቀጠልም የሙሽራው እናት የሙሽሪትን ፀጉር ለሁለት በመክፈል በግንባሩዋ ግራና ቀኝ ሁለት ሹሩባ ይሰሯታል፡፡ ይህ የሹሩባ አሰራርም ልጅቱ ማግባቱዋን የሚያመለክት መለያ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም ሙሽሮቹ በተዘጋጀላቸው እልፍኝ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ጎረቤቶችና ዘመድ አዝማድ ለሙሽሪት የቤት ውስጥ መገልገያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን ያበረክቱላታል፡፡ በአከባቢው ማህበረሰብ ለሙሽሪት ከፍተኛ እንክብካቤ የሚደረግ ሲሆን ስጦታዎቹና መስተንግዶዎቹም የዚሁ አካል ናቸው፡፡

(ደራሽ ሚዲያ ከተሰኘ ፌስቡክ ገጽ፣ 2014፡፡ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ዓ.ነገሮች ከላይ በቀረበው ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት››፣ ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት በጽሑፍ መልሱ፤ በመቀጠልም በግል የመለሳችኋቸው መልሶች ላይ በቡድን ተወያዩና ቃላዊ ጽብረቃ አቅርቡ፡፡

1. በባህላዊ ጋብቻ ለጋብቻ የታሰበችውን ልጅ በተመለከተ ጥናት የሚያደርጉት የልጅቷ ቤተሰቦች ናቸው፡፡
2. የወንዱን ወላጆች ወክለው የሄዱት ሽማግሌዎች ቡናና ጨው በስጦታ መልክ የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡
3. የሙሽራው እናት የሙሽሪትን ፀጉር ለሁለት በመክፈል በግንባሯ ግራና ቀኝ ማግባቷን ለማመልከት ሹሩባ ይሰሯታል፡፡
4. ከታረደው በግ እግር አካባቢም ቆዳው በቀጭኑ ይተለተልና በሴት ሙሽራና በቅርብ ዘመድ እጅ ላይ ይጠለቃል፡፡
5. ሙሽራው ያለውን ጥንካሬና ክብሩን ለመግለጽ ሱሪውን አውልቆ የራሱ ትከሻ ላይ ጣል ያደርገዋል፡፡

## መልመጃ ሦስት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በምረጥ መልሱ።**

1. በቦረና የጋብቻ ስርዓት የሰርጉ ቀን እንዲቆረጥ የሚጠይቁት፡-

   ሀ. የሙሽሪት ቤተሰቦች　　　　ሐ. ጋብቻ ጠያቂው

   ለ. የሙሽሪት ጎረቤቶች　　　　መ. የአካባቢው ማህበረሰብ

2. ቡና በቅቤ ተቆልቶ /ቡን ቀላ/ ለሽማግሌዎች የሚቀርበው ____________________።

   ሀ. እሺታን ለማረጋገጥ ነው　　　　ሐ. ሽማግሌዎቹ ቡና ስላመጡ ነው

   ለ. አልተስማማንም ለማለት ነው　　　　መ. በአከባቢው እንግዳ ስለሚከበር ነው

3. በሙሽሪት ቤሰቦች ቤት ቤተዘመድ ተሰብስቦ የሚመካከርበት ምክንያት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አለመግባባት ቢፈጠር በሽማግሌ እንዲፈታ ለማሳሰብ

   ለ. ለጥሎሽ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለመወሰን

   ሐ. ለሙሽራው ሞጋሳ ለመስጠት (ስም ለማውጣት)

   መ. ሙሽራው ሙሽሪትን መንከባከብ እንዳለበት ለማሳወቅ

4. ለሙሽሪት የሚቀርቡት ስጦታዎችና የክብር መስተንግዶ የሚያመለክቱት፡-

   ሀ. የወንድ ሚዜዎች አካላዊ ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማመልከት

   ለ. የወንዱ ቤተዘመድ የሐብት መጠን ከፍ ያለ መሆኑን ለማሳየት

   ሐ. ስጦታና መስተንግዶ ቢደረግለት የሚጠላ አለመኖሩን ለማረጋገጥ

   መ. በአከባቢው ማህበረሰብ ለሙሽሪት ከፍተኛ ክብካቤ የሚደረግ መሆኑን

5. "በዚህ የጋብቻ ጥያቄ ሂደት…" ሲል የትኛውን የጋብቻ ጥያቄ ሂደት ማለቱ ነው?

ሀ. የወንድ ቤተሰቦች የሴቷን ቤተሰቦች ልጃችሁን ለልጄ የሚሉበትን

ለ. የሴት ቤተሰቦች የወንዱን ቤተሰቦች ልጃችሁን ለልጄ የሚሉበትን

ሐ. ሽማግሌዎች ልጅን ለጋብቻ ስጡን የሚል ጥያቄ የሚቀበሉበትን

መ. ሙሽሪትና ሙሽራው በፈቃዳቸው ለትዳር የሚተጫጩበትን

## መልመጃ አራት

የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። በ ‹‹ሀ›› ክፍል ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ የሆኑትን በ ‹‹ለ›› ክፍል ከቀረቡት ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መዝለቅ | ሀ. ተቃውሞ |
| 2. መመካከር | ለ. ተወሰነ |
| 3. ተቆረጠ | ሐ. ተቀባይነት |
| 4. መታጠቂያ | መ. መግባት |
| 5. ቅሬታ | ሠ. ቀበቶ |
| 6. ተሰሚነት | ረ. መነጋገር |
| | ሰ. መጎዳት |

# ክፍል አራት: መፃፍ

በመጻፍ ትምህርት ክፍል የድርሰት ክፍሎችን የተመለከተ ማስታወሻ ቀርቧል። ይህንኑ ማስታወሻ መሰረት በማድረግ የቀረቡትን መልመጃና ተግባር ስሩ።

## የድርሰት ክፍሎች

ድርሰት ሶስት ዋና ዋና ክፍሎችን አካቶ ይይዛል። እነዚህም መግቢያ፣ ሐተታ እና መደምደሚያ ናቸው።

ሀ. መግቢያ፡ ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ ቀድመን የምንጽፈው የማስተዋወቂያ ክፍል ነው። የመግቢያ ክፍል ድርሰታችን ስለምን ሊሆን እንደሚችል ለአንባቢ ጥቆማ ይሰጥልናል።

ለ. ሐተታ፡ ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ በመግቢያ ላይ የሰፈሩ ሃሳቦች በዝርዝር የምናቀርብበት ነው። በዚህ ክፍል የርዕሰ ጉዳያችን ዋናው ሃሳብ እየተተነተነ ይቀርባል።

ሐ. መደምደሚያ፡ ከመግቢያው አንስተን እስከ ሐተታ ድረስ ያለውን ሃሳብ ጠቅለል አድርገን የምናሰፍርበት የማሳረጊያ ክፍል ነው።

(ደበበ ኃይለጊዮርጊስ ፣ 2012:298)

## መልመጃ አምስት

**ቀጥለው የቀረቡላችሁን ነጥቦች መነሻ በማድረግ ሦስት አንቀጽ ያሉት አንድ ድርሰት ጻፉ።**

የመግቢያ ክፍል /አንድ አንቀጽ/

- ጋብቻ ማህበረሰብን የማቆሚያ አንዱ ምሶሶ ስለመሆኑ
- አጀማመሩም ሁለት ሰዎች (አንድ ወንድና አንድ ሴት) በሙሉ ፈቃደኝነትና በፍቅር የሚፈጥሩት መሆኑን
- ተቃራኒ ጾታ ካላቸው ግለሰቦች መጣመር ባሻገር የጋብቻ ፍሬ የሆኑ ልጆችን ስለሚያስገኝ ዘር እንዲተካና ትውልድ እንዲቀጥል ስለማስቻሉ

ሐተታ/ዋና/ ክፍል /ሁለት ወይም ሦስት አንቀጽ/

- ጋብቻ በሁለት ሊከፈል ስለመመቻሉ (ባህላዊ ጋብቻና ዘመናዊ ጋብቻ)
- ባህላዊ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ፈቃደኝነት ወይም በቤተሰብ ይሁንታ የሚከናወን ስለመሆኑ
- ሽማግሌ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ
- ባህላዊ ጋብቻ በባህላዊ አለባበስ፣ በባህላዊ ጭፈራ፣ በማህላዊ የምግብና መጠጥ ዝግጅት፣ በማህላዊ መጓጓዣ (ሙሽራው ሙሽሪትን በማዘል፣ በፈረስ ወይም በበቅሎ...) ወዘተ ታጅቦ ስለመከናወኑ
- ከጥንት ጀምሮ አሁንም ድረስ ጥቅም ላይ ስለመዋሉ፤ ነገር ግን እንደጠለፋ ያሉት ያለፍላጎት ጋብቻዎች ተቀባይነት እያጡ ስለመምጣታቸው
- ዘመናዊ ጋብቻ እንደ ባህላዊ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ፈቃደኝነት ወይም በቤተሰብ ምርጫ ሊከናወን ስለመቻሉ
- ሽማግሌ እዚህም ሊኖር ስለመቻሉ
- ስምምነቱ በመንግስታዊ ተቋም (ማዘጋጃ) እማኝነት ስለመከናወኑ
- ዘመናዊ አለባበስ፣ ዘመናዊ የምግብና መጠጥ ዝግጅት፣ በዘመናዊ ሙዚቃ ስለመታጀቡ
- እንዲሁም ዘመናዊ ማጓጓዣች (ዘመናዊ ተሽከርካሪዎች ስለመሳተፋቸው) ወዘተ

የመደምደሚያ/ማጠቃለያ/ ክፍል /አንድ አንቀጽ/

- በአጠቃላይ ጋብቻ ክቡር ስለመሆኑና ቤተሰብን ከመመስረት ባሻገር ማህበረሰብንም የሚያቆም ስለመሆኑ
- ስለሆነም ጋብቻን ማበረታታትና ማስቀጠል እንደሚገባ
- ጋብቻ ባህላዊም ዘመናዊም ሊሆን ስለመቻሉ፤ ነገር ግን

የተጋቢዎች እርስበርስ ትውውቅ ወሳኝ መሆኑን፤ ይህ ካልሆነ ግን ለመፍረስ አደጋ መጋለጡን

- ትውልድ የማስቀጠያ መሳሪያ በመሆኑ ሁሉም ሰው የጋብቻን ክቡርነት ተቀብሎ ጥበቃ ሊያደርግለት እንደሚገባ

## ተግባር ሦስት

ቀጥሎ ከተሰጧችሁ ርዕሶች አንዱን በመምረጥ ሶስቱን የ ድ ር ሰ ት ክፍሎች (መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ) የያዘ ድርሰት ጻፉ።

ሀ. ኮሮና

ለ. ትምህርት ቤቴ

መ. ሀገሬን እወዳታለሁ

ሐ. በጎ ስነ-ምግባር

# ክፍል አምስት: ቃላት

በቃላት ትምህርት ክፍል የቃላት አጠቃቀምን የተመለከተ ማስታወሻና መልመጃዎች ቀርበዋል። መልመጃዎቹን ትዕዛዛቱን ተከትላችሁ ስሩ።

### የቃላት አጠቃቀም

1. በፅሑፋችን ውስጥ የምንጠቀምባቸው ቃላት አንባቢያችን ሀሳባችንን እንዲረዳልን ለማድረግ ከፍተኛ ሚና አላቸው። በመሆኑም በአንድ ቋንቋ ውስጥ ተዘውታሪ /የተለመዱ/፣ ሙያዊ፣ የመሳሰሉትን ቃላት ልንጠቀም እንችላለን።

ተዘውታሪ ቃላት፡ ተዘውታሪ ቃላት የሚባሉት በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ በስፋት የሚታወቁና በዕለት ከዕለት የምንገለገልባቸው ቃላት ናቸው።

ምሳሌ፡ እርሻ፣ ምግብ፣ ዘመናዊ...

ሙያዊ ቃላት፡ የሚባሉት በተመሳሳይ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚያውቋቸውና የሚጠቀሙባቸው ሲሆኑ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል በግልጽ የማያውቃቸው ቃላት ናቸው።

ምሳሌ፡- ድሪ ገጽ፣ ቀዶ ጥገና፣ ተከታታይ ምዘና...

2. ቃላትን እያዋቀርን ዓረፍተ ነገር በምንመሰርትበት ጊዜ የቃላት

ድግግሞሽ፣ ድረታ፣ የተሰለቹ ቃላት፣ የተውሶ ቃላትና አገላለጽ መጠቀም የለብንም።

አላስፈላጊ የቃላት ድግግሞሽ፡- አንድን ቃል ያለ ዓላማ በዓረፍተነገር ውስጥ መደጋገም ቃላትን እንደማባከን ይቆጠራል፤ ሃሳብን ያደበዝዛል፤ ውበት ይቀንሳል፤ መልዕክቱ በቀጥታ እንዳይተላለፍ እንቅፋት ይሆናል።

ምሳሌ፡-‹‹ፍቅርን ያወቅሁት በእርሱ ነው፤ ህይወትን ያጣጣምኩት በእርሱ ነው፤ ተድላና ደስታዬን ያየሁት በእርሱ ነው።››

በዚህ ገለጻ አጽንኦት ለመስጠት የተደጋገሙ ቃላት አሉ። ይሁን እንጂ ድግግሞሹ አሰልቺ ስለሆነ ተገቢ አይደለም።

የቃላት ድረታ፡-አንድ ቃል በራሱ የሚፈልገውን ትርጉም ማስተላለፍ እየቻለ ሌላ ተጨማሪ ቃል ደርበን የምንጠቀምበት ከሆነ የቃላት ድረታ ይሰኛል።

ምሳሌ፡ ሀ. ራሴን አሞኝ ስለነበር ዲፕሮን መድሃኒት ውጤ ተኛሁ።

ለ. በእስር ቤቱ ውስጥ ጽሁፎችን መጻፍ የሚያስቀጣ ነበር።

በመጀመሪያው ምሳሌ ...ዲፕሮን ውጩ ተኛሁ ወይም ... መድሃኒት ውጩ ተኛሁ በማለት ድረታውን ማስቀረት ይቻላል። እንዲሁም በሁለተኛው ምሳሌ... መጻፍ የሚያስቀጣ ነበር። ማለት እየተቻለ ጽሁፎችን መጻፍ የሚለው ድረታን ያመላክታል።

የተሰለቹ ቃላት፡ ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ የምንሰማቸው አገላለፆች ናቸው። እነዚህ ቃላት በአንድ ወቅት ማራኪነትን የተላበሱ አባባሎች የነበሩ፤ ነገር ግን አሁን ትኩስነታቸውንና ኃይላቸውን ያጡ ቃላት ወይም ሀረጋት ናቸው።

ምሳሌ፡-ውድ ወንድሜ የሰማይ ርቀቱን፣ የባህር ጥልቀቱን፣ የአሸዋ ብዛቱን፣ የከዋክብት ድምቀቱን ያህል እንደምን አለህ!

በቀረበው አገላለጽ በቀደመው ጊዜ ደብዳቤ ሲጻፍ የተለመደና ለዛ ያለው ነበር። በአሁኑ ጊዜ ይህ አገላለጽ የተሰለቸ ሆኖ እናገኘዋለን።

## መልመጃ ስድስት

ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተደገሙ፣ የተሰለቹና የተደረቱ ቃላት ይገኛሉ። ስለሆነም በምሳሌው መሰረት ቃላትና ሃረጋቱን በሌሎች ቃላት በመተካት ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፏቸው።

ምሳሌ፡

ሀ. በእግሩ ተራምዶ ደረሰብኝ። (ድረታ)

ተራምዶ ደረሰብኝ። (የተስተካከለ)

ለ. አጉል ሱስን የመተውና እርግፍ አርጎ የመተው እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። (ድግግሞሽ)

ሱስን እርግፍ አድርጎ የመተው እርምጃ ያስፈልጋል። (የተስተካከለ)

1. በርዕሰ ከተማችን የመጠለያና የመኖሪያ ቤት ችግር አለ።
2. አርአያ መሆን ሲገባቸው አርኣያ አይሆኑም።
3. በሀቅ ላይ የተመሰረተ እውነተኛ አባባል ነው።
4. ስቃይ በርትቶብኝ እየተሰቃየሁ ቆየሁና ስቃዬን ልገልጽለት ፈልጌ አጎቴ ቤት በስንት ስቃይ ደረስኩ።
5. የአባቴ እህት የሆነችው አክስቴ መጣች።
6. ታላቁ ደራሲ በትናንትናው እለት ተቀብሮ ግብአተ መሬቱ ተፈጸመ።
7. በአእምሮዬ የማስበውን ያወቀብኝ መስሎኝ ድንግጥ አልኩ።

ለ. በሚከተሉት ዓፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙ ሙያዊ ቃላትን ለይታችሁ አውጡ።

1. መሐመድ በምህንድስና ትምህርት ትናንት ተመረቀ።
2. ቤቶች በሚገነቡበት ወቅት የውሃ ልካቸው ተጠብቆ መስራት አለባቸው።

3. ሰላምታ መለዋወጥ ከባህላችን አንዱ ነው።

4. መልካም ህይወት እንዲገጥማችሁ እመኛላችኋለሁ።

## መልመጃ ሰባት

**ከዚህ በታች የተጓደለ አንቀጽ እንድታሟሉ የሚረዱ ቃላት ተሰጥተዋል፤ አንቀጹን በመጻፍ ቃላቱን በተገቢ ቦታቸው አስቀምጧቸው።**

ሀ. ወሳኝነት ሐ. ሚስጥራትን ሠ. ብልጭታ ሰ. ይሆኑብናል

ለ. አይኖረውም መ. ፊደላት ረ. አንጻር ሸ. በፋሽኖች

እያንዳንዱ የቀለም ጠብታ ልዩ _______________ የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። የምንጠቀማቸው ቀለማት እራሳቸውን ችለው እንደ _______________ የሚነበቡ ናቸውና፣ ቀለማቱን በተገቢው ካላሰባጠርናቸው ፊደላቱ የተዘበራረቀ መጽሃፍ ጽፎ እንደማሳተም _______________ ። በተመሳሳይ _______________ ውስጥም ጊዜና ሁኔታን ያላገናዘበ ቀለማትን የምንጠቀም ከሆነ የምናቀርብለት ማህበረሰብ ይህንን የመቀበል ፍላጎት _______________። ጊዜና ሁኔታዎችን ማገናዘብ በእጅጉ _______________ አላቸው። በአብዛኛው የምንከተላቸው የፋሽን ፈጠራዎች ውድቀት የሚጀምረው ከእነዚህ _______________ ነው። የፈጠራዎቹ እድሜም በጣም አጭርና እንደ መብረቅ _______________ ገና ሳይታዩ የሚከስሙ ይሆናሉ።

# ክፍል ስድስት፡ ሰዋስው

በሰዋስው ትምህርት ክፍል የአረፍተነገር አይነቶችን ከአገልግሎታቸው አንጻር የምትረዱበት ማስታወሻ ቀርቧል። ስለሆነም ማስታወሻውን መሰረት አድርጋችሁ የቀረበውን መልመጃ ስሩ።

## የዓረፍተነገር ስልቶች

ዓረፍተነገሮች ከአገልግሎታቸው አንጻር ጥያቄያዊ፣ ሀተታዊ፣ ትዕዛዛዊና አጋናኝ በመባል ይታወቃሉ።

ሀ. ሐተታዊ ዓረፍተ ነገር፡ ስለ አንድ ድርጊት ወይም ሁነት የሚያትትና መልዕክትን ማስተላለፍ ዓላማው አድርጎ የሚመሰረት ነው። ሐተታዊ ዓረፍተነገር በውስጡ አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገሮችን ይይዛል።

አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር፡- በአዎንታ የሚነገር የዓረፍተ ነገር ስልት ነው።

ምሳሌ፡- ጓደኛዬ በጣም ጎበዝ ተማሪ ናት።

እውቀት የማይሞት ሃብት ነው።

አሉታዊ ዓረፍተነገር በአሉታ ወይም በአፍራሽ የሚነገር የዓረፍተ ነገር ስልት ነው። በውስጡም አፍራሽ የሆኑ ቅጥያዎችን (አል-ም፣ አይ- ም፣ አን - ም) ወዘተ... ይይዛል።

ምሳሌ፡- ጎበዙ ተማሪ ዛሬ አልመጣም።

ጓደኛዬ የእግር ኳስ መጫወት አይወድም።

ለ. ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር መጠይቃዊ ቃላትን ወይም የጥያቄ ምልክትን በመጠቀም የሚመሰረት ሲሆን ምላሽ የሚያስፈልገው የዓረፍተነገር አይነት ነው።

ምሳሌ፡- የኮሮና ቫይረስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው የት ነው?

ጓደኛሽ ነገ መምጣት ትችላለች?

ሐ. ትዕዛዛዊ ዓረፍነገር አንድ ነገር እንዲከናወን ወይም እንዲፈጸም ሲባል በትዕዛዝ መልክ የሚቀርብ የዓረፍተነገር ስልት ነው። ይህ ዓረፍተነገር በአራት ነጥብና በትዕምርተ አንክሮ ሊቋጭ ይችላል።

ምሳሌ፡ ነገ ሀገር ተረካቢ እንድትሆኑ በርትታችሁ ተማሩ!

መልዕክቱን በነገርኩሽ መሰረት አድርሽ።

መ. አጋናኝ ዓረፍተነገር ነገሮችን በማጋነን፣ በመገረም፣ በመደነቅ የሚያቀርብ ዓረፍተነገር ሲሆን መደሰትን፣ መገረምን፣ መናደድና መሰል ሀይለኛ ስሜቶችን ያንፀባርቃል።

ምሳሌ፡- ዋው! ዛሬ ቀኑ ደስ ይላል።

እሰይ! እህቴ ነገ ከውጭ ሃገር ትመጣለች።

## መልመጃ ስምንት

ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ሐተታዊ (አዎንታዊ፣ አሉታዊ)፣ ትእዛዛዊ፣ መጠይቃዊና አጋናኝ መሆናቸውን ለዩ።

1. እመጣለሁ ባለችበት ሰዓት አልደረሰችም።
2. ወደ ኢትዮጵያ መቼ ትመለሳለህ?
3. ትምህርት ለሃገር እድገት መሰረት ነው።
4. በዚህ አደገኛ ስፍራ ላይ ስትጫወት ሁለተኛ እንዳላይህ!
5. መምህራችን መጽሐፍ ማምጣት እንዳለብን ነገሩን።
6. የክብር እንግዳው ሳይመጣ ቀረ።
7. ኦ! ፈጣሪዬ ከዚህ ፈተና አውጣኝ።
8. ዘምዘም ህይወቷን ሙሉ ለሃገሯ እየሰራች ነው።

ለ. በሚከተሉት ቃላት ሐተታዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ጥያቄያዊና አጋናኝ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ።

1. ፈለገ (ሐተታዊ)
2. ብሩህ (አጋናኝ)
3. ራእይ (ጥያቄያዊ)
4. መሰረት (ትዕዛዛዊ)
5. አመረቃ (ሐተታዊ)
6. ኩራት (አጋናኝ)
7. ቆረጠ (ጥያቄያዊ)
8. አረንቋ (ሐተታዊ)

ሐ. አዎንታዊ የሆኑ አምስት ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ወደ አሉታዊ ዓረፍተነገር ለውጧቸው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ‹‹የቦረና ባህላዊ ጋብቻ›› በሚል ምንባብ አንብባችኋል። ይህ ምንባብም የማንበብ ክሂላችሁን በማሻሻል ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል። እንዲሁም ስለ ክርክር ምንነት፣ ዝግጅትና አቀራረብ ተምራችኋል። በዚህም ክርክር በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል በአንድ ርዕሰ ጉዳይ የተለያየ አቋምን በማራመድ የሚደረግ የሃሳብ ሙግት ነው። የክርክር አዘገጃጀት እና አቀራረብ መመሪያ መሰረት አድርጋችሁም ክርክር አቅርባችኋል። በማስከተልም ድርሰትንና የድርሰት ክፍሎችን ተምራችኋል። እነዚህም መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ ሲሆኑ ክፍሎቹን ባካተተ መልኩ በተሰጣችሁ ርዕስ ድርሰት ጽፋችኋል።

በሌላኛው የቃል ትምህርት ክፍል የቃላትን አውዳዊ ፍች በንግግርና በጽሁፍ ውስጥ ሰጥታችኋል። የቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ ዘወትራዊና ሙያዊ ቃላትን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በመለየት ጽፋችኋል። ከዚህም በተጨማሪ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰለቹ፣ የተደረቱና የተደጋገሙ ቃላትን በመለየት አስተካክላችሁ መጻፍ እንዳለባችሁ ተገንዝባችኋል። አንድን ቃል ያለ ዓላማ በዓረፍተነገር ውስጥ መደጋገም አስፈላጊ እንዳልሆነ፤ አንድ ቃል በራሱ የሚፈልገውን ትርጉም ማስተላለፍ እየተቻለ ሌላ ተጨማሪ ቃል ጨምረን መጠቀም እንደሌለባችሁና ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ የምንሰማቸው አገላለጾች በሌላ ጊዜ ትኩስነታቸውን ስለሚያጡ ይህን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንዳለባችሁ አይታችኋል። በመጨረሻም የዓረፍተነገር ስልቶችን በመለየት ሐተታዊ፣ ትእዛዛዊ፣ ጥያቄያዊና አጋናኝ ዓረፍተነገሮችን መስርታችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ክርክር የሚያቀርብ ሰው ከሚተገብራቸው ነጥቦች መካከል አራቱን ጠቅሳችሁ ማብራሪያ ስጡባቸው።

3. ለሚከተሉት የቃላት አጠቃቀሞች ምሳሌ የሚሆኑ ሁለት ሁለት አረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

ሀ. ሙያዊ ቃላት

ለ. ዘወትራዊ ቃላት

ሐ. አላስፈላጊ የቃላት ድግግሞሽ

መ. ድረታ

ሠ. የተሰለቹ ቃላት

3. የሚከተሉትን የአረፍተ ነገር ስልቶች ተጠቅማችሁ ሁለት ሁለት ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ።

ሀ. ጥዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር

ሐ. ሐተታዊ ዓረፍተ ነገር

ለ. ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር

መ. አጋናኝ ዓረፍተ ነገር

4. መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ ያለው ከአንድ ገጽ ያልበለጠ አጭር ጽሁፍ ጻፉ።

5. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱና የያዙትን አውዳዊ ፍቺ አመልክቱ።

ሀ. ራደ

ሐ. አገደ

ለ. በላው

መ. ሰማ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ሁለት ስር የቀረበላችሁን ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✔)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | |
|---|---|---|
| 1. | ስለባህላዊ ጋብቻ የማውቃቸውን ለጓደኞቼ መናገር እችላለሁ። | |
| 2 | ንግግሮችን በማዳመጥ ግብረ መልስ መስጠት እችላለሁ። | |
| 3 | የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን መሰረት በማድረግ በማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ ላይ መከራከር እችላለሁ። | |
| 4. | ለቃላት ዓውዳዊ እና መዝገበ ቃላዊ ፍች መስጠት እችላለሁ። | |
| 5 | የጽሁፍን ሀሳብ አገናዝቤ አነባለሁ። | |
| 6 | የድርሰት ክፍሎችን መለየት እችላለሁ። | |
| 7. | የድርሰት ክፍሎችን መሰረት አድርጌ በተሰጠኝ ርዕስ ድርሰት መጻፍ እችላለሁ። | |
| 8 | በጽሁፍ ውስጥ ሙያዊና ዘወትራዊ ቃላትን መለየት እችላለሁ። | |
| 9. | የተሰለቹ ቃላት፣ የቃላት ድግግሞሽና ድረታ ለይቼ ማስተካከል እችላለሁ። | |
| 10. | ዓረፍተ ነገር ስልቶችን በመለየት በተሰጡ ቃላት ዓረፍተ ነገር መመስረት እችላለሁ፡ | |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዱ ቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

# ምዕራፍ ሶስት

## ሴቶች እና ልማት

### የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በሴቶች እና ልማት ዙሪያ የቀረቡ ይዘቶችን አዳምጣችሁ የተናጋሪውን ሀሳብ ትገመግማላችሁ፤
- አንድን ምንባብ አንብባችሁ ተፈላጊውን ሀሳብ ታወጣላችሁ።
- በሴቶችና ልማት ዙሪያ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ያገኛችሁትን ሀሳብ በቃል ታንጸባርቃላችሁ፤
- ለተሰጣችሁ ጽሁፍ በአንድ አንቀጽ ማጠቃለያ ትጽፋላችሁ፤
- ዓርፍተነገሮችን ከሰዋስዋዊ ቅርጻቸው አንጻር ትለያላችሁ።

## ክፍል አንድ፡ ማዳመጥ

በማዳመጥ ክፍል ለማዳመጥ ክሂል መለማመጃ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ምንባቡን መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በትኩረት በማዳመጥ ጥያቄዎችን ስሩ።

## የሴቶች ሚና

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በቅርቡ ሴቶችን በተመለከተ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን (ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ማህበራዊ መገናኛዎች) የተላለፈና ያዳመጣችሁት ዝግጅትን አስመልክቶ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ሀሳብ ተለዋወጡ።
2. በአካባቢያችሁ ሴቶች ለቤተሰብ፣ ለማህበረሰብ እና ለሀገር እድገት የሚያበረክቱትን አስተዋጽዖ በማንሳት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለክፍሉ አጋሩ።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የአንድ ሀገር እድገት ያለ ሴቶች ________ የትም ሊደርስ አይችልም።
2. የሴቶች ተግባር የሚጀምረው ___________በመንከባከብና ትክክለኛ ምሪት በመስጠት ነው።
3. አንድ ማህበረሰብ ተመስርቶ ሊቆም የሚችለው እንዴት ነው?
4. ቀጣዩ የምንባቡ ክፍል ምን ምን ጉዳዮችን ሊያነሳ ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ያዳመጣችሁን ምንባብ መሰረት በማድረግ ተገቢውን ምላሽ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. የሴቶችን ተሳትፎ ይጠይቃሉ ተብለው በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት ተግባራት ምን ምን ናቸው?
2. ስለሴቶች 'በልበ ሙሉነት መናገር ይቻላል' የተባለው ምኑን ነው?
3. ሴቶች በማኅበረሰብ ፖለተካ ለውጥ ውስጥ ያላቸው አበርክቶ በምን ይገለጻል?

4. ሴቶች ለማህበረሰብ ህልውና የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ የሚዘልቀው እስከምን ድረስ ነው?

5. ሴቶች ለህጻናት የህይወትን ትርጉም ባያስተምሩ ኖሮ ምን ይከሰት ነበር?

6. ያዳመጣችሁትን ምንባብ አጠቃላይ ሀሳብ በአንድ አንቀጽ አጠቃላችሁ ጻፉና ለክፍሉ በንባብ አቅርቡ።

# ክፍል ሁለት፡ መናገር

በዚህ ክፍል ንግግርን የምትለማመዱባቸው ተግባራትና የቃለመጠይቅ አተገባበርን የተመለከተ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። ትዕዛዙን ተከትላችሁ ተግባራቱን ስሩ።

## ተግባር አንድ

አጀንዳቸውን በሴቶች እድገት ላይ ያደረጉ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን (ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ ወ.ዘ.ተ) አዳምጡ። ስታዳምጡ የተናጋሪዎቹን መልዕክት፣ አመለካከትና ዝንባሌ በአግባቡ ከመረመራችሁ በኋላ የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

## ተግባር ሁለት

በአካባቢያችሁ ወደሚገኙ የህዝብ መገልገያ ተቋማት ቢሮ ኃላፊዎች በመሄድ ከታች የቀረበውን የቃለ መጠይቅ መመሪያ መሰረት አድርጋችሁ 'ሴቶች በሀገር እድገት ላይ እያደረጉ ስላሉት አስተዋጽዖ' ቃለ መጠይቅ አድርጉ። መረጃ ለመሰብሰብ እንድትችሉ የሚከተሉትን ነጥቦች ተግባር ላይ አውሉ።

1. አምስት አባላት ያለው ቡድን በመመስረት መረጃ ሊገኙባቸው የሚችሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን አዘጋጁ (ጥያቄዎቻችሁ ሴቶች ለአገር ዕድገት ስለሚጫወቱት ሚና ጥሩ መረጃ የሚሰጡ መሆናቸውን አረጋግጡ።)

2. ስለርዕሰ ጉዳያችሁ በቂ መረጃ ሊሰጧችሁ የሚችሉ ሶስት ሰዎች ምረጡ።

## ቃለ-መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ጠያቂው ከተጠያቂው ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ መረጃ የሚሰበሰብበት ሒደት ነው። ቃለ መጠይቅ የተዋቀረ ወይም ያልተዋቀረ ሊሆን ይችላል። የተዋቀረ ቃለመጠይቅ በአቀራረብ ጊዜ የምንተገብራቸው ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የቃለ መጠይቅ አቀራረብ

- ለቃለ መጠይቁ ዝግጁ በመሆናቸው ተጠያቂዎችን በቅድሚያ ማመስገንና ዓላማውን በአጭሩ ማስተዋወቅ፣
- የወዳጅነትና የመግባባት ስሜት መፍጠር፣
- ጥያቄዎችን በልበ ሙሉነት በቅደም ተከተል ማቅረብ፣
- ትህትና ያልተለየው አቀራረብ ማሳየት (ግትርና ተሟጋች አለመሆን)
- አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነትን ማስወገድ፣
- ዋና ዋና ሀሳቦችን እያዳመጡ ማስታዎሻ መያዝ፣
- በተጠያቂው ዘንድ ግልጽና ታማኝ ሆኖ መገኘት (የመዘገቡትን መረጃ ለተጠያቂው መልሶ ማሳየት)
- ሁኔታዎችን እዳስፈላጊነቱ ለመቀያየር ዝግጁነት ማሳየት
- ቃለ መጠይቁ ሲጠናቀቅ ተጠያቂውን ማመስገን የሚሉት በቃለ መጠይቅ፣ አቅርቦት ወቅት የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው።

3. በጥያቄዎቻችሁ መሰረት የሰበሰባችኋቸውን መረጃዎች በጽሁፍ አዘጋጅታችሁ በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

# ክፍል ሦስት፡ ማንበብ

በማንበብ ትምህርት ክፍል 'አበበች ጎበና' በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቧል። ትኩረት ሰጥታችሁ ምንባቡን አንብቡና ተከትለው የመጡትን መልመጃዎች ስሩ።

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. የኢትዮጵያ ሴቶች ተሳትፎ በሀገር እድገት ላይ ምን ምን አስተዋጽዖ ያበረክታል ትላላችሁ? በቡድን ሁናችሁ በመወያየት የደረሳችሁበትን ለክፍሉ በቃል አቅርቡ።
2. በማንኛውም የሙያ መስክ ላይ ተሰማርተው አንቱታን ያተረፉ የሀገራችንን ሴቶች ጥቀሱ።
3. ከዚህ ቀደም ስለአበበች ጎበና ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ አዎ ከሆነ ስለአበበች ጎበና የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ።



(አበበች ጎበና ከ 1928 — 2013 ዓ.ም)

## አበበች ጎበና

ጊዜ ባለሥልጣን ነው። ሰው የተባለ ፍጥረት ሊቋቋመው የማይችለው ክንድ አለው፤ የሚሸነፍ አይመስልም። አንዳንድ ሰው ግን አለ፤ በጊዜ ላይ ይሠለጥንበታል። እንዴት ቢሉ በጊዜ ፊት ጊዜ የማያስረሳው፣ ዘመንም፣ ትውልድም ተሻጋሪ ሥራን ይሠራልና ነው። ብዙዎች ‹‹ማን ብለን እንሰይማት!› ብለው ተቸግረው በየፊናቸው የኮረኮራቸው ስሜት ባቀበላቸው የፍቅር ቃል የሚጠሯቸው የክብር ዶክተር አበበች ጎበና እንዲያ ካሉ ሰው መካከል ናቸው። ጊዜን ያሸነፉ፣ በጊዜ ላይ ንግሥት የሆኑበት ብርቱ እና ባለውለታ እናት። በእድሜ በምንሰፍረው ጊዜ፣ በየአንዳንዱ ሰዓትና ደቂቃ፣ ቀንና ወር፣ ወራትና ዓመት ውስጥ የወለዱን፣ ያሳደጉን፣ ማንም ሊያውቀው ይችል ያልነበረን የተተወ ትውልድ በለምለም ልባቸው ጻንሰው፣ በመልካም እናትነት አንስተው ያሳደጉ እናት ናቸው።

አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ፤ አንድ ሰው ወደ አበበች ጎበና ቀርቦ በመሣሪያ አስፈራርቶ ሊዘርፏቸው ይሞክራል። ታድያ ብዙም ሳይቆይ ያ ሰው በተመሳሳይ በፈጸመው ሌላ ድርጊት ተይዞ ወደ እስር ቤት ይላካል። ይሄኔ ልጆቹ ያለአሳዳጊ ቀሩ። ጉዳያቸው ትውልድ፣ ልጆችና ሕጻናት ነበሩና አበበች የዚህን ሰው ልጅ ሊያሳድጉ ወደ ጉያቸው አስገቡ። በቃ! ልባቸው እንዲህ በቅዱስ መጽሐፍ አልያም በቅዱስ ቁርዓን ተመዝግቦ እንዳለ የጻድቅ ሰው ሥራ፣ በየጊዜው ለበጎነት የሚያተጋቸው ነው። አበበች ጎበና ምንም የሥጋ ልጅ ሳይኖራቸው፣ እናት ተብለዋል፤ ናቸውና። ብዙ ቤተሰብ የጠፋበትን ደስታ በእርሳቸው አግኝቷል። ከፈረሰ ቤተሰብ አውጥተው ‹የእኔ› የሚሉትን ቤት እንዲመሠርቱ ያገዟቸውና የአበበች ውለታ ያለባቸው ጥቂት አይደሉም። ያ ውለታና ድካማቸው፣ ቀናነትና እናትነታቸው በብዙዎች ልብና ሕይወት ታትሟል። በአካል ስጋ አብረውን ባይሆኑም ትውልድ የሚቀባበለው መልካም ሥራቸው አረአያ ሆኖ ሲያስመሰግናቸው ይኖራል።

አበበች ጎበና የተወለዱት ጥቅምት 10 ቀን 1928 ፍቼ ከተማ ነው። ጊዜው ጣልያን ኢትዮጵያን የወረረችበት ነበርና ገና የአንድ ዓመት እድሜን በቅጡ ሳይዙ አባታቸውን በጣልያን ወታደሮች ጥይት ተነጠቁ።

ልጅነታቸው አልጋ በአልጋ አልነበረም፤ በአስራ አንድ ዓመታቸው በቤተሰብ ግፊት ወደ ትዳር ለመግባት ተገደዱ። ሆኖም ይህን ግዳጅ አልተቀበሉትም። ስለዚህም ከቤታቸው ጠፍተው እናታቸው ቤት አቀኑ። ነገር ግን ከእናታቸው በኩል ‹‹እንኳን መጣሽልኝ!›› የሚል አቀባበል አላገኙም። ይልቁንም ‹‹እንዴት ታዋርጅናለሽ!›› ተባሉ፤ ወደትዳራቸውና ባላቸው እንዲመለሱ ሆነ። ይህን ጊዜ ነገሩ ተባባሰ፤ በድጋሚ ቤት ጥለው እንዳይወጡ በጠባቂ በር ተዘጋባቸው። ያም አላገዳቸው፤ ከእለታት በአንዱ ቀን በእኩለ ሌሊት አምልጠው መንገድ ጀመሩ ።ሦስት ቀን በየደረሱበት እያረፉ ከተጓዙ በኋላ አንድ የጭነት መኪና አሽከርካሪ ወደ አዲስ አበባ ሊያደርሳቸው ይተባበራቸዋል። በደረሱ ግዜ ግን የአሽከርካሪው ሁኔታው አላምር ብሏቸው ነበርና ፒያሳ ላይ ተሽከርካሪው በቆመበት አጋጣሚ ወረዱ። ልብ በሉ! ገና የአስራ አንድ ዓመት ልጅ ናቸው። በጊዜው አንድ የተከበሩ የተባሉ ሰው በፒያሳ ጊዮርጊስ መንገድ ሲያልፉ አጥሩ ጥግ የተቀመጠችውን ትንሽ አዳጊ ልጅ ተመለከቱ። አልፈው አልሄዱም፤ ጠጋ ብለው አነጋግረው ትንሿን ልጅ ወደ ቤታቸው ይዘው ሄዱ። እንደልጃቸው ቆጥረው አሳደጓት። በወቅቱ በነበረው የእጅ ሥራ ትምህርት ቤት ሳይቀር የመማር እድል እንድታገኝ  አደረጉ።

### የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አበበች ጎበና ተወልደው ብዙም ሳይቆዩ የተከሰተው ምን ነበር?
2. አበበች ጎበና ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ስንት አመታቸው ነበር?
3. ከቤታቸው ጠፍተው ወደ _______________ ቤት አቀኑ::

አበበች ጎበና በጊዜው የእህል ሰብል በሚባል ድርጅት ውስጥ ተቀጥረውም ሠርተዋል። ሆኖም ሕይወታቸውን በምንኩስና የማሳለፍ ጽኑ ፍላጎት ነበራቸው። ቤተሰቦቻቸው ግን ትዳር እንዲመሠርቱ ስለሚፈልጉ አገቡ። ከትዳሩ ግን ልጅ አልተገኘም። እንዲያም ሆኖ የተመቻቸ ኑሮን ይገፉ ነበር። ጊዜው ደረሰ፤ 1972 ነው። አበበች ጎበና የግሸን ማርያም በዓል ለማንገሥ በቀድሞ አጠራር ወሎ ክፍለ ሀገር አመሩ። በጉዞ መካከል በድርቅ ምክንያት እናታቸውን ያጡ፣ ነፍስ ያላወቁ ሕጻናትን ተመለከቱ።

ሥራቸውን በዚህ ጀመሩ። ትንሽና ተራ ጉዳይ አላደረጉትም። ይልቁንም የሞቀ ቤታቸውን ትቶ ለመውጣት የማይሰስቱለት የሕይወት ግብና ዓላማቸው አደረጉት። ‹የእኔ› የሚለውን በአንድ አጥር ጊቢ፣ በአንድ ቤት፣ በደም የተሳሰረና በሥጋ የተዛመደ ብቻ አይደለም የሚል አቋም ሳይዙ አልቀሩም። ‹የእኔ›ን ከፍ አደረጉት፤ አገር ሆኑ፤ አገር አከሉ።

በአንድ ዓመት ውስጥ ሃያ ሕጻናትን ለማሳደግ ሰበሰቡ። ይህ ግን በቤተዘመዶቻቸው ዘንድ ‹‹አበበች አብዳለች››ን አስከተለባቸው። የበጎነታቸው ልቀቱ የቅርቤ ያሏቸው ሰዎች ጤናቸውን እስኪጠራጠሯቸው ነበር። እርሳቸው ግን ገፉበት። የሞቀውን ቤት ትተው፣ ከተተዉ፣ ብቻቸውን ከቀሩ ሕጻናት ጋር ተኮራምቶ፣ ችግራቸውን መካፈልና የእነዚህን ሕጻናት ነገ መሥራት ላይ አተኮሩ። በኢትዮጵያ መንግሥታዊ ያልሆነ አገር በቀል የሕጻናት ማቆያ ድርጅት በአበበች ጎበና የመጀመሪያ ሆኖ ተመሠረተ።

ከብዙ ሀብት መካከል ጥቂት ፍራንክና ጌጣጌጦች ይዘው ከቤታቸው የወጡት አበበች ጎበና፣ ያንንም ለሕጻናቱ አዋሉት። ግን አላዘለቃቸውም። ስለዚህም በጊዜው በገበያው አዋጭ ነው ያሉትን ቆሎ አዘጋጅተው መሸጥን ተያያዙት። ልጆቼ ስላሏቸው ልጆቻቸው፣ ማንም ግዴታን ሳይጥልባቸው፣ እንደ ጻድቅ መልካምነትን በተጎናጸፈ ልባቸው ገፊነት የተነሳ መደብ ላይ ተኙ፣ የሚሞቅ አልጋ ግን ነበራቸው፤ ልብሳቸውን ቀድደው ለሕጻናት አለበሱ፣ ያለውን ቆርሰው ለልጆች አካፍለው ጾማቸውን አደሩ።

አላረፉም። ጥረታቸው ከተለያዩ የውጪ የእርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያገኙ አስቻላቸው። እርሳቸውም አልቦዘኑም፣ የቆሎ ንግዱ ላይ የተለያዩ ተጨማሪ ሥራዎችን አክለው ገቢ መሰብሰቡ ላይ በረቱ። ተሻገሩት። በልጅነት፣ በወጣትነትና በአዋቂነት ዘመን ሁሉ እንደየሁኔታው በጊዜው ውስጥ ተፈትነዋል። ጊዜ አላስቆማቸውም፣ አልተሸነፉለትም። እንደውም የነገ አዋቂ የሚሆኑ ጨቅላ ሕጻናት ላይ ሊሠለጥን የነበረን ጊዜ አስረጁት። በሥጋ ሳይሆን በነፍስ መመሪያና መርህ ኖረዋልና፣ የሥጋቸው መድከም አቅማቸውን ቢገታ ነፍሳቸውንና ለአገር ያጋቡትን መንፈስ አይረታም።

አበበች ጎበና ባይጠይቁም ለሰጡት አገልግሎት የምስጋናና የእውቅና

ሽልማቶች ተበርክተውላቸዋል። ድርጅቱን ከመሠረቱ ጀምሮ ደመወዝ እንኳ ተቀብለው የማያውቁት አበበች ግን፣ የሚሰጣቸውን የገንዘብም ሆነ ጌጣጌጥና ልዩ ሽልማት ለራሳቸው ተጠቅመውት አያውቁም። ለልጆችና ሕጻናት ፈገግታ አውለውታል፣ በልጆችና ሕጻናት ፈገግታና ሕይወት ውስጥ ሽልማታቸውን ተቀብለዋል።

## አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጥንቃቄ በማንበብ ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ።**

1. በጊዜ ፊት ጊዜ የማያስረሳው፣ ዘመንም፣ ትውልድም ተሻጋሪ ሥራን የሚሰራ ሰው ጊዜን ያሸነፈ ነው።
2. አበበች ጎበና በመሣሪያ አስፈራርቶ ሊዘርፋቸው የነበረን ሰው አሳስረው እንዲቀጣ አድርገዋል።
3. አበበች ጎበና አባታቸውን በጣልያን ወታደሮች ጥይት ሲነጠቁ እድሜያቸው አስራ አንድ ነበር።
4. አበበች ጎበና ያላቸውን ጥሪት ለልጆችና ሕጻናት ፈገግታ አውለውታል፤ በዚህም ደስተኛ ነበሩ።
5. አበበች ጎበና በወቅቱ ከገጠማቸውችግር ለመላቀቅ ቆሎ አዘጋጅተው እስከመሸጥ ደርሰው ነበር።
6. የአበበች ጎበና የትውልድ ስፍራ ምዕራብ ሸዋ ዞን አምቦ ከተማ አካባቢ እንደነበር የሚታወቅ ነው።

**ለ. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሁፍ መልስ ስጡ።**

1. አበበች ጎበና ያለእድሜያቸው ከተዳሩበት ትዳር አምልጠው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የገጠማቸው ምን ነበር?

2. አበበች ጎበና የተበረከተላቸው ሽልማት ምን አይነት ነበር?

3. አበበች ጎበና በቤተሰባቸው ዘንድ “አብዬለች” ያስባላቸው ምን ነበር?

4. አበበች ጎበና በህይወታቸው ያጋጠማቸውን ተግዳሮቶች እናንተ ገጥሟችሁ ቢሆን ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

## መልመጃ ሦስት

**ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን ጻፉ።**

ሀ. አላዘለቃቸውም

ለ. አዋጭ

ሐ. ተሻገሩት

መ. መርህ

ሠ. ተበርክተውላቸዋል

ረ. ልቀቱ

ሰ. ነፍስ ያላወቁ

ሸ. የወረረችበት

ቀ. ቀናነት

በ. የሚያተጋቸው

# ክፍል አራት: መጻፍ

**በመጻፍ ትምህርት ክፍል መጻፍን የምትለማመዱባቸው የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ትዕዛዛቱን ተከትላችሁ ስሯቸው።**

## መልመጃ አራት

1. በኢትዮጵያ በሃገር ዕድገት ላይ ሴቶች ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በተመለከተ ሁለት አንቀጽ ጻፉ።
2. ከላይ አበበች ጎበና በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሃሳብ በአንድ አንቀጽ አጠቃላችሁ ጻፉ።
3. ቀጥሎ ሶስት አንቀጽ ያለው ድርሰት ቀርቦላችኋል። ሁለቱ አንቀጾች ቀጥለው የቀረቡ ሲሆን እናንተ የመጨሻውን (ማጠቃለያ) አንቀጽ ጻፉ።

በዚያ ለጋ ዘመኔ ወዜ ከፊቴ ላይ ሳይመጠጥ፣ ተንኮልና ነገር በልቤ ውስጥ ባልሰረፀበት ዕድሜ በከብት አጋጅነት ወላጆችን እረዳ ነበር። የዛሬን አያድርገውና በዚያ ሙያ ከመጠን በላይ እደሰት እንደነበር ዛሬ ከተሜ ስለሆንኩ ልክድው አልችልም። ፀሀይ ፍንጥቅ ስትል ከብቶቼን ከበረት አውጥቼ፣ በቁልቁለቱና በአግድመቱ እያንጋጋሁ ወደማሰማሪያው መስክ ይገፔ ስሄድ አእምሮዬ ፍፁም ንፁህ በሆነ የደስታ ውሃ ይታጠብ ነበር።

የደስታዬ ምንጮች ብዙ ነበሩ። የነፋሱ ፉጨት፣ የወፎቹ ዝማሬ፣ የወንዞቹ አወራረድና የአበቦቹ ሽታ በተፈጥሮ የሰጡኝ አስደሳች ባልንጀሮቼ ነበሩ። በቀትር ጊዜ የፀሃይ ሃይል በጣም አቃጣይ ሲሆን ከብቶችን በውሃ አረካቸው ነበር። በዛሬው መስታወት ወደ ኋላ ሳየው በጣሙን እገረማለሁ።

4. በአካባቢያችን (ሀገራችን) ሴቶች ለቤተሰባቸው፣ ለአካባቢያቸው ብሎም ለሀገራቸው የተለያዩ አስተዋጽዖዎችን እንደሚያበረክቱ ይታወቃል። አስተዋጽዎአቸውንም በተለያዩ ዘርፎች ከፍሎ ማየት ይቻላል። ቀጣዩን ቻርት በመጠቀም ሴቶች በዘርፎቹ ምን ምን አበርክቶ እንዳደረጉ

ምሳሌዎችን ከጠቀሳችሁ በኋላ ሀሳቡን በአንድ አንቀጽ አጠቃላችሁ ግለጹ።



# ክፍል አምስት፡ ቃላት

በዚህ ክፍል የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍቺ የምትረዱበት መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ መልመጃውን በትዕዛዛቱ መሰረት ስሩ።

## መልመጃ አምስት

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ።

1. ቁንጮ 3. መልቲ 5. ዳረጎት 7. ደለዘ 9. ረጃ

2. አምበልጋ 4. ተቆራመደ 6. ቀልጣፋ 8. ሲራክ 10. ሐጫ

ለ. ለቀረበው መዝገበ ቃላዊ ፍች ወይም ገለጻ የሚስማማ ቃል ከቀረቡት አማራጮች በመምረጥ መልሱ።

1. ሀላፊነትን ያለአግባብ በመጠቀም ያልተገባ ጥቅም ማግኘት

ሀ. ሌብነት ለ. ስርቆት ሐ. ሙስና መ. ዳተኝነት

2. ያለ እድሜ ትልቅ ሰው መሰለ (ሰውነቱ ገዘፈ)

ሀ. ገረጀፈ ለ. ወፈረ ሐ. ቀውላላ መ. በረደደ

3. ጭፈራ ወይም ድለቃ በመባል ይታወቃል

ሀ. ሙዚቃ ለ. ዳንኪራ ሐ. ዘፈን መ. ዘበናይ

4. ጽሑፍን መሰረዘ፣ ማጥፋት፣ መደምሰስ

ሀ. መደለዝ ለ. ማስመር ሐ. ማጥቆር መ. ማቅለም

5. የሚናገረው ወይም የሚያደርገው ሁሉ በክፉ የሚወሰድበት

ሀ. ደመ ከልብ ለ. ደመ ነፍስ

ሐ. ደመ መራራ መ. ደመ ከልብ

6. የማይፈራ ወይም እውነቱን ፊት ለፊት የሚናገር

ሀ. ልበ ቢስ ለ. ለፍላፊ ሐ. አሽሙረኛ መ. የግንባር ስጋ

# ክፍል ስድስት፡ ሰዋስው

በሰዋስው ክፍል አረፍተነገሮችን ከሰዋስዋዊ አገልግሎታቸው አንጻር ለይታችሁ መጠቀም የሚያስችላችሁ መልመጃና ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። መልመጃውን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

## መልመጃ ስድስት

ሀ. ዓረፍተ ነገሮች ከሰዋስዋዊ ቅርፃቸው አንጻር በስንት ይከፈላሉ? ምሳሌ በመጥቀስ አስረዱ።

ለ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ተራ ወይም ውስብስብ በማለት ለዩ።

1. ቋንቋ በመልመድ እንጂ በመወለድ አይገኝም።
2. ችግር ሲመጣ ድንገት ከተፍ ይላል እንጅ ነጋሪት አይጎስምም።
3. ኢትዮጵያውያን ኩሩና ጨዋ ህዝቦች ናቸው።
4. አለማየሁ ከክፍለ ሀገር ትናንት በመኪና መጣ።
5. በዓለም ላይ ጥቂት ሰነፎች ቢኖሩም አብዛኞቹ ግን ዓላማቸውን አይስቱም።
6. ሲዲሴ ቁርሷን ስለበላች በጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች።
7. የመዲና እናት ጣፋጭ ፍራፍሬዎችን ከጓሯቸው ቆረጡ።
8. መምህራችን በዕቅድ አንብቡ ብለው መከሩን።

ሐ. በሚከተሉት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ነጠላ (ተራ) ዓረፍተ ነገሮችን በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ አውጡ።

ለምሳሌ፡ አለሚቱ በጠዋት ተነስታ ቁርሷን ከበላች በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች።

ሀ. አለሚቱ በጠዋት ተነሳች።
ለ. አለሚቱ ቁርሷን በላች።
ሐ. አለሚቱ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች።

1. ዛፎችና ቅጠሎች ዳንኪራ እየረገጡ ይወዛወዛሉ።
2. ካፊያው መሬቱን ማራስ ስለጀመረ ትኩስ የአፈር ሽታ አፍንጫውን ወጋው።
3. በምድር ላይ ርግቦች ቢኖሩም እባቦች ደግሞ በርካታ መሆናቸውን አትዘንጋ፣
4. እንደቦይ ውሃ ዝም ብሎ የሚፈስ ሰው፤ የህይወት እንቅፋት ነው፤ ሲሉ ታላላቆቻችን መክረውናል።
5. ምድር አረንጓዴ ቀሚሷን እንደገና መልበስ ስለጀመረች እንንከባከባት።
6. ወላጆቼ ወደ ገበያ ሄደው የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ገዝተው መጡ።
7. ጊዜያችንን በአግባቡ በመጠቀም የወደፊት ህልማችንን ማሳካት ይገባናል።
8. እህቴና እኔ ወላጆችንን በአቅማችን የቤት ውስጥ ስራ የምናግዛቸው ሲሆን፣ ለምሳሌ እህቴ ቤቱን ስታጸዳ እኔ ደግሞ ምግብ አበስላለሁ።

**መ. በሚከተሉት ቃላት ነጠላ ዓረፍተ ነገር መስረቱና ወደ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ቀይሯቸው።**

1. ተጣሉ/እርቅ
2. አረሰ/ዘር ዘራ
3. አጠናለሁ/አስመዘግባለሁ
4. ትችላለች/ተመርቃለች
5. ያዘች/ሄደች
6. ላክልኝ/ደውልልኝ

## የዓረፍተ ነገር ዓይነቶች

ዓረፍተ ነገሮች በውስጣቸው ከሚይዙት ግስ አንጻር ተራና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ በቀደመው የክፍል ደረጃ ተምራችኋል። በዚሁ መሰረት በውስጡ አንድ ግስ የያዘ አረፍተ ነገር ነጠላ (ራሱን ችሎ የሚቆም ሀረግ) ወይም ተራ ዓረፍተ ነገር ይባላል።

ምሳሌ፡- አረንጓዴ ሜዳ መንፈስን ያድሳል።

ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ደግሞ በውስጡ ሁለትና ከዚያ በላይ ግሶችን ይይዛል። በሌላ አነጋገር ውስብስብ አረፍተነገር ሁለትና ከዚያ በላይ ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን ወይም ሀረጎችን አጣምሮ የሚይዝ የአረፍተነገር አይነት ነው። ይህን ሃሳብ ለማጠናከር የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች እንመልከት።

ለምሳሌ፡ 'ትናንት ከጅቡቲ የመጣው ልጅ ዛሬ ተመለሰ።' በዚህ ዓረፍተ ነገር ሁለት ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች አሉ።

እነርሱም፡ ልጁ ትናንት ከጅቡቲ መጣ።

ልጁ ዛሬ ተመለሰ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ሴቶችና ልማት የሚል ርዕስ በተሰጠው ምዕራፍ፣ የሴቶች ሚና በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦልን ማዳመጥን ተለማምደናል። አዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎንም መልሰናል። በሁለተኛው የመናገር ክሂልም ከዚሁ ሴቶችንና ልማትን ከተመለከተ ርዕስ ሳንወጣ መናገርን ተለማምደናል። ቃለመጠይቅ ማድረግ የሚያስችል ተግባርም አከናውነናል። ቃለ መጠይቅ ጠያቂና ተጠያቂው በአካል ተገናኝተው ተጠያቂው በቃል መልስ የሚሰጥበት ሒደት ነው፣ ፡ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ስናስብም በዝግጅትና አቀራረብ ጊዜ የምንተገብራቸው ነጥቦች እንዳሉ ተምረናል። ሴቶች ለሀገር እድገት በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ዙሪያ ቃለ ምልልስ በማድረግ ሀሳባችንን በቃል አቅርበናል።

በማንበብ ክፍልም ስለአበበች ጎበና የስራ ጥንካሬ ልምድ ተጋርተናል። አንድን ንባብ አንብበን ተፈላጊውን ሀሳብ እንዴት ማውጣት እንዳለብንም አይተናል። ስናነብም እንደ ዓላማችን የተለያዩ ስልቶች ልንጠቀም እንችላለን። በዚህ ክፍልም የአሰሳ፣ የገረፍታ፣ ጥልቅና ሰፊ ንባብን አይተናል። የአሰሳ ንባብ ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የምንፈልገውን አንኳር ሃሳብ በፍጥነት አንብቦ ለማግኘት የሚጠቅም ንባብ እንደሆነም ተረድተናል።

ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የማጠቃለያ ሃሳብ ጽፈናል። ከዚህም በተጨማሪ ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች በመስጠት የቃላትን ቀጥተኛ ፍች ተምረናል። በሌላ በኩል ስለ ተራና ውስብስብ ዓርፍተ ነገሮች ተረድተናል። ዓረፍተ ነገሮች ውስጣቸው ከሚይዙት ግስ አንጻር ተራና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉም አይተናል። ተራ ዓረፍተ ነገር አንድ ግስ ያለው ሲሆን ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ደግሞ ሁለትና ከዚያ በላይ ግሶችን (ጥገኛ ሀረግ) እንደሚይዝ ተመልክተናል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አራት ግሶች (ሶስት ጥገኛ ዓ.ነገር) ያሉት ውስብስብ አረፍተ ነገር ከመሰረታችሁ በኋላ በውስጡ ያሉ ነጠላ አረፍተ ነገሮችን ለይታችሁ ጻፉ።
2. ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ከሚዘጋጅ ሰው ተግባራት መካከል ሶስቱን ጠቅሳችሁ አብረሩ።
3. የአሰሳ ንባብ ከገረፍታ ንባብ በምን እንደሚለይ ከጻፉችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አስረዱ።
4. ለሚከተሉ ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን ከጻፉችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ዝባድ | ሐ. ወርች | ሠ. አስቤዛ |
| ለ. ደራ | መ. አሜከላ | ረ. መኳተን |

5. ከትምህርት ቤታችሁ ጋር የተያያዘ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ምረጡና ስለጉዳዩ የሚመለከተውን አካል ለዩ። የለያችሁትን አካልም የቃለ መጠይቅ መመሪያን መሰረት አድርጋችሁ ቃለመጠይቅ አድርጉለት፤ የተገኘውን መረጃም ለክፍላችሁ በቃል አቅርቡ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ ስር የቀረበላችሁን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✔)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | |
|---|---|---|
| 1. | ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በሴቶች እና እድገት ዙሪያ የቀረቡ ሀሳቦችን በማዳመጥ መገምገም እችላለሁ። | |
| 2. | የቃለ መጠይቅ ምንነት፣ አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን ተከትዬ ቃለ መጠይቅ ማቅረብ እችላለሁ። | |
| 3. | የንባብ ስልቶችን ለይቼ በአሰሳ ማንበብ እችላለሁ። | |
| 4. | አንድን ጽሁፍ አንብቤ ተፈላጊውን ሀሳብ ለይቼ ማውጣት እችላለሁ። | |
| 5. | ከአንድ ንባብ ውስጥ የማጠቃለያ ሃሳብ መጻፍ እችላለሁ። | |
| 6. | በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ቃለ ምልልስ ማድረግ እችላለሁ። | |
| 7. | ከጽሁፍ ውስጥ አንድ አንቀጽ ማጠቃለያ እችላለሁ። | |
| 8. | ለቃላት ዓውዳዊ እና መዝገበ ቃላዊ ፍች መስጠት እችላለሁ። | |
| 9. | የአረፍተ ነነገር አይነቶችን እለያለሁ። | |
| 10. | ከውስብስብ ዓርፍተ ነገሮች ውስጥ ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን አችላለሁ። | |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ አራት

## በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት

### የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የተለያዩ ተናጋሪዎችን ሃሳብ በማዳመጥ ትንተና ትሰጣላችሁ፤
- የቀረበ ጽሑፍን አንብባችሁ ትረዳላችሁ፤
- ፈሊጣዊ አገላለጾችን በንግግራችሁ እና በጽሁፋችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤
- የቃላትን ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺዎችን ትሰጣላችሁ፤
- ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ትጠቀማላችሁ፤
- ድርሰት ትጽፋላችሁ፤
- የቃል ክፍሎችን ለይታችሁ ታመለክታላችሁ።

## ክፍል አንድ፡ ማዳመጥ

በማዳመጥ ትምህርት ክፍል መምህራችሁ የሚያስደምጧችሁ ምንባብ ቀርቧል። ምንባቡን በጥሞና አዳምጣችሁ ተከትለው የመጡ ጥያቄዎችን ስሩ።

# የመቻቻል ጀግኖች

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. መቻቻል ምንድን ነው?
2. እናንተ ከጎረቤቶቻችሁ ጋር እንዴት ነው ተቻችላችሁ የምትኖሩት?
3. በመቻቻል ምን ምን ጠቀሜታዎችን እናገኛለን? ባንቻቻልስ?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው። ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. ኔልሰን ማንዴላ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል የተባሉት ምንን ለማስወገድ ስለታገሉ ነበር?

   ሀ. የመረረ ጥላቻን　　　　ሐ. ኢ-ፍትሐዊ አስተዳደርን

   ለ. የቀለምና የዘር ልዩነትን　　　　መ. ሁሉም ምላሽ ይሆናሉ

2. "ደስታ ተዘጋጅቶ የሚገኝ ሳይሆን ከራስህ ድርጊት የሚገኝ ነው።" የሚለውን የሚተካው፦

   ሀ. በጎ የተመኘ በጎ ነገር ያገኛል

   ለ. ክፉ ምግባር ያለው መልካም ይሆናል

   ሐ. መልካም ያደረገ መልካም ይደረግለታል

   መ. ጥሩ ያደረገ ክፉ ይገጥመዋል

3. ከሁሉም ስጦታዎች ሁሉ የላቀ ስጦታ ነው የተባለው ______ ነው።

   ሀ. ሰላም የሰፈነበት ቀንና ሌሊት

   ለ. ድሎት ያለበት ሰላም የተነሳ ወቅት

   ሐ. መቻቻል የራቀበት ጥል የቀረበበት

   መ. ህይወት የሌለበት መኖር

4. በመቻቻል ይገኛል ከሚባሉ ጠቀሜታዎች መካከል የማይጠቀሰው፡-

ሀ. ሰላም ይሰፍናል ሐ. የሰው ሕይወት አይጠፋም

ለ. የሥራ ጊዜ ይባክናል መ. አብሮ መኖር ይፈጠራል

5. "እኚህ የኖቤል ሽልማት ባለቤት..." የተባሉት ማን ናቸው?

ሀ. ኔልሰን ማንዴላ ሐ. ጆን ኤፍ ኬኔዲ

ለ. ቶልስቶይ መ. ኻሊል ጂብራን

ለ. በ 'ሀ' ስር የቀረቡትን ሀሳቦች በ 'ለ' ስር ከተዘረዘሩ ባለቤቶቻቸው ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. «የሰው ልጅ ታላቅ ክብር ከመውደቁ ላይ ሳይሆን ኬኔዲ በወደቀ ቁጥር ለመነሳት ከመቻሉ ላይ ነው።" | ሀ. ጆን ኤፍ |
| 2. «የተለወጠች ዓለምን ለመመልከት የምትሻ ከሆነ ራስህ ተለወጥ።» | ለ. ቶልስቶይ |
| 3. «በሚቻለው ሁሉ ሩሁሩሆች ሁኑ፤ያም ምንጊዜም ይቻላል።" | ሐ. ዳላይ ላማ |
| 4. "..እኔና አንተ ሁላችንም የአንድ ሃይማኖት ጂብራን ነው። ልጆች ነን፤›› | መ. ኻሊል |
| 5. «... አንድም ሰው ግን ራሱን ለመለወጥ ጥረት ማንዴላ ሲያደርግ አይታይም፤» | ሠ. ኔልሰን |
| 6. "ልዩነታችንን ልናቆም ካልቻልን ቢያንስ ጋንዲ ዓለማችንን ለልዩነት ምቹ ልናደርጋት ይገባል» | ረ. ካራማቻድ |

ሐ. የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት "የመቻቻል ጀግኖች" ከሚለው የማዳመጥ ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው፤ ስለሆነም የቃላቱን ፍቺ በምንባቡ መሰረት ጻፉና ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

| | | |
|---|---|---|
| 1. መስዋዕትነት | 4. መቻቻል | 7. የሰፈነበት |
| 2. መንገላታት | 5. አበክረው | 8. ጉጉት |
| 3. ይደጋገማሉ | 6. የተዘረጉት | 9. ተግተው |

መ. ምንባቡ ሲነበብላችሁ ስለ ምን ምን ጉዳዮች አዳመጣችሁ? በጥንድ ሆናችሁ ያዳመጣችሁትን ነጥብ በነጥብ ዘርዝሩ።

# ክፍል ሁለት፡ መናገር

በመናገር ትምህርት ክፍል መናገርን በተግባር ልምምድ የምታደርጉባቸው ተግባራት ቀርበዋል። ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሩ።

## ተግባር አንድ

ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች (ከሰዎች፣ ከመጻሕፍት፣ ከመገናኛ ብዙሃን…) በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት ስለሚሰጠው ጠቀሜታ አዳምጣችሁ ለጓደኞቻችሁ በክፍል ውስጥ በቃል አቅርቡላቸው።

## ተግባር ሁለት

ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ የተለያዩ ጥያቄዎችን በየግላችሁ አዘጋጁና በክፍል ውስጥ ጓደኞቻችሁን ቃለ መጠይቅ አድርጉ።

ሀ. ስለብሔራዊ እርቅ
ሐ. በልዩነት ውስጥ አንድነት
ለ. መለያየት ስለሚያስከትላቸው ጉዳቶች
መ. ተከባብሮ ስለመኖር

# ክፍል ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ክፍል 'የብዛኀነት ህብር' የሚል ምንባብ የቀረበ ሲሆን፣ ምንባቡን በጥሞና አንብቡና መልመጃዎቹን ስሩ።

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት ስላለው ጠቀሜታ ያላችሁን ልምድ በመጠቀም በቡድን በመወያየት የደረሳችሁበትን በተወካዮቻችሁ አማካኝነት ቃላዊ ጽብረቃ አቅርቡ።
3. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ብዝኀነት    ለ. ወግ    ሐ. ቀንበር    መ. ማቀላጠፍ

## የብዝኀነት ህብር

ሀገራችን የብዙኀ ባህል፣ ታሪክና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት ናት። ከትልቁ ራስ ዳሽን ተራራ እስከ ዝቅተኛው ዳሎል እና በመካከሉ ያለው የአየር ንብረት ክልል አቅፎ የያዘው የተፈጥሮ ሃብት ስብጥር በተፈጥሮ ከታደሉ ውስን ሀገራት አንዷ ያደርጋታል። በታሪካዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ስር የሚካተቱት የአክሱም፣ የላሊበላ፣ የጎንደር ፋሲለደስ፣ የሀረር ጀጎል ግንቦች እና ሌሎችም ሃብቶቿ ዓለምን የሚያስደምሙ የክብር መገለጫዎቿ ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶቿ ባሻገር ሀገራችን ኢትዮጵያ ከ80 በላይ የየራሳቸው የሆነ ባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክና ወግ ያላቸው ሕዝቦችንም አቅፋ የያዘች ታላቅ ሀገር ናት። ህዝቦቿ መካከል ያለው የልዩነት ህብር መገለጫዎቹ በርካታ ሲሆኑ፤ የተለያዩ ቀለማትን ፈጥረው ተሳስረው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። በልዩነቱ መካከል ያለው ህብር ከመራራቅ ይልቅ መቀራረብን፣ ከመቃቃር ይልቅ መስማማትን፣ ከመነጣጠል ይልቅ መተባበርን፣ ከጥልና ክርክር ይልቅ እርቅ ማስቀደምን እንዲመርጡ በማድረግ ለረጅም አመታት

በሰላም አብረው እንዲዘልቁ አስችሏቸዋል፤ ወደፊትም የሚቀጥል ይሆናል።

በብዝኀነት ውስጥ ያለ አንድነትን አስተናግዳ የኖረችና የምትኖር ቅን ሀገር ኢትዮጵያ ለወዳጆቿ ፍቅር ለጠላቶቿ ደግሞ ሬት የሆነች ህብራዊ ሀገር ናት። ህብራዊ ሲባልም ከላይ እንደተገለጸው በአንድ በኩል እንደ ኅብረ ቀለማት የየራሳቸው ማንነት፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ ያላቸው ህዝቦች መኖሪያ መሆኗን ማመላከቱ ነው። በሌላ በክል ደግሞ እነዚሁ ህዝቦች አብረው፣ ተባብረው የኖሩና፣

**የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው።
2. በብዝኀነት ውስጥ ያለ አንድነትን አስተናግዳ የኖረች ሀገር የተባለችው ማን ናት?
3. የሰላም ምንጭ የተባለው ምድን ነው?

ኢትዮጵያ የምትባለውን የጋራ ሀገር የገነቡ፤ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ከዚህ ባሻገርም ይህ በህዝቦቿ መካከል ያለው የልዩነት ህብር ለዜጎቿ የሰላማቸው ምንጭም ሆኖ የሚያገለግል ነው። የሰላም መኖር ደግሞ እንኳን የሰው ልጆችን ይቅርና አዕዋፍና አራዊትም ተከባብረው እንዲኖሩ ያደርጋል። ለኢትዮጵያዊያን አብሮነታቸው የእኛ የሚሏቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ የሚያስጠብቁበት ኃይላቸው ነው ማለት ይቻላል።

የብዝኀነት ህብር መገለጫዎች ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ በሃይማኖቶች መካከል ያለው መቻቻል ነው። ኢትዮጵያና ህዝቦቿ ‹‹ሃይማኖት የግል ነው፤ ሀገር የጋራ ነው!›› በማለት በአብሮነት በኩራት መኖርን ልማዳቸው ያደረጉ ናቸው። በገና፣ በጥምቀት፣ በኢድ አልፈጥርና በመውሊድ ክብረበዓላት ወዘተ የሚታየው መፈቃቀድና መተሳሰብ የመንፈስ እርካታን የሚያጎናጽፍ ነው። በተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች መካከል በየወቅቱ የሚፈጠረው ውህደትም አብሮነት በጠነከረ

መልኩ እየተሰናኘ እንዲሄድ አስችሏል። ለምሳሌ ሀይማኖትንና ዘርን ከግምት ያላስገባው የጋብቻ ክንውን ዜጎቿ ተጋብተው በመዋለድ አንድነታቸውን አስጠብቀውና ልዩነታቸውን አጥብበው በሀሴት እንዲኖሩ አስችሏቸዋል። የአንዱ እምነት ተቋም በሚሰራበት ጊዜም የሌላኛው እምነት ተከታዮች ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን እያዋጡ ተሳታፊ ሲሆኑ መመልከት የተለመደ ተግባር ሆኗል። ለዚህም አይደል ዘፋኙ በስንኞቹ፦

"አንቺም በሃይማኖትሽ እኔም በሃይማኖቴ

መኖር እንችላለን አይጠበንም ቤቴ" ሲል የተቀኘው!

በልዩነት ውስጥ ላለው አንድነት ማሳያ ከሚሆኑት መገለጫዎች መካከል ሌላኛው የውጪ ጠላቶች በመጡ ጊዜ ኢትዮጵያዊያን ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን በማለት ለሀገር ሰላምና ክብር ሲሉ በአንድ ሃሳብ በአንድ ልብ መስዋዕት ለመሆን ያለማወላወል ዘብ የሚቆሙበት ጽናት ነው። ለዚህ በርካታ ምሳሌዎችን መጥቀስ ቢቻልም በዋናነት ማሳያ የሚሆነን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ ተምሳሌት የሆነው የአድዋ ጦርነት ድል ነው። በአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያዊያን ልዩነትና የቦታ ርቀት ሳይገድባቸው ከያሉበት ተጠራርተው ለቅኝ ግዛት ቋምጣ መጥታ የነበረችውን ወራሪ ጣልያንን ድል አድርገው መልሰዋታል። ቀሪዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች በቅኝ ገዢዎች እጅ ሲወድቁ ከአራቱም አቅጣጫዎች ቀፎው እንደተነካባቸው ንቦች ሆ ብለው የተነሱት ኢትዮጵያዊያን ግን በህብረታቸው አድዋ ላይ ደማቅ ታሪክ ጽፈዋል። ይህም በቀኝ ግዛት ቀንበር ስር ሲማቅቁ ለነበሩት አፍሪካዊ ወንድም እህቶቻችን ትልቅ መነቃቃትን በመፍጠር ትግላቸውን በተደራጀ መልኩ እንዲያቀለጣጥፉና ሀገሮቻቸውን ነጻ እንዲያወጡ ፈር ቀዳጅ ሆኖላቸዋል። በኋላ ላይ ወደ አፍሪካ ህብረትነት የተቀየረው የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም በተቋምነት እንዲመሰረትና መቀመጫውንም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲያደርግ ይኸው በህብረ ብሔራዊ አንድነት ቅኝ ገዢዎች ላይ የተገኘው ድል ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል።

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. ሀገራችን በተፈጥሮ ከታደሉ ውስን ሀገራት አንዷ ያደረጋት ምንድን ነው?

   ሀ. ታሪካዊ ቅርስ ለ. ባህላዊ ቅርስ

   ሐ. የተለያየ መልክዓምድር መ. ሁሉም

2. በኢትዮጵያዊያን መካከል ያለው የልዩነት ህብር ያስገኛቸው ትሩፋቶች መካከል የማይጠቀሰው፡-

   ሀ. መራራቅ ለ. እርቅ

   ሐ. መስማማት መ. መተባበር

3. ኢትዮጵያ ህብራዊ ሀገር ናት ሲባል ምን ማለት ነው?

   ሀ. ህዝቦቿ እንደ ህብረ ቀለማት የተለያየ ማንነት አላቸው።

   ለ. ህዝቦቿ ሀገራቸውን የገነቡት በጋራ ሆነው ነው።

   ሐ. ዜጎቿ ሰላምም ጦርነትም በሌለበት ሁኔታ የሚኖሩ ናቸው።

   መ. ከ'ሐ' በስተቀር ሁሉም መልስ ናቸው።

4. ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ተምሳሌት የሆነው ምንድን ነው?

   ሀ. ታሪካዊ ቅርሶቻችን ለ. በልዩነት ያለ አንድነታችን

   ሐ. የአድዋ ድል መ. ሁሉም

5. ‹‹ሃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው።›› የሚለው አባባል ምንን ያመለክታል?

ሀ. ተለያይቶ መኖርን ለ. ተከባብሮ መኖርን

ሐ. ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀልን መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

**ለ. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በንምባቡ መሰረት በቃል መልስ ስጡ።**

1. "የሰላም መኖር የሰው ልጆችን ይቅርና አዕዋፍና አራዊትም ተከባብረው እንዲኖሩ ያደርጋል።" የዚህን ሀሳብ ተጨባጭነት ማሳያዎችን በማቅረብ አስረዱ።
2. የዜጎች አንድነት ተጠብቆና ልዩነታቸው ጠብቦ የተኖረው እንዴት ነው?
3. ዜጎች በአንድ ሃሳብ በአንድ ልብ መስዋዕት ለመሆን ያለማወለላወል ዘብ የሚቆሙት መቼ ነው?
4. የአድዋ ድል ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትን ለቀኝ ግዛት ቀንበር ሊያላቅቅ የቻለው እንዴት ነው?
5. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱትን 'የብዝኀነት ህብር' መገለጫዎች በአካባቢያችሁ ከሚታዩት ተጨባጭ ሁኔታዎች ምሳሌ እያቀረባችሁ ግለጿቸው።

## መልመጃ ሁለት

**ለሚከተሉት ቃላት በቡድን እየተወያያችሁ በምንባቡ መሰረት ዓውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

ሀ. መቻቻል መ. ዘብ

ለ. ስብጥር ሠ. አስተናግዳ

ሐ. የሚያጎናጽፍ ረ. መቃቃር

# ክፍል አራት፡ መጻፍ

**በዚህ ትምህርት ክፍል ድርሰትን የተመለከተ ማስታወሻና ማስታወሻውን ተከትሎ ደግሞ መልመጃና ተግባራት ቀርበዋል።መልመጃና ተግባራቱን በትዕዛዛቱ መሰረት ስሩ።**

1. ድርሰት ማለት ምን ማለት ነው?

2. በምንጽፍበት ጊዜ የምንከተላቸው መርሆች ምንምን ይመስሏችኋል?

## ድርሰት

ድርሰት ደረሰ ከሚለው ቃል የተገኘ ሲሆን ሀሳብን በጽሑፍ መግለጽን ወይም መፃፍን ይመለከታል። ስለዚህ ድርሰት በአዕምሯችን የሚመላለስን ጉዳይ በጽሑፍ የማስተላለፍ /የማንጸባረቅ/ ስልት ነው ልንለው እንችላለን። በድርሰት ፈጠራዊ እና ፈጠራዊ ያልሆኑ ገዳዮች እየተነሱ ሊብራሩና ትንታኔ ሊቀርብባቸው ይችላል። በዚህም ድርሰትን ልቦለዳዊ (ፈጠራዊ) ወይም ኢ-ልቦለዳዊ (ፈጠራዊ ያልሆነ) በማለት በሁለት እንከፍለዋለን። ልቦለዳዊ ድርሰት የምንለው ፈጠራዊ ሥራን የሚያመለክት ሲሆን በውስጡም ኪናዊ ለዛ ያላቸውን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ያካትታል (ልብወለድ፣ ተውኔት)።

ኢ-ልቦለዳዊ ድርሰት ደግሞ እውነተኛ የሆኑ ኩነቶችን በጽሑፍ የምናስተላልፍበት መንገድ ነው ። ከተከሰተው ኩነት ምንም ሳንጨምር ማለትም ሳንከልስና ሳንበርዝ እንዳለ ማቅረብ ነው (ሳይንሳዊና ታሪካዊ እውነታዎች)።

### ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ የምንከተላቸው መርሆች

ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ ልንከተላቸው የሚገባን (ሊያግዙን የሚችሉ) መርሆች አሉ። እነርሱም ድርሰት ከመጻፋችን በፊት እንዲሁም በምንጽፍበት ጊዜ የምንከተላቸው ናቸው።

1. ድርሰት ከመጻፋችን በፊት (ቅድመ ድርሰት ተግባር)

ቀጥለን የምንዘረዝራቸው ተግባራት ድርሰት ከመጻፋችን በፊት

የምንፈጽማቸው ናቸው።

1.1 ራሳችንን ድርሰት ለመጻፍ ማነሳሳት፡- በዚህ ተግባር ሥነ-ልቦናችሁን ዝግጁ የማድረግ ተግባር የሚፈጸምበት ነው።

1.2 ድርሰት የመጻፍ ዓላማ መያዝ፡- ድርሰት የመጻፍ ዓላማ የምንለው ለማን፣ ለምን እንዴት እጽፋለሁ የሚለውን ቀድመን መመለስ የሚገባውን ጥያቄዎች የምንመልስበት ተግባር ነው።

1.3 ርዕስ መምረጥ፡- የሚመረጠው ርዕስ ሳቢ፣ ግልጽና አጭር መሆን አለበት።

1.4 ርዕስ ማጥበብ/መወሰን/፡- የምንጽፈው ድርሰት ሊዳስስየሚችላቸውን ነጥቦች የምንወስንበት ነው፡

1.5 አስተዋጽኦ /ቢጋር/ ማዘጋጀት፡- የምንጽፈው ድርሰት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ፍሰቱን ጠብቆ እንዲጻፍ የሚያግዘን ትልም ወይም መንገድ ቀያሽ ነው።

1.6 መረጃ ማፈላለግ፡- በርዕሱ መሰረት ከሰዎች፣ ከመጻሕፍት ወይም ከመገናኛ ብዙሀን ልንፈልግ እንችላለን።

1.7 መረጃዎችን መምረጥ /መለየት/፡- ከርዕሳችን ጋርየሚስማሙና ተመሳሳይነት ያላቸው ነጥቦች ብቻ የሚቀርቡበት ነው።

1.8 የተደራሲ ዓውድ፡- የምንጽፈው ድርሰት በሰዎች ተቀባይነት እንዲያገኝ የምናደርግበት ነው።

2. ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ (የጽሕፈት ተግባር)

2.1 ረቂቅ መጻፍ፡- በተነደፈው ቢጋር መሰረት ቀድሞየመጣልንን ሀሳብ በቅደምተከተል ወረቀት ላይ ማስፈርን ይመለከታል።

2.2 አርትኦት /እደታ/፡- የፊደል፣ የቃል ወይም የዓረፍተ ነገር ግድፈት እንዳይኖር ሙሉ ጥንቃቄ ተደርጎ የሚታረምበት ነው።

2.3 የመጨረሻ ረቂቅ መጻፍ፡- ፀሀፊው ማድረግ የሚገባውን ሁሉ መፈፀሙን ባመነ ጊዜ ተከታዩ ተግባር በተፃፈበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሙያ ያላቸው ሰዎች አንብበው ተገቢ ማስተካከያ፣ አስተያየትና ምዘና እንዲሰጡ ማድረግ ነው።

(ደረጀ ገብሬ፣ 2007 ዓ.ም.፣ ተግባራዊ የጽህፈት መማሪያ)

## መልመጃ ሦስት

ከላይ የቀረቡትን የድርሰት መጻፍ መርሆች በመጠቀም ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ አጭር ድርሰት ጻፉ።

ሀ. አብሮነት በልዩነት

ለ. መከባበር ለእድገት

ሐ. በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት

መ. ሁሉም ለሰላም ዘብ ይቁም

ማሳሰቢያ፡ የድርሰታችሁን ርዕስ ከመረጣችሁ በኋላ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት አስገቡ (ወይም ከላይ ስለድርሰት አፃፃፍ የቀረበውን ማስታወሻ መልሳችሁ እዩት)

1. የመረጣችሁትን ርዕስ አጥብቡት/ወስኑት፤
2. ላጠበባችሁትን ርዕስ ከሦስት አንቀጽ በላይ ማጻፍ የሚያስችል ቢጋር ንደፉለት፤
3. በነደፋችሁት ቢጋር መሰረት ግልጽና ሳቢ በሆነ መንገድ ድረሰት ጻፉ፤

## መልመጃ አራት

የሚከተለውን ቢጋር ስለ መርካቶ የሚያትት ነው፡፡ አስተዋጽዖውን መሰረት አድርጋችሁ ሶስት አንቀጽ ያለው ድርሰት ጻፉ፡፡

ርዕስ፡ መርካቶ

ሀ. የሁሉም ነገር መገኛ

1. ለማህበረሰቡ ሰፊ ግልጋሎት ይሰጣል
2. የተለያዩ ቁሳቁሶች ይገኙበታል
3. አዲስና ያገለገሉ የሚሸጥባት

ለ. የተጨናነቀች ከተማ

1. ኑዋሪዎቿ ሁሌ በመገፋፋት የሚኖሩባት
2. በሰውና በቁሳቁሶች የተሞላች
3. ሰውና መኪና የሚገፋፉባት

ሐ. ዋና የንግድ ማዕከል

1. ከተለያዩ ስፍራ እየመጡ የሚገበያዩባት
2. እቃዎችን በጅምላ የምታከፋፍል
3. አቅም ያለውንም የሌለውንም አቻችላ የምታስተናግድ

## ተግባር አራት

የሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋሮች የሰውነት ክፍሎቻችን ስያሜዎች መሰረት ያደረጉ ናቸው። መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ወይም ሰዎችን በመጠየቅ ፍቻቸው ከለያችሁ በኋላ የተወሰኑትን በመጠቀም አንድ የተሟላ አንቀጽ ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፀጉር ስንጠቃ | ዓይነ አፋር | ሆደ ሰፊ | አፍ ለአፍ |
| እግረ እርጥብ | እጅ በእጅ | የግንባር ስጋ | ዓይኑን ገለጠ |
| እጅ አጠረው | ዓይነ ልም | እግረ ደረቅ | እግር ጣለው |

# ክፍል አምስት፡ ቃላት

**በቃላት ትምህርት ክፍል ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እና የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺን የተመለከቱ መልመጃዎች ቀርበዋል። ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሯቸው።**

## መልመጃ አምስት

ሀ. በሚከተለው አጭር ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በመለየት ፍቻቸውን ጻፉ።

"‹ከልጅ ልጅ ቢለዩ ዓመት አይቆዩ› እንዲሉ ሰውየው ሰው ለየ። በዚያ ለዛ ቢስ ንግግሩ ቆሽቱ ያላረረ የለም። ‹መቼም ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት› እንደሚባለው እሱም እንደ ጻድቅ ድንግል መሬት ላይ አፈር ቀመሰ። ሙት ወቃሽ አያድርገኝና ግፉ ብዙ ነው። ታዲያ እንደ ጠዋት ጤዛ ለምትረግፍ እድሜ ሰው ነገር ሲቀምም ይውላል።ይህ ነው ያልገባኝ የሃገሬ ሊቃውንት፤ አስረዱኝ ። እንደ ድርስ እርጉዝ ሆዱን አንገፍጦ፤ በሆድ እየታሰበ እንዴት ሀገር ልታድግ ትችላለች?" አሉ። የስብሰባው መሪ ግንባራቸውን ሸብሸበው ታዳሚውን በቆረጣ እየጠመለከቱ።

ለ. በ ‹‹ሀ›› ስር የተዘረዘሩትን ፈሊጣዊ አባባሎች በ‹‹ለ›› ስር ካሉት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. ሀረግ መዘዘ | ሀ. እወደድ ባይ |
| 2. ልብ አድርቅ | ለ. ድንገተኛ አጋጣሚ |
| 3. ሰማይ ጠቀስ | ሐ. ዘሩን ቆጠረ |
| 4. ሰኔና ሰኞ | መ. አሰልቺ |
| 5. ቅቤ አንጓች | ሠ. በጣም ረጅም |
| | ረ. ጅል፣ ቂል |

## መልመጃ ስድስት

1. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጧቸው።

ሀ. መቋደሻ　　መ. ሽፍጥ　　ሰ. ወሸከሬ

ለ. መናጆ　　ሠ. ወርች　　ሸ. ድርሰት

ሐ. ህላዌ　　ረ. ቅምጫና

2. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ፈልጉላቸው።

ሀ. ህልም　　መ. የምስራች　　ሰ. ማክሰም

ለ. ተባረከ　　ሠ. አደባባይ　　ሸ. ንቁ

ሐ. ባላንጣ　　ረ. ብርቅ

# ክፍል ስድስት፡ ሰዋስው

**በሰዋስው ትምህርት ክፍል የቃል ክፍሎችን የተመለከተ ማስታወሻ ቀርቧል። ማስታወሻውን መሰረት አድርጎ የቀረበውን መልመጃ ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሩ።**

## የቃል ክፍሎች

የቃል ክፍሎች በአምስት ይከፈላሉ። በአምስት ለመክፈል በመስፈርትነት የሚያገለግሉን ሶስት ነጥቦችን ከግምት በማስገባት ነው። እነርሱም ቅርፅ፣ አገባብ እና ፍቺ/ትርጉም ናቸው።

ቅርጽ፡ ቃላት በቅርጻቸው የሚወስዱትን ቅጥያ ይመለከታል፣ ተመሳሳይ ቅጥያ የሚወስዱ በተመሳሳይ የቃል ክፍል ይመደባሉ

አገባብ፡- ቃላት በዓረፍተነገር መዋቅር ውስጥ የሚገቡበት ቦታ ይመለከታል።

ፍቺ /ትርጉም/፡- ቃሉ የሚሸከመው መሰረታዊ ትርጉም ወይም ፍቺን የሚመለከት ጽንሰ ሃሳብ ነው።

በእነዚህ ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች መመዘኛነት የተከፈሉት የቃል ክፍሎች ስም፣ ግስ፣ ቅፅል፣ ተውሳከ ግስና መስተዋድድ ናቸው።

ሀ. ስም፡ የሰዎች፣ የእንስሳት፣ የእጽዋትና የማንኛውም ግኡዝና ረቂቅ ነገሮች መጠሪያ በመሆን የሚያገለግል ቃል ነው። ስሞች በዓረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ የባለቤነት፣ የተሳቢነት እና የዘርፍነት ሙያ ይወጣሉ።

እንደ /-ኦች/ እና /-ዎች/ የመሳሰሉትን አብዢ ቅጥያዎችን ይቀበላሉ። መጠን፣ አይነትና ባህሪ የሚጠቁሙ ቃላትን ይወስዳሉ።

ምሳሌ፡ ልጅ፣ ተራራ፣ ሰው፣ በግ፣ ውሃ፣ ቤት፣ አንበሳ ወዘተ

ለ. ቅፅል፡ ከስም በፊት እየገባ የስሙን ባህሪ፣ ቅርጽ፣ መጠን፣ ቀለም፣ ወገን ወዘተ የሚገልፅ ሲሆን የስም ገላጭ በመባልም ይታወቃል። ነገር ግን ከስም በፊት የመጣ ቃል ሁሉ ቅጽል ሊሆን አይችልም። ቅጽሎች በጣም የሚለውን መግለጫ ቃል ተከትለው መግባት ይችላሉ።

ምሳሌ፡- ደግ፣ ቸር፣ የዋህ፣ አዋቂ፣ ንፉግ፣ረጅም፣ ቀይ፣ ወፍራም ... ወዘተ

ሐ. ግስ፡- በአገባቡ የዓረፍተ ነገር መቋጫ በመሆን ድርጊትን ወይም ሁነትን ያመለክታል። በቅርጹ ደግሞ የአረፍተ ነገር ባለቤት አመልካች ቅጥያዎችን ያስከትላል።

ምሳሌ፡ መጣ፣ ናቸው፣ በላች፣ አመሰገነ፣ ገደለ ... ወዘተ

መ. ተውሳከ ግስ፡- ማለት የግስ ጭማሪ ማለት ሲሆን ከግስ በፊት እየገባ ግሱን ከመጠን፣ ከሁኔታ፣ ከጊዜ፣ ከቦታ ወዘተ አንፃር የሚገልፅ ነው።

ምሳሌ፡ ግምኛ፣ ምንኛ፣ ጅልኛ፣ ክፉኛ፣ ቶሎና ገና የመሳሰሉት ናቸው።

ሠ. መስተዋድድ፡- ማለት ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግ እና ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር ጋር የሚያዋድድ ወይም የሚያስማማ ማለት ነው። መስተዋድዶች የሚከተሉትን ባህሪያት የሚያሳዩ ቃላት ናቸው።

1. የራሳቸው የሆነ ፍች የላቸውም ወይም ፍቻቸው አገልግሎታዊ (ሰዋስዋዊ) ነው።

2. እንደ ሌሎቹ ቃላት እርባታ የላቸውም።

ምሳሌ፡ ስለ፣ ወደ፣ እንደ... የመሳሰሉት ናቸው።

(ጌታሁን አማረ፣ 2007)

## መልመጃ ሰባት

ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት የቃል ክፍል ለዩ።

1. ልጁ ቶሎ ቶሎ ይናገራል።
2. እሷ ለኔ እንደታናሽ እህቴ ናት።
3. የጤና ባለሙያዎቹ መምጫ ጊዜ ገና ነው።
4. መምህሩ የተሸለመውን ልጅ አደነቀው።
5. ሀይሉ ጠንክሮ ስላጠና ፈተናውን ደፈነው።
6. የመስሪያ ቤታችን ጠንካራው ሰራተኛ ትናንት ተሸለመ።
7. ልጁ ሲሮጥ ክፉኛ ወደቀ።
8. ሀገራችን በእድገት ጎዳና ላይ እየገሰገሰች ነው።
9. እሷ አዲስ ቀሚስ ተገዛላት።
10. ነጋችንን የምናሳምረው ዛሬ ላይ በምንሰራው ስራ ነው።

ለ. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ከለያችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

ሀ. ገና
ለ. ብርሃን
ሐ. ወደ
መ. መረመረ
ሠ. ጎበዝ
ረ. ፈጣን
ሰ. ኮሮና
ሸ. አሁን

ሐ. በክፍል ሶስት ‹‹ብዝኀነት›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ አንድ አንቀጽ ከመረጣችሁ በኋላ በውስጡ ያሉትን ቃላት በየቃል ክፍላቸው መድቧቸው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በማዳመጥ ክፍል የመቻቻል ጀግኖች የተሰኘ ምንባብ አዳምጣችሁ ከታላላቅ ሰዎ ተግባራትና የህይወት መርህ ልምድ ቀስማችኋል። በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት በሚል ርዕስ የተሰናዳ ጽሑፍም አንብባችኋል።

ድርሰትን በተመለከተም በአዕምሯችን የሚመላለስን ጉዳይ በጽሑፍ የማስተላለፍ /የማንጸባረቅ/ ስልት እንደሆነና በውስጡም ፈጠራዊ እና ፈጠራዊ ያልሆኑ ገዳዮች እየተነሱ ሊብራሩና ትንታኔ ሊቀርብባቸው እንደሚችል ተገንዝባችኋል። ድርሰት ልቦለዳዊ ወይም ኢ-ልቦለዳዊ ተብሎ በሁለት እንደሚከፈልም አውቃችኋል። ልቦለዳዊ ድርሰት የምንለው ፈጠራዊ ሥራን የሚያመለክትና በውስጡም ኪናዊ ለዛ ያላቸውን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ያካተተ ሲሆን ኢ-ልቦለዳዊ ድርሰት ደግሞ እውነተኛ የሆኑ ኩነቶችን በጽሑፍ የምናስተላልፍበት መንገድ ነው።

በተጨማሪም ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ የምንከተላቸው መርሆች ተረድታችኋል። በተሰጣችሁ ርዕስ ቢ.ጋር በመንደፍ እንዴት መጻፍ እንዳለባችሁ በመገንዘብ ድርሰት ጽፋችኋል። በመቀጠልም የፈሊጣዊ አነጋሮችን ሙያ በመለየት በድርሰታችሁና በንግግራችሁ ተጠቅማችኋል። በመጨረሻም የቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ሰርታችኋል። የቃል ክፍሎች ለመክፈል የሚያገለግል መስፈረቶችን ቅርጽ፣ አገባብና ፍቺን ለይታችሁ ቃላትን በየምድባቸው መድባችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት የሚለውን ጽንሰሃሳብ ምሳሌዎችን በማንሳት ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ለክፍል አቅርቡ።
2. የድርሰት አጻጻፍ መርሆችን ተከትላችሁ ከሚከተሉት ሁለት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ድርሰት ጻፉ።

   ሀ. ክብረ በዓላት　　　ለ. ሀገር ተረካቢነት

3. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍቻውን በመስጠት ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

   ሀ. ወሽመጡ ተቆረጠ　　ሐ. በጅ አለ　　ሠ. ወይን ረገጠ

   ለ. ሱቅ በደረቱ　　መ. ቅርሻ ቅርሻ አለ　　ረ. በመላ ሄደ

4. በሚከተሉት ቃላት የቃል ክፍላቸውን በመለየት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱባቸው።

   ሀ. ምጣድ　　ሐ. እንደ　　ሠ. ተመለከተች

   ለ. ብዝኀነት　　መ. አሸባሪ　　ረ. ምንኛ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ ስር የቀረበላችሁን ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✔)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | |
|---|---|---|
| 1. | ረዘም ያለንግግሮችን በማዳመጥ፣ ነጥቦችን በማውጣት ምላሽ እሰጣለሁ። | |
| 2. | አንድን ምንባብ በለሆሳስ በማንበብ ተገንዝቤው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መመለስ እችላለሁ። | |
| 3. | የቃላትን ዓውዳዊ ፍቺ መስጠት እችላለሁ። | |
| 4. | የቃላትን ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺዎችን እሰጣለሁ። | |
| 5. | ፈሊጣዊ ንግግሮችን በፅሁፍና በንግግር ውስጥ በአግባቡ መጠቀም እችላለሁ። | |
| 6. | የድርሰት አንቀፆችን ሃሳብ አብራራለሁ። | |
| 7. | በተሰጠኝ ርዕስ ላይ የተሟላ ፅሁፍ/መጣጥፍ/ ወይም ድርሰት እጽፋለሁ። | |
| 8. | የቃላት ክፍሎችን በመለየት በአግባቡ እና በትክክል መጠቀም እችላለሁ። | |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዱ ቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ አምስት

# ቋንቋዊ ለዛ

## የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የቀረበ ታሪክ አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ፤
- የቋንቋ ለዛን ፅንሰ ሀሳብ ትገልጻላችሁ፤
- የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ዘውጎችን ትዘረዝራላችሁ፤
- ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ እንቆቅልሾችን፣ አፈታሪኮችን ትለያላችሁ፤
- የተለያዩ የቋንቋ ለዛ ጭብጦችን ትተነትናላችሁ፤
- ለዛ ያለው ቋንቋ በመጠቀም ሀሳባችሁን ትገልጻላችሁ።

## ክፍል አንድ፡ ማዳመጥ

ከዚህ ቀጥሎ መምህራችሁ 'ቃል አፍራሹ ተኩላ' በሚል ርዕስ አንድ ታሪክ ያነቡላችኋል። ሃሳባችሁን ሰብሰብ በማድረግ አዳምጧቸውና የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በየግላችሁ ስሩ። አስቀድማችሁ ግን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን መልሱ።

## ቃል አፍራሹ ተኩላ

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመነጋገር ለሚከተሉት ጥያቄዎች ቃላዊ ምላሽ ስጡ።**

1. ስነ ቃል ምንድን ነው ብትባሉ ምን ብላችሁ ትመልሳላችሁ?
2. አንድ ነገር አግባብ ነው ወይም አግባብ አይደለም የምንለው ምንን መሠረት አድርገን ይመስላችኋል?
3. ትንሽ ልጅ እያላችሁ ያዳመጣችሁትና እስካሁን ድረስ አይረሴ የሆነባችሁ ተረት አለ? ስለተረቱ የምታስታውሱትን ጥቂት ነገር ለጓደኛችሁ ንገሩ።

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

#### መልመጃ አንድ

**ያዳመጣችሁትን ተረት መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።**

1. በተረቱ ውስጥ የተሳተፉት አካላት እነማን ናቸው?
2. ተኩላው ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘው ማንን ነበር?
3. ጥንቸል ተኩላውን እንድትረዳው ያነሳሳት ምን ነበር? ምክንያቷ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ለምን?
4. ተኩላው ጥንቸሏን “ከኔ ጋር ክርክር ውስጥ አትግቢ፣” ያላት የትኛውን ‘ተፈጥሯዊ ህግ’ መነሻ አድርጎ ነበር?
5. የአዛውንቱ የመጀመሪያ ውሳኔ ምን ነበር? ለምንስ ሀሳባቸውን ቀየሩ?
6. ከአዳመጣችሁት ተረት ጋር የሚመሳሰል ሌላ ታሪክ ታውቁ ነበር? ከዚህኛው ጋር አንድነትና ልዩነታቸው ምንድን ነው?
7. የተረቱ ጭብጥ ምንድን ነው? የተኩላው ታሪክ ከሰው ልጆች ህይወት ጋር ምን ያገናኘዋል?

# ክፍል ሁለት፡ መናገር

በመናገር ትምህርት ክፍል ከስነቃል አይነቶች የተወሰኑትን የተመለከተ ማስታወሻና ማስታወሻውን ተከትሎም ተግባራት ቀርበዋል። ተግባራቱን ትዕዛዞቹን ተከትላችሁ በትኩረት ስሩ።

## ተግባር አንድ

1. ስለምሰሌያዊ አነጋገር፣ ተረት እና አፈ ታሪክ የምታውቁትን በቡድን ሁናችሁ ተወያዩ። ለእያንዳንዳቸውም ምሳሌ የሚሆኑ ማሳያዎች በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
2. ተረት፣ አፈታሪክ እና እንቆቅልሽ ለማህበረሰቡ ምን ምን ጠቀሜታዎችን ይሰጣሉ። በቋንቋ አጠቃቀም ወቅትስ የምንገለገልባቸው ለምንድን ይመስላችኋል?

### ማስታወሻ

#### ተረት

ተረት በእንስሳትና በተፈጥሮ ገፅታዎች እንዲሁም በሰዎችና ከእውኑ ዓለምሰዎች ለየት ያለ መልክ፣ ባህሪና ችሎታ በተሰጣቸው የምናብ ዓለም ፍጥረቶች አማካይነት የሰዎችን ሰናይና እኩይ ባህሪያት እንዲሁም የተለያዩ ድርጊቶች ያሳያል። ተረት የማህበረሰቡን ወግ፣ ልማድ፣ አጠቃላይ ማንነትና አመለካከት ሊያስተላልፍ ይችላል።

#### አፈታሪክ

አፈታሪክ ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ሲሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈፀመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገፅታ በመውሰድ ስነቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው። የአፈታሪክ ዓላማ በታሪክ የተፈፀመ አንድ ድርጊት እንዴት ሊፈፀም ቻለ? ለምን ተፈፀመ? የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ መልስ መስጠት ነው።

#### እንቆቅልሽ

እንቆቅልሽ በጠያቂና በተጠያቂ መካከል የሚደረግ የልጆችን አዕምሮ

በማስላት፣ አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ፣ የአስተሳሰባቸውን አድማስ ለማስፋት፣ የሰውን፣ የእንስሳትንና የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ባህሪና ቅርፅ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚረዳ የውድድር መንፈስ የሚታይበት የጥያቄና መልስ ስነቃል ነው።

(ዘሪሁን አስፋው፣ 2002፣ 28-41)

ለምሳሌ፡- ጠያቂ - ቀይ ዘንዶ ዋሻ ውስጥ ተጋድሞ

መላሽ - ምላስ

## ተግባር ሁለት

**የሚከተሉት የምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ አፈታሪኮችና እና እንቆቅልሾች የያዟቸውን ሃሳቦች ጥንድ ጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ ለሌሎች ጓደኞቻችሁ አጋሩ።**

### ሀ. ምሳሌያዊ ንግግር

ሀ. ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ አለዚያ ድንገይ ነው ብለው ይወረውሩሃል

ለ. ስም ከመቃብር በላይ ይውላል

ሐ. ለጨለማ ጊዜ መብራት፣ ለመከራ ጊዜ ብልሃት

### ለ. አፈታሪክ

‹‹እሪ በከንቱ›› የተባለው ሰፈር እንዴት ተሰየመ?

በድሮ ጊዜ የአራዳ ዘበኞች የአራዳን (የአሁኑን ፒያሳ) አካባቢ ብቻ ይጠብቁ በነበረበት ወቅት ይህ ሰፈር ጫካና በርከት ያሉ መሸታ ቤቶች ይኖሩበት ነበር። ይህም ብቻ ሳይሆኑ መሸት ሲልም የዘረፋ ተግባር የሚያካሂዱ ማጅራት መቺዎች ብዙ ጊዜ ይገቡኙት ነበር።

በወቅቱ ታዲያ አንድ ወንድ አንዱ ቤት ገብቶ እረብሻ ቢያስነሳ አንዱዋ ዱላዋን፣ ሌላዋ ዘነዘነዋን የያዙትን ይዘው ይደበድቡታል። በተጨማሪም ማጅራት መቺዎችም አላፊ አግዳሚውን እየያዙ የአካል ጉዳት አድርሰው ገንዘብ ያለውን ገንዘቡን፣ የሌለውን ልብሱን ጫማውን ይዘርፉታል። ተጠቂው ክፍል ቢጮህ አንድም ሰው ዝር አይልም።

ዝር ለማለት የሚቃጣው የአራዳ ዘበኛ ቢኖር በዚያው ይቀራል። በዚህ የተነሳ አካባቢው “እሪ በከንቱ” የሚል ስያሜ አገኘ።

## ሐ. እንቆቅልሽ

ሀ. እኔ ቢጠሩኝ አንቺ ምን አመጣሽ

ለ. ሞቶ አይቀበር ወድቆ አይሰበር፣ አባቴ የሰጠኝ ወንበር

ሐ. ባለ ግማሽ እምነት ባለአደራ፣ ግማሹን አኑሮ ግማሹን የበላ

## መ. ተረት

**አንድ የምታውቁትን ተረት ለጓደኛችሁ ንገሩና የተረቱ መልዕክት ምን እንደሆነ ጠይቁ።**

## ተግባር ሦስት

ከቤተሰቦቻሁ በመጠየቅ ወይም ከመጽሐፍ በመፈለግ አራት አራት እንቆቅልሾችን በማምጣት ጥንድ ጥንድ በመሆን በየተራ ተጠያየቁ። ስትጠያየቁ የእንቆቅልሽ የአጠያየቅ ስርዓቱን ተከትላችሁ መሆኑን አትዘንጉ።

# ክፍል ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ክፍል ‘የቋንቋ ለዛ ማስገኛዎች’ የሚል ምንባብ ቀርቦላችኋል። ምንባቡን ተከትሎም መልመጃዎች ስለተሰጡ ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሯቸው።

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. የቋንቋ ለዛ ሲባል ምን ማለት ነው?
2. የምንናገረው ወይም የምንጽፍበት ቋንቋችን ለዛ እንዲኖረው ምን ማድረግ ይጠበቅብናል ትላላችሁ?
3. ምንባቡን መሰረት ምንባቡ ምን ምን ጉዳዮችን ሊያነሳ ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

# የቋንቋ ለዛ ማስገኛዎች

ጽሁፋችን ወይም ንግግራችን በአንባቢ ወይም በአድማጭ ዘንድ ደርሶ ሳቢና ማራኪ እንዲሆን የተለያዩ ስልቶችን እንጠቀማለን። ለምሳሌ ሀሳባችንን በምንገልጽበት ወቅት የምንጠቀማቸው ቃላት፣ ሀረጋትና ዓረፍተ ነገሮች ግልጽ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ከተለመደውና ዘወትራዊው የቋንቋ አጠቃቀማችን በተጨማሪ የተለያዩ የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ዘዴዎችንም እንጠቀማለን። እነዚህ ስልቶች የቋንቋው ተጠቃሚ ሀሳቡን አጉልቶና አስውቦ እንዲያስተላልፍ የሚያስችሉ ስልቶች ናቸው። በርካታ የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶች ቢኖሩም በዚህ ክፍል ፈሊጣዊ፣ ቅኔያዊ፣ ዘይቤያዊና ምሳሌያዊ አነጋገር የሚሉትን እናያለን።

ከቋንቋ ለዛ መፍጠሪያ ስልቶች መካከል አንዱ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ይህ ዘዴ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍና ሀሳብን ተጨባጭና እና አይረሴ አድርጎ ለማቅረብ የሚረዳ ነው። ምሳሌያዊ አነጋገር በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስምምነት መሰረት የሚፈጠር፣ በቁጥብና እምቅ ቃላት የሚመሰረትና ሀሳብ በማመንጨት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ምሳሌያዊ አነጋገሮች በረጃጅም አረፍተ ነገሮችና ንግግሮች የሚብራራን ሃሳብ አሳጥረውና ጨምቀው የማቅረብ ሀይላቸው ከፍተኛ ነው። በዚህ ባህሪያቸውም የማህበረሰቡን ማንነት፣ እምነት፣ ሀይማኖት፣ ባህል፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አመለካከት ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ የቋንቋ ቅመሞች ናቸው ማለት ይቻላል።

ሰዎች በምሳሌያዊ ንግግሮች አዋዝተው ሃሳባቸውን ሲሰነዝሩ አድማጮችን ያዝናናሉ፣ የሚወዱትን ያሞግሳሉ፣ የሚጠሉትን ይነቅፋሉ፣ ተከራክረው ይረታሉ፣ ለሰዎች ተግሳጽ ይሰጣሉ፣ ባለጌ ከስህተቱ እንዲማር ያደርጋሉ፣ በአደባባይ ላይ ሲናገሩም አዋቂና አንደበተ ርቱዕ ይሰኙበታል።

ባጠቃላይ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ነገሮችን በትኩረት እንድናያቸው፣ ለሁሉ ነገር መቸኮል እንደሌለብን፣ ክፋት፣ ተንኮልና ሀሜት

እንደማያስፈልገን፣ መረዳዳትና ከታላላቆች ምርቃት ማግኘት ተገቢ እንደሆነ፣ አጉል ተስፋ ማድረግ እንደሌለብን ወዘተ የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ምሳሌ፡- ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አይወጣም።

ለብልህ አይነግሩም ለአንበሳ አይመትሩም።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለምናደርጋቸው ነገሮች ትኩረት እንድንሰጥና ጥንቃቄ እንድናደርግ ይመክሩናል።

ሁለተኛው የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ሀሳባችንን በመግለጽ ወቅት ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እያዋሃዱ መጠቀሙ ጥልቀትና ምጥቀት ያላቸውሃሳቦችን ለማስተላለፍ ከማስቻላቸም በላይ የቋንቋ ችሎታ ደረጃን ለማንጸባረቅም አይነተኛ መመዘኛ ይሆናሉ።

ቃላትን እያቀናጀን ወይም ቀደም ሲል በተናጠል ከሚሰጡት ትርጉም በተለየ መንገድ ስንጠቀምባቸው ፈሊጦች ይሆናሉ። ፈሊጦች ከሌሎች ቃላት የሚለዩባቸው ባህሪያት አሏቸው። ለአብነትም ፈሊጣዊ ንግግሮች አዕምሯዊ ምስል መፍጠር ይችላሉ፤ ብዙ ጊዜ ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው በቀጥታ አይተረጎሙም፤ ከቃላት ቀጥተኛ ትርጉም ተነስቶ ፍቻቸውን ለመስጠትም የሚከብዱ ናቸው። እንዲሁም እነዚህ የቋንቋ አጠቃቀሞች ከሌሎች ቃላት በተለየ መልኩ ሃሳብን አጠናክረውና አይረሴ አድርገው የመግለጽ ሀይል አላቸው።

ምሳሌ፡- እግረ እርጥብ = እድለኛ

ሆደ ባህር = ቻይ፣ ትዕግስተኛ

መሬት ያዘ = ተመቻችቶ ተቀመጠ

ከምሳሌዎቹ መረዳት እንደምንችለው ፈሊጣዊ ንግግሮች የተመሰረቱባቸው ቃላት በተናጠል ከሚሰጡን ፍቺ የበለጠ ውበትና ለዛን አስገኝተውልናል። የአማርኛ ፈሊጦች ለንግግራችን ለዛ፣ ለጽሁፋችን ደግሞ አጽንኦት ለመስጠት ያገለግላሉ።

ሃሳብን በትክክልና በተዝናና መንገድ ማሸጋገር መቻልና ሌሎች የሚያስተላልፉትን መልዕክት እንድንረዳ ማስቻል የፌሊጣዊ ንግግሮች ተቀዳሚ ተግባር ነው። ከዚህም በተጨማሪ ገለጻን በሀይለቃል በማጠናከር በንግግርም ሆነ በጽሁፍ መጠቀም የሚተላፍ መልዕክት ይበልጥ ፍሬ ያለውና ወደ ተግባር እንድንቀይረው የሚያስገድድ አቅም እንዲላበስ ያስችለዋል።

**አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው።**

**ቀጥሎ የቀረቡት አንቀጾችስ ምን ላይ ያተኩራሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?**

ሶስተኛው የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልት ዘይቤ ነው። ዘይቤ አንድን ሃሳብ ወይም ድርጊት፣ የአንድን ነገር ቅርጽ፣ የሰውን ባህሪ፣ ስሜትና መልክ አጉልቶና አድምቆ ለተመልካችና ሰሚ ምናባዊ ፍስሃ በመስጠት የሚያቀርብ የአነጋገር ስልት ሲሆን በግጥምም ሆነ በዝርው መልክ ሊቀርብ ይችላል። ዘይቤ ነገሮች ንረውና ከረው፣ ብሩህና ጉልህ ሆነው እንዲቀርቡ የሚያደርግ ሲሆን ከቋንቋ ለዛ መፍጠሪያ ስልቶች መካከል አንዱ ነው። ለአነጋገር ትኩስነትና ጥንካሬ ለመስጠት፣ ሃሳብን ለየት ባለ መንገድ ለመግለጽና ረቂቅ የሆኑ ነገሮችን አጉልቶ ለማሳየት ሲባል ከመደበኛው የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ሆን ብሎ ማፈንገጥ ዘይቤ ይባላል። ዘይቤ ረቂቅ ነገሮችን ብቻ ሳይሆን ወትሯዊ የሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮችንም አግዝፎ ለስሜት በማቅረብ የሚባለው ነገር በአእምሮ ውስጥ እንደ ስዕል እንዲታይ የማስቻል አቅም አለው።

ዘይቤ የአድማጭን ወይም የአንባቢን ስሜት ለመሳብ፣ ሃሳብን ግልጽ፣ ጥልቅና ስሜት ነኪ ለማድረግ፣ መልዕክትን በተቀባዩ አእምሮ ውስጥ ምስል ከሳች በሆነ መንገድ ለማስተላለፍና ትውስታን ለመፍጠር ወዘተ ያገለግላል።

ዘይቤዎችን ማፍለቅ የሚቻለውም አንዱን ካንዱ ጋር በማነጻጸር፣

አንዱን ከአንዱ ጋር በማመሳሰል፣ አንዱን በሌላው በመወከል፣ ያንዱን ባህሪ ለሌላው በመስጠት፣ ግዑዙ ነፍስ እንዲዘራ በማድረግ፣ ደብዛዛውን ብሩህ በማድረግ፣ ረቂቁን በማግዘፍ ወዘተ ሊሆን ይችላል።

ለምሳሌ፡- ‹‹ዘሪሁን እንደንብ ታታሪ ሰራተኛ ነው።›› በሚለው ዓረፍ ነገር ውስጥ የዘሪሁንን ታታሪነት ከንብ ጋር በማነጻጸር መልዕክቱ የበለጠ ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ ተችሏል።

ሌላኛው የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ዘዴ ቅኔ ነው። ቅኔ ረጅም ታሪክ ያለው በግጥም ወይም በዝርው ሊቀርብ የሚችልና በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ረቂቅ እውቀት የታከለበት የህዝብ ሀብት ነው። ቅኔ በንግግርም ሆነ በጽህፈት ሊከሰት የሚችል፣ በውስጡ ስውር መልዕክትን ይዞ፣ ያ ስውር መልዕክት እንዳይታወቅ ሌላ ግልጽ የሆነ መልዕክት በመጨመር ሀሳብ የሚተላለፍበት ያገላለጽ ለዛ ነው።

ቅኔ የሚፈጠረው በቃላትና ሀረጋት የእርስ በርስ ቅንጅት ነው። ሲመሰረትም ቀጥተኛውንና ሚስጥራዊውን መልዕክት ባንድ አዋህዶ የሚይዝ ቃል ወይም ሀረግ በገለጻው ውስጥ የሚኖር ሲሆን እሱም ህብረቃል ይባላል። ህብረ-ቃል የቅኔውን ግልጽና ስውር ፍች የያዘ ቃል ወይም ሀረግ ነው። ህብረቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚገኘው በቅኔው በስተመጨረሻ ሲሆን በውስጡም ሁለት ነገሮችን አጣምሮ ይይዛል። እነሱም ሰም እና ወርቅ ናቸው። የቅኔው ግልጽ ፍች ሰም ሲሆን ስውር(ድብቅ) ፍችው ደግሞ ወርቅ ይባላል። ሰም ቅኔውን በመጀመሪያ ስናነብ በአእምሯችን የሚመጣው ትርጉምና ቅኔ የሚቀኘው ሰው በትክክል ለማስተላለፍ የፈለገውን ሚስጥራዊ መልዕክት እንደመሸፈኛ የሚጠቀምበት ነው። ወርቅ ደግሞ ጸሀፊው ወይም ተናጋሪው ቅኔውን የተቀኘበት ምክንያት መልስ የሚያገኝበት ነው። ቅኔ ታሪክን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ፣ ለምስጋና፣ ለደስታና ለፍቅር መግለጫ፣ ለወኔ መቀስቀሻና ለመሳሰሉት ተግባራት ይጠቅመናል። በዚህም የምናስተላልፈው መልዕክት ለዛና ውበት ያለው እንዲሆን ይረዳናል።

ለምሳሌ፡- ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ የሚወዷቸውና ታላቅ ደጋፊያቸው የነበሩት ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች የሞቱባቸው ጊዜ ‹‹እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ፣ እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ። እጅግ ሙያ አዋቂ ዛሬ ተቀበረች፣ መዳኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች።›› በማለት አስለቀሰዋል። (በመጀመሪያው ሚስት፣ እናት፣ ገረድ በመሆን ታገለግለኝ ነበር ለማለት፤ በሁለተኛው ደግሞ መድሃኒቱን በመማስ (ፊልጋ በማምጣት) ለህመሜ ደራሽ ነበረች ለማለት)

(መንግስቱ ታደሰ፣ 2012 ዓ.ም፣ ሜጋ የአማርኛ ሰዋሰው አጋዥ መጽሀፍ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው። የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆነ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት መልሱ።

1. የፈሊጣዊ ንግግሮች ፍች በቃላት ተናጠላዊ ትርጉም ላይ የተመሰረተ ነው።
2. ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች ተመሳሳይ የሆኑ ለዛ ማስገኛ ስልቶች ናቸው።
3. ቅኔ በግጥም ወይም በዝርው ሊቀርብ የሚችል ቃላዊ የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ነው።
4. ዘይቤያዊ ቋንቋን መጠቀም ሀሳብን በአእምሮ ውስጥ ምስል ከሳች ያደርገዋል።
5. ምሳሌያዊ አነጋገሮች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት በጽሁፍ ነው።
6. የቅኔን ግልጽና ስውር ፍች የያዘው ቃል ወይም ሀረግ ወርቅ ተብሎ ይጠራል።

### ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ፊሊጦች ከሌሎች ቃላት በምን ይለያሉ? አብራሩ።
2. ዘይቤን ከተራው የቋንቋ አጠቃቀም ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?
3. ‹‹ምሳሌያዊ ንግግሮች በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስምምነት መሰረት የሚፈጠሩ ናቸው›› ሲል ምን ማለቱ ነው? ምሳሌ በመስጠት አስረዱ።
4. ለዛውን የጠበቀ ንግግር እንዴት ማቅረብ ይቻላል?
5. ቅኔ ምንድን ነው? የቋንቋ ለዛንስ እንዴት ያስገኛል?

### ሐ. የሚከተሉት ቃላትና ሃረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ በምንባቡ መሰረት ፍቻቸውን በጽሁፍ መልሱ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. በአደባባይ | መ. ጨምቀው | ሰ. ወትሯዊ | በ. አጽንኦት |
| ለ. ተግሳጽ | ሠ. ምስል ከሳች | ሸ. ማፈንገጥ | ተ. ለዛ |
| ሐ. አንደበተ ርቱዕ | ረ. አግዝፎ | ቀ. ፍስሃ | ቸ. ስውር |

# ክፍል አራት፡ መጻፍ

## መልመጃ ሦስት

ከዚህ በታች በቀረበው ምሳሌ መሰረት ለተሰጧችሁ ርዕሶች በሃሳብ የሚስማሙ ከአራት በላይ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመሰብሰብ ጻፉ።

ምሳሌ፡ ርዕስ፡ ተንኮል ጥሩ እንዳልሆነ ለማሳየት

- ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን፤
- ምቀኛ ጠላቱን ይተክል ወዳጁን ይነቅል፤
- ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው፤
- በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም፤
- እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሳው፤

1. ጠንክሮ መስራት
2. የመማር ጠቀሜታ
3. የጊዜ ክቡርነት
4. ምስጢር መጠበቅ
5. በህብረት መስራት
6. ከመጥፎ ነገር መጠንቀቅ

## መልመጃ አራት

1. የሚከተሉትን ግጥሞች በማንበብ ግጥሞቹ የተገነቡበትን ዘይቤዎች በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ስለዘይቤዎቹ አይነትና ጠቀሜታ አጭር ማብራሪያ በጽሑፍ አቅርቡ።

   ሀ. ለወትሮው ዳመና ፊቱ እየጠቆረ ይዘንብ ነበረ...

   የዘንድሮ ሰማይ እየሳቀ ገዳይ

   ፈ.ጋግ ሰማያዊ መልኩን አሳምሮ፣

   ስንቱን ፈጀ በላ ከራብ ተመሳጥሮ።

   (ነብይ መኮንን)

   ለ. አካሄድሽ ይምጣ አረማመድሽ፣

   ጥርስ አገላለጥሽ ከከንፈሮችሽ፣

ትህትናሽ አታላይ ከቅንነትሽ፣
አንገትሽ ብርሌ ወይኒቱ ማር ነሽ።

(መንግስቱ ለማ )

ሐ. ፈላስፋው ሲመክር አደራ ብሏል፣
በምትሰራው ስራ ቀስ ብለህ ቸኩል።

(ከበደ ሚካኤል)

መ. አዕዋፍ በጠዋቱ ተነሳ እምትሉኝ ለምን ይሆን ከቶ፣
ባማረ ድምጻችሁ መስኮቴ ተንኳኩቶ።
በሉ እኔስ ተነሳሁ ነቃሁኝ ታግየ፣
አዎ! በእርግጥ ነግቷል የሰው እግር ታየ።
ግን ልጠይቃችሁ አዕዋፍ በያይነቱ፣
ነጋ ጠባ ባዮች ሰርክ በየጠዋቱ።
ያነጋችሁት ቀን ባማረ ዜማችሁ፣
ለማን እንደጠባ ግን ታውቅታላችሁ?

(አያልነህ ሙላቱ)

ሠ. አስደንጋጭ

አልማዝ ያስነጠፈች ወርቅ ያስጎዘጎዘች
በቫነር በዲዩር ሽቱ የታጠበች
በጌጥ ተብረቅርቃ
ጌጥ ሆና ጌጥ ይዛ ጨረቃ ታፍራለች ፀሀይ ትጠፋለች
ፀዳል፣ ብርሃን፣ ንጋት ሁሉን ታስንቃለች።

(ገብረ ክርስቶስ ደስታ)

ረ. ብቸኝነት ጥምቡሳሱ፣

የፍርሀት ግሳንግሱ።

እንዳልተገራ ፈረስ ሲያደባየኝ፣

እንደ ደራሽ ውሃ ሲያፍነኝ።

እንደተጋለጠ ሐሜት ሲሰብረኝ፣

አለ! በርታ ጠና በል የሚለኝ።

(ደበበ ሰይፉ፡ "አለ ‹ጠና በል› የሚለኝ")

2. ከሚከተሉት የግጥም ርዕሶች ሁለቱን በመምረጥ ባለ አምስት ስንኝ ዘይቤያዊ ግጥም ጻፉ።

ሀ. እያየሁ አላይም

ለ. ጨረቃ

ሐ. ሰው ሆይ አንተ ማነህ

መ. በሳቄ አለቅሳለሁ

# ክፍል አምስት፡ ቃላት

በቃላት ትምህርት ክፍል ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠትን እና ምሳሌያዊ ንግግሮችን የተመለከቱ የመለማመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለሆነም የተሰጡትን ትዕዛዛት በመከተል ጥያቄዎቹን በመጻፍ መልስ ስጡባቸው።

## መልመጃ አምስት

1. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

ሀ. አጉረጠረጠ

መ. መረቅ

ለ. በለዘ

ሠ. ተቀናጀ

ሐ. ቦረቦረ

ረ. ዘመዘመ

2. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

ሀ. መልካም
ለ. እድገት
ሐ. ሆነ
መ. ወዳጅ
ሠ. ማርጀት
ረ. ወጠነ

3. በሚከተሉት ጥንድ ጥንድ ቃላት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ዓረፍተነገር በመመስረት አሳዩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ለገሰ | ለ. ፈካ | ሐ. ትርፍ | መ. አስታረቀ |
| ነፈገ | ጠወለገ | ኪሳራ | አጣላ |

## መልመጃ ስድስት

በ “ሀ” ረድፍ ለተዘረዘሩት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በ “ለ” ረድፍ ከተዘረዘሩት አቻ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሹርባ ልትሰራ ሄዳ ፀጉሯን ተላጭታ መጣች | ሀ. ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ |
| | ለ. ደህና ሲታጣ ይመለመላል ነባጣ |
| 2. ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ | ሐ. ሞኝ ለጠበቃው ምስጢር ይሸሽጋል |
| 3. አህያ ቢሰባ ምን ረባ | መ. ማሩን አምርሮ ወተቱን አጥቁሮ |
| 4. ኃሜተኛ ያፍራል ሀሰተኛ ታማስላለች ይረታል | ሠ. የራሷ እያረረባት የሰው |
| 5. ዛፍ በሌለበት እንቧጮ አድባር ነው | ረ. ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ ነው |
| | ሰ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች |

# ክፍል ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ክፍል የቅኔ መፍቻ ብልሃቶች ተዋውቀዋል፤ ይህንንም ተከትሎ የመለማመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በተጨማሪም ስምና ግሶችን መለየት የሚያስችሉ መልመጃዎች ተሰጥተዋል። ትዕዛዛቱን ተከትላችሁ መልመጃዎቹን ስሩ።

## ቅኔን ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎች

- ቃላትን በማጥበቅና በማላላት
- ታሪክን በማወቅ
- አንድን ቃል ወይም ሃረግ ሁለት ቦታ ላይ በመክፈል
- ሁለት ቃላትን ወይም ሃረጋትን በማገናኘት ወዘተ...

## መልመጃ ሰባት

ሀ. የሚከተሉትን ቅኔዎች ህብረ ቃላቸውን ከለያችሁ በኃላ የሰምና ወርቅ ፍቻቸውን በመጻፍ ቅኔዎቹን የፈታችሁባቸውን ብልሃቶች አስረዱ።

1. ውሀ ክፍቱን አድሮ እንዳናጣ ጤና፣

   ከዳድኚ እንደሆን ልየው እንደገና።

   ህብረቃል ______________________

   ሰም ______________________

   ወርቅ ______________________

   ቅኔው የተፈታበት ዘዴ ______________________

2. አስራ ሁለት ውሻ ታስሮ ከደጅሽ፣

   አስፈትቼ ገባሁ እኔ ወዳጅሽ።

   ህብረቃል ______________________

   ሰም ______________________

ወርቅ ______________________________

ቅኔው የተፈታበት ዘዴ ____________________

3. ሚስቴ በየዓይነቱ ቁርሴን ስትሰጠኝ፣

ቅንጪዋ ናት በጣም የምትጣፍጠኝ።

ህብረቃል ___________________________

ሰም ______________________________

ወርቅ ______________________________

ቅኔው የተፈታበት ዘዴ ____________________

4. አዳራሹ ሰፊ በሩ አልጠበባችሁ፣

በተራ በተራ ምነው መግባታችሁ።

ህብረቃል ___________________________

ሰም ______________________________

ወርቅ ______________________________

ቅኔው የተፈታበት ዘዴ ____________________

ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡ የቅኔ ጥያቄዎች ህብረ ቃላቸውን ከለያችሁ በኋላ የሰምና ወርቅ ፍቻቸውን ጻፉ።

ምሳሌ፡ ዝናቡ ዘነበ ይሞላል ውሃው

አወይ ይህን ጊዜ ለተሻገረው።

ህብረ ቃል፡ ይህን ጊዜ ለተሻገረው

ሰም - ውሃው ሳይሞላ መሻገር ነው

ወርቅ- መጥፎውን ዘመን እንደምንም ማለፍ መታደል ነው።

1. በጣም አደነቅሁ ተመልከቼ፣

የሰውን ስራ አይቼ።

2. ድጓ ጸመ ድጓ ተሰቅሎ ከቤቴ፣

   እኔን የሚቆጨኝ ሳልማር መቅረቴ።

3. ወተት በጨለማ ታበላሻላችሁ፣

   ቀን እንዲህ ይገፋል እኔ ላሳያችሁ።

4. እሬት በመታቀፍ አለቀ ሸማዬ፣

   በቃ አድርገህ ስጠኝ እባክህ ጌታየ።

## መልመጃ ስምንት

1. የቋንቋ ለዛ ማስገኛዎች ከሚለው ምንባብ አንድ አንቀጽ ውሰዱና በውስጡ የሚገኙ ስሞችና ግሶችን ለይታችሁ ጻፉ።
2. የለያችኋቸውን ስሞችና ግሶች በመጠቀም አምስት አምስት ዓረፍተ ነገሮችን ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስለቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶች ተምራችኋል። ማዳመጥና መናገር በሚለው ክፍል ከስነ ቃል ዘውጎች መካከል ተረት፣ አፈታሪክና የእንቆቅልሽን ምንነት ተገንዝባችኋል። ተረት በእንስሳትና በተፈጥሮ ልዩ ልዩ ገፅታዎች እንዲሁም በሰዎችና ከእውኑ ዓለም ሰዎች ለየት ያለ መልክና ባህሪ በተሰጣቸው የምናብ ዓለም ሰዎች አማካይነት የሰዎችን ሰናይና እኩይ ባህሪያት ሲያሳይ አፈታሪክ በአንድ አካባቢ ከተፈፀመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገፅታ በመውሰድ ስነቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው። እንቆቅልሽ ደግሞ በጠያቂና ተጠያቂ መካከል የሚደረግና ልጆች አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ፤ የሰውን፣ የእንስሳትንና የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ባህሪና ቅርፅ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚረዳ የውድድር መንፈስ የሚታይበት በጥያቄና መልስ የሚቀርብ ስነቃል እንደሆነ ተረድታችኋል። በመሆኑም እነዚህን ቃላዊ ስነጽሁፎች በአግባቡ መጠቀም ችላችኋል።

በመቀጠል ፈሊጣዊ፣ ዘይቤያዊ፣ ቅኔያዊና የምሳሌያዊ አነጋገሮችን ምንነትና በንግግራችን ወይም በጽሁፋችን እንዴት ለዛን እንደሚያስገኙ አይታችኋል። የምንጠቀማቸው ቃላት፣ ሀረጋትና ዓረፍተ ነገሮች ሳቢና ግልጽ እንዲሆኑ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ከተለመደውና ዘወትራዊው የቋንቋ አጠቃቀማችን ለየት ባለ መልኩ ሀሳቡን አጉልቶና አስውቦ እንዲያስተላልፍ የሚያስችሉ ናቸው። እነዚህን ለዛ ማስገኛ ዘዴዎች ተጠቅመን የተለያዩ ቅኔዎችን መፍታት ችላችኋል፤ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮችን በጽሁፋችንና በንግግራችን ውስጥ ለምንና እንዴት መጠቀም እንዳለባችሁ አውቃችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶች የሚባሉትን በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ምሳሌዎችን በመጥቀስ በቃል አስረዱ።
2. የሚከተሉትን ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ።

   ሀ. ከአፍ የወጣ ቃል ከእጅ ________________

   ለ. ክርና መርፌ፤ ስንደዶና ________________

   ሐ. ከመምህሩ ________________

   መ. ያለ ፍቅር ሰላም ________________

   ሠ. ከሮከረ ይሻላል ________________

   ረ. ያለ አቻ ጋብቻ ________________

3. በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በእንቆቅልሽ፣ በተረትና እና በአፈ-ታሪክ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በጽሁፍ አቅርቡ።
4. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ ንግግሮች ፍቻቸውን ጻፉ።

   ሀ. አንገተ ወፍራም

   ሐ. ሰምና ፈትል

   ለ. የቀለም ቀንድ

   መ. ወንር ዘረጋ

5. ለአፈ-ታሪክ ምሳሌ የሚሆኑ ታሪኮች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በመፈለግ በክፍል ውስጥ ለጓኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ።
6. ለሚከተሉት ቅኔዎች ህብረ-ቃል፣ ሰምና ወርቃቸውን ለይታችሁ ጻፉ።

   ሀ. ቁጠባ ሳናደርግ ተሻምተን በልተን፣

   እነኛ ወጣጡ እኛ እንጀራ አጣን።

   ለ. አለ ትለኛለች ሞኝ መስያት እኔ፣

   ቅቤው በፊት አልቆ እያየሁት ባይኔ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ ስር የቀረበላችሁን ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✔)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | |
|---|---|---|
| 1. | የቋንቋ ለዛን ዕንሰ ሀሳብ ተረድቼ ዘውጎችን መዘርዘር እችላለሁ። | |
| 2. | ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ እንቆቅሎሾችን፣ አፈታሪኮችንና ተረቶችን ምንነት በመረዳት ፋይዳቸውን ለይቻለሁ። | |
| 3. | ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮችን በጽሁፍና በንግግር በመጠቀም መልዕክታቸውን ማስረዳት እችላለሁ። | |
| 4. | የስነቃል ዘውጎችን የምንጠቀምበትን ማህበራዊ አውድ ማስረዳት እችላለሁ። | |
| 5. | ዘይቤዎችን ከግጥም ውስጥ መለየት እችላለሁ። | |
| 6. | የቅኔ አፈታት ዘዴዎችን ለይቼ ቅኔዎችን መፍታት እችላለሁ። | |
| 7. | የተለያዩ የቋንቋ ለዛ ጭብጦችን መተንተን እችላለሁ። | |
| 8. | ለቃላት ዓውዳዊ፣ ተመሳሳይና፣ ተቃራኒ ፍቺ መስጠት እችላለሁ። | |
| 9. | ከማንኛውም ጽሁፍ ውስጥ ስሞችንና ግሶችን መለየት እችላለሁ። | |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዱ ቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ስድስት

## የታላላቆች ሚና

### የሚጠበቁ ውጤቶች:-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- በማድመጥ የፅሁፉን ዋና ሀሳብ ትተነትናላችሁ ።
- በክርክር በመሳተፍ ምክንያታዊ ዳኝነት ትሰጣላችሁ።
- በማንበብ እንደገና ጭምቃችሁ ትፅፋላችሁ።
- የስራ ማመልከቻ ደብዳቤ ትፅፋላችሁ ።
- ቃላትን በመገጣጠም ለቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ።
- ተሻጋሪ ግሶችን በመለየት ትጠቀማላችሁ።

## ክፍል አንድ: ማዳመጥ

የማዳመጥ ክሂልን በምትለማመዱበት በዚህ ክፍል 'ሀገር ማለት የኔ ልጅ' የሚል ግጥም ቀርቦላችኋል። ግጥሙ ሲነበብ በጥሞና አዳምጡና የተዘጋጁትን ጥያቄዎች ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ መልሷቸው።

# ሀገር ማለት የኔ ልጅ

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታላላቅ ሰዎች ሚና ምን እንደሆነ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ የሚኖራቸውን አውዳዊ ፍቺ ገምቱ።

ሀ. ረቂቅ ለ. ፍንትው ሐ. ተወጠነ መ. ታድጎ

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ግጥሙ ሲነበብ በጥሞና እያዳመጣችሁ ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ የሚገኙ ባዶ ቦታዎችን አሟሏቸው።

1. እትብትሽ ______፣ ቀድመሽ የተነፈሽው አየር ብቻ እዳይመስልሽ።
2. ሀገር ______________ ነው ቃሉ።
3. ሀገር ማለት ቋንቋ ነው፤ ______________ አይናገሩት።
4. የግጥሙ ደራሲ መልዕክቱን ለማን እንደሚናገር አድርጎ ነው ያቀረበው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ቃላት ‹‹ሀገር ማለት የኔ ልጅ›› በሚለው ግጥም ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በመሆኑም የነበሩበትን አውድ ከግምት በማስገባት በቡድን ተወያዩና የቃላቱን ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. ሀገር | ሐ. ባዳ | ሠ. ሸቅጦ | ሰ. የላቡን | በ. ደጃፍ |
| ለ. ኸረት | መ. ጥሪት | ረ. ፍንትው | ሸ. ከራማ | ቀ. የሚለማ |

**መልመጃ ሁለት**

**ቀጥሎ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል፤ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ መልሱ።**

1. ከግጥሙ የተረዳችሁትን መነሻ በማድረግ ሀገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአጭሩ ለጓደኞቻችሁ አስረዱ።
2. ሀገር የሚለው ፅንሰ በግጥሙ በአግባቡ የተገለጸ ይመስላችኋል? ለምን?
3. የግጥሙን ሃሳብ ጨምቃችሁ በራሳችሁ አባባል በአንድ አንቀጽ ግለጹ።

# ክፍል ሁለት: መናገር

**በዚህ ትምህርት ክፍል የክርክር ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችል ተግባር ቀርቦላችኋል። በቂ ዝግጅት በማድረግ የክርክሩ ተሳታፊ ሁኑ።**

**ተግባር አንድ**

ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን በመምረጥ በሁለት ቡድን በመከፈል ምክንያታዊ የሆነ ክርክር አድርጉ። ክርክር በምታደርጉበት ወቅትም በምዕራፍ 2 ስለክርክር የተሰጣችሁን ማስታወሻ ከግምት አስገቡ።

- እርስ በእርስ የመከባበር ጉዳይ
- ከታላላቆቻችን የተቀበልነውን የመተሳሰብ ዕሴት በአግባቡ እየተወጣን ነው ወይስ እየተወጣን አይደለም?

# ክፍል ሶስት:ማንበብ

**በዚህ ክፍል ‘የሰፈሩ አድባር’ በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም ትኩረት በመስጠት አንብቡና የተዘጋጁትን መልመጃዎች ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሯቸው።**

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ‹‹መካሪ ሽማግሌ አያሳጣን›› የሚባለው አባባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. 'የሰፈር አድባር' የሚባለው ምንን ለማመልከት ነው?
3. ለሚከተሉት ቃላት በቡድን እየተወያያችሁ ፍቺ ስጧቸው።

   ሀ. የተኮለኮሉ  ለ. ማንቆርቆር  ሐ. ዘገባ  መ. ምክር



### የሰፈሩ አድባር

የሰፈሩ ታላቅ ሰው ተማሪዎችን ሰብስበው ምሽት ላይ ምክር ይለግሳሉ። ተማሪዎች ቀናቸውን እንዴት እንዳሳለፉ ይጠይቋቸዋል። ተማሪዎችም የተለመደ ምክራቸውን ለመስማት የጠሀይን ማዘቅዘቅ ይጠባበቃሉ። ከሾላ ዛፍ ስር ተቀምጠው ዙሪያውን ለተኮለኮሉ ህጻናትና ወጣቶች እንደማር የሚጣፍጠውን ንግግራቸው ያንቆረቁሩላቸዋል። ረጅም የእጅ ጭራቸውን እያወዛወዙ ሲናገሩና ሲያዳምጡ ወደር የላቸውም። የእምነትና ቋንቋ ልዩነት ያላቸውና የሌላቸው ብለው አይመርጡም። በዚህ ተግባራቸውም የአካባቢው ሰው ሁሉ ይወዷቸዋል።

አንድ በሰውነቱ ሙልት ያለ የአስረኛ ክፍል ተማሪ የገጠመውን መሰረት በማድረግ ፊቱን አኮሳትሮና ምላሽ እንደሚሰጡት በመተማን ከሌላ ተማሪ ጋር ስለገጠመው የውሎ ዘገባ በጥያቄ

አቀረበና ‹‹እኔን ተማሪዎች ይጠሉኛል፤ ለምንድን ነው?›› ሲል የሰፈሩን አድባር ጠየቃቸው። የሰፈሩ አድባር ነገርን በምሳሌ ማስረዳት ከልጅነታቸው ጀምሮ የተካኑበት በመሆኑ የዚያን ወጣት ተማሪ ጥያቄ ከአንድ ታሪክ ጋር አገናኝተው ሊያስረዱት በመዘጋጀት ‹‹ልጆቼ አንድ ታሪክ እነግራችኋለሁ፤ እንደተለመደው በጥሞና አዳምጡኝ›› በማለት እያዋዙ መናገር ጀመሩ።

"አንድ ቀን ዝንብና ንብ አያወሩ በወሪያቸው መሃል ዝንብ ንብን እንዲህ ስትል ጠየቀቻት 'ንብ ሆይ ለምንድን ነው የሰው ልጅ እኔን የሚጠላኝ? ለምንስ ነው የሚፀየፉኝ? ቤታቸው ስገባ ያባርሩኛል ይገድሉኛል። ከሚጠጡት ነገር ላይ ከተገኘሁ ይደፉታል፤ የሚበሉት ነገር ላይ ካረፍኩ ያረፍኩበትን ቦታ ያለውን እህል ቆርሰው ይጥሉታል። አንቺን ግን እንደኔ አይፀየፉሽም። እንዲያውም ቤታቸው ስትገቢ ይንከባከቡሻል' አለቻት። ንግግሯን በመቀጠልም 'ደግሞም መልካም ነገርን ተስፋ አድርገው ቤት መግባትሽን በደስታ ይቀበሉታል። ግን ለምንድን ነው?' ስትል ለንብ ጥያቄዋን በመብሰልሰል አቀረበች። በዚህ ጊዜ ንብ ክንፎቿን እያርገፈገፈች 'ውሎሽ የት ነው?' አለቻት። ይህን ከተናገረች በኋላም ወደ አበባዋ (ወደ ስራዋ) ሄደች።

## የማንበብ ጊዜ

**ተማሪዎች! አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው።**

**ቀጥሎ የቀረቡት አንቀጾችስ ምን ላይ ያተኩራሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?**

እንግዲህ እዚህ ጋር ቆም እንበል እናስብ፣ ሰው ጠላን፣ ገፋን፣ ናቀን እያልን እንደ ዝንቧ ጥያቄን አዝለን ከምንጓዝ ውሏችንን በደንብ እንይ። የሚገርመው ንቧ የምታወራው ከማን ጋር እንደነበር እረስታ መቼም 'ከዝንብ ማር አይጠበቅም።' ልትል ፈልጋ ከእሷ ጋር እያወራች መሆኑን ስታስታውስ ዝም አለች። ታዲያ ወዲያው 'መቼም ማንም በጤፍ ማሳ ላይ ስንዴ አይጠብቅም' በማለት ተካቸው"

አሉ ታላቁ ሰው። ቀጥለውም "ስለዚህ ምንግዜም ውድቀታችንን ለማረምም ይሁን ብርታታችንን ለማብዛት ውሏችንን እንቃኝ። ምክንያቱም ሀሳባችን ስራችንን፣ ስራችን ውጤታችንን፣ ውጤታችን እኛነታችንን ይገልፅልናልና" ብለው ትንፋሻቸውን በረጅሙ ተንፍሰው ሃሳባቸው ቋጩ።

የሰፈሩን አድባር ንግግር በተመስጦ ሲያዳምጡ የነበሩት ልጆችም ተነስተው ጉልበታቸውን ሳሙ። የሰፈሩ አድባር ቀጥለውም ‹‹እስኪ የተራዳችሁትን በአጭሩ የሚነግረኝ ማነው?›› በማለት ለልጆቹ ጥያቄ አቀረቡ። በክፍል ጓደኞቹ የተነቀፈው ተማሪ ከሰፈሩ አድባርና ከጓድኞቹ መሃል ፈጠን ብሎ ቆመና "ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ... ምን ... ተምራ መጣች ነው የሚሉት አባቴ? አዋዋሌ ጥሩ ስላልነበር የክፍል ጓደኞቼ በመልካም ሊመለከቱኝ አልቻሉም። በዝንቧ እና በንቧ መስለው ያስተማሩኝ ከመጥፎ ጓደኛ መራቅ እንዳለብኝ ተገንዝቤያለሁ" አለ። የልቡን ጥያቄ መልስ በሚያገኝበት ቦታ በመጠየቁና አንጀት የሚያርስ ምላሽ በማግኘቱ በሀሴት ተሞልቶ። ለጥያቄ መልስ ሲያገኙለት የማይደሰት ማን አለ ሲል ውስጡን እየጠየቀ። በመጨረሻም የሰፈሩ አድባር ትምህርታቸውን በምርቃት አሳረጉ።

## አንብቦ የ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሦስት

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የተሰናዱ ናቸው። ለጥያቄዎቹ ምላሽ የሚሆኑትን ከቀረቡት አማራጮች በመምረጥ መልሱ።

1. ንብ ለዝንብ የሰጠቻት ምላሽ ምን ነበር?

    ሀ. ውሎሽ የት ነው　　　　ለ. ሰው አይጠላሽም

    ሐ. ለጥያቄዋ የጥያቄ መልስ　　　　መ. 'ሀ' እና 'ለ'

2. በምንባቡ ውስጥ የቀረቡ ምሳሌያዊ ንግግሮች ብዛት ______ ናቸው።

   ሀ. 4　　ለ. 3　　ሐ. 2　　መ. 1

3. ምንባቡ የተጻፈበት የዘይቤ አይነት ______________ ነው?

   ሀ. እንቶኔ　　ለ. ግነት　　ሐ. ሰውኛ　　መ. ተለዋጭ

4. ብዙ ጊዜ ሰው ጠላን፣ ገፋን፣ ናቀን የምንለው ለምንድን ነው?

   ሀ. ውሏችንን በደንብ ስለማናይ　　ለ. ውሏችንን በደንብ ስለምናይ

   ሐ. ውሏችንን ከመልካም ጓደኛ ጋር ስለምናሳልፍ　　መ. ሁሉም

5. ከሚከተሉት ስህተት የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. መክር በመጠየቅ የሚገኝ ነገር የለም።

   ለ. እንደ ዝንቧ ጥያቄ አዝለን ከመጓዝ ጥያቄአችንን ማቅረብ።

   ሐ. ውድቀታችንን ለማስቀጠልና ለብርታታችን ውሏችንን እንቃኝ።

   መ. እንደ ዝንቧ ጥያቄ አዝለን ከምንጓዝ ውሏችንን መመርመር።

6. የምንባቡ ፍሬ ሃሳብ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

   ሀ. ሁሉም ጓደኛ ወደ ጥሩ መንገድ የሚመራ መሆኑ ይታወቃል።

   ለ. ውድቀታችንን ለማረምምና ብርታታችንን ለማብዛት ውሏችንን እንቃኝ።

   ሐ. ዝንብ ተወዳጅ የሆነችው ጠንክራ የምትሰራ ባለሙያ በመሆኗ ነው ።

   መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ፡፡

ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. 'ንብ በሃገራችን የምትመሰለው በታታሪ ሰራተኝነቷ ነው።' ይህን ሃሳብ ከምንባቡ በየትኛው አንቀጽ ላይ ቀርቧል በማስረጃ አስደግፋችሁ ተናገሩ።
2. የሰፈሩ አድባር ምክራቸውን የዝንብና የንብን ታሪክ በመጥቀስ ያቀረቡት በምን ምክንያት ነው? አብራሩ።
3. በክፍል ጓደኞቹ የተነቀፈው ተማሪ የሽማግሌውን ምክር ለማብራራት ከሌሎቹ ፈጠኖ የተነሳው ለምድን ነው? አብራሩ።
4. ‹‹ምንግዜም ውድቀታችንን ለማረምም ይሁን ብርታታችንን ለማብዛት ውሏችንን እንቃኝ።›› ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
5. የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ አሳጥራችሁ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

# ክፍል አራት: መፃፍ

በመጻፍ ትምህርት ክፍል ደብዳቤ መጻፍን የተመለከተ ማስታወሻና ደብዳቤ መጻፍን የምትለማመዱበት ተግባር ቀርበውላችኋል። ለተግባሩ የተሰጠውን ትዕዛዝ ተከትላችሁ ስሩ።

## መልመጃ አራት

የቀደመ እውቀታችሁን በመጠቀም ቀጣዮቹን ሁለት ጥያቄዎች መልሱ።

1. ከዚህ በፊት ደብዳቤ ጽፋችሁ ታውቃላችሁ? ልምዳችሁን አጋሩ።
2. ደብዳቤ ለምን ለምን ጉዳዮች እንጽፋለን?

## ደብዳቤ

ደብዳቤ ሰዎች ሃሳባቸውን በተሳካ መልኩ በጽሁፍ የሚለዋወጡበት ዘዴ ነው። ደብዳቤ የግል እና የመስሪያ ቤት በመባል በሁለት ይከፈላል።

ሀ. የግል ደብዳቤ፡- ይህ የደብዳቤ አይነት ግለሰብ ለግለሰብ፣ ግለሰብ ለቤተሰብ፣ ቤተሰብ ለቤተሰብ ወይም ቤተሰብ ለግለሰብ የሚጽፉት ሲሆን ዓላማውም ማህበራዊ ህይወታቸውንና መስተጋብራቸውን (ሰላምታ ለመለዋወጥ፣ ለምስጋና፣ ለይቅርታ፣ ለወቀሳ፣ ለማጽናኛ፣ ለፍቅር፣ ለደስታ መግለጫና ለተለያዩ ፕሮግራሞች ጥሪ ለማድረግ) ማጠናከር ሊሆን ይችላል። የግል ደብዳቤ የራሱ የሆነ ቅርጽ የሌለውና ቅርጹና ይዘቱም በጸሀፊው ፍላጎት የሚወሰን ነው። የሚጠቀመው ቋንቋው ብዙውን ጊዜ መደበኛው አይነት አይደለም።

ለ. የስራ ወይም የመስሪያ ቤት ደብዳቤ፡- የራሱ ቅርጽ ያለው ሲሆን ግለሰብ ለድርጅት፣ ድርጅት ለግለሰብ ወይም ድርጅት ለድርጅት የሚጽፉት የደብዳቤ አይነትነው። የደብዳቤው ዓላማም ስራ ለመቀጠር፣ ቅሬታ ለማቅረብ፣ ዋጋ ለመጠየቅ፣ ለማንኛውም ህጋዊ ጥያቄ ምለሽ ለመስጠትና ምላሽ ለማግኘት ወዘተ. ሊሆን ይችላል። የስራ ደብዳቤ ሲጻፍም የሚከተሉትን ነጥቦች አካቶ ይይዛል፡-

- ደብዳቤው የተጻፈበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት ያስፈልጋል።
- በድርጅት የሚጻፍ ማንኛውም ደብዳቤ የሚመዘገብበት ልዩ ቁጥር ያስፈልገዋል። ነገር ግን ግለሰብ ለድርጅት በሚጽፈው ደብዳቤ ውስጥ ቁጥር አይኖርም።
- የተቀባይ አድራሻ፡ መልዕክቱ የሚላክለት ግለሰብ ወይም ድርጅት ስምና አድራሻ በትክክል መጻፍ አለበት።
- የላኪ ስም፣ ፊርማና ኃላፊነት፡- ደብዳቤውን የጻፈው ግለሰብ ወይም ያጸደቀው ድርጅት ሙሉ ስም፣ ፊርማና ኃላፊነት በግልጽ ይሰፈራል።

- ጉዳዩ በሚል ርዕሱ በአጭሩ መቀመጥ ይኖርበታል።
- የደብዳቤው ሀተታ ወይም መልዕክት በግልጽ ቋንቋ ይጻፋል።
- የመልካም ምኞት መግለጫ፡- ደብዳቤውን ለምንጽፍለት አካል ዓላማውን በጠበቀ መልኩ፣ በአጭርና ግልጽ ቃላት የመልካም ምኞት መግለጫ(‹‹ከሰላምታ ጋር!››) የምንጽፍበት ነው።

ማህተም፡- ደብዳቤውን የጻፈው ድርጅት ከሆነ የራስጌና የግርጌ ማህተም ያስፈልገዋል። የራስጌ ማህተም በአራት ማዕዘን ቅረጽ (የተቋሙ ልዩ ምልክት) ከደብዳቤው ራሰጌ ላይ የሚቀመጥ ሲሆን የግርጌ ማህተም ክብ ቅርጽ ኖሮት በደብደቤያችን ግረጌ ላይይገኛል።

ግልባጭ፡- ግልባጭ የሚጻፈው ደብዳቤው ከተጻፈለት በተጨማሪ ሌላ አካል እንዲያውቅልን ወይም እንዲደርሳቸው ከፈለግን ነው




## መልመጃ አምስት

ከላይ በቀረበው ደብዳቤ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በቡድን ተወያዩና ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ።

ምሳሌ 2

ቀን____________

ለጊምቢ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

ጊምቢ

ጉዳዩ:- የመሸኛ ደብዳቤ እንዲጻፍልኝ ስለመጠየቅ ይሆናል

የትምህርት ቤታችሁ ተማሪ የሆንኩት እኔ መገርቱ አለማየሁ ዘንድሮ በተከናወነው ሀገር አቀፍ ፈተና ከፍተኛ ውጤት አምጥቼ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለመግባት በመጠባበቅ ላይ እገኛለሁ። ጥሪውም በቅርቡ እንደሚካሄድ ትምህርት ሚኒስቴር አስታውቋል። ስለሆነም ከወዲሁ የጉዞ ዝግጅቴን እጨርስ ዘንድ የትምህርት ቤታችሁ ተማሪ እንደነበርኩ የሚገልጽ የመሸኛ ደብዳቤ ትጽፉልኝ ዘንድ በአክብሮት አመለክታለሁ።

ከሠላምታ ጋር

መገርቱ አለማየሁ

## ተግባር ሁለት

ከላይ የቀረበላችሁን ማስታወሻና ሞዴል ደብዳቤዎች መሰረት በማድረግ የራሳችሁን አንድ የስራ ማመልከቻ ደብዳቤ ጻፉ።

# ክፍል አምስት: ቃላት

በዚህ ትምህርት ክፍል አብሮ ሂያጅ ቃላት ማጣመርንና ምስረታ ምዕላዶችን በመጠቀም ለቃላት ተጨማሪ ፍቺ መስጠትን የሚያስችል መለማመጃ ቀርቧል። ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሩ።

## አብሮሂያጅ ቃላት

አንዳንድ ቃላት ሲጠሩ ሌሎች ትዝ የሚሉን አብሮሂያጅ ቃላት አሉ።

ለምሳሌ፡- ቤት (መስሪያ ቤት፣ መኖሪያ ቤት፣ የእስር ቤት፣ የግጥም ቤት፣ ዳቦ ቤት፣ ቅኔ ቤት)



## መልመጃ ስድስት

ከላይ የተሰጣችሁን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላት አብሮሂያጅ የሆኑ ሌሎች ቃላትን በመፈለግ በስዕላዊ መግለጫ (ቻርት) አሳዩ።

ሀ. መንገድ　　　　ሐ. መስጠት

ለ. ምግብ　　　　መ. ወለድ

# ክፍል ስድስት: ሰዋሰው

በሰዋስው ትምህርት ክፍል ተሻጋሪ (ሳቢ)ና ኢ-ተሻጋሪ (ኢ-ሳቢ) ግሶችን በተመለከተ ማስታወሻና መልመጃ ቀርቦላችኋል። ግሶቹን ከለያችሁ በኋላ መልመጃዎቹን ትእዛዛቱን ተከትላችሁ ስሩቸው።

## የድርጊት ግስ

የድርጊት ግሶች የሚባሉት አንድ ሰው የሚፈፅመውን ድርጊት ወይም ተግባር የሚገልፁ ናቸው። በላ፣ ፈለጠ፣ ሄደ፣ ተኛ፣ ከተፈ ወዘተ የድርጊት ግስ ምሳሌዎች ናቸው። የድርጊት ግሶች በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም፡- ሳቢና ኢሳቢ ግሶች ይባላሉ።

ሀ. ሳቢ ግስ /ተሻጋሪ ግስ/፡- ሳቢ የሚባሉት ከተሳቢ ስም ጋር እየተዋቀሩ ግሳዊ ሀረግ የሚመሰርቱ ግሶች ናቸው። ተሳቢው ስም ከግሱ በፊት ይገኛል። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

1. በቆሎ ዘራ።

2. ደብዳቤ ጻፈች።

ሁለቱም ግሳዊ ሀረጎች ናቸው። ዘራ እና ጻፈች የሚሉት ሳቢ ግሶች ስለሆኑ በቆሎ እና ደብዳቤ የሚሉትን ስሞች በተሳቢነት ወስደው ግሳዊ ሀረግ መስርተዋል። የአረፍተነገሮቹ ባለቤቶች (ድርጊት ፈጻሚዎቹ)ም እንደቅደም ተከተላቸው 'እሱ' እና 'እሷ' ናቸው።

ለ. ኢ-ሳቢ ግስ /ኢ-ተሻጋሪ ግስ/፡- ኢ-ሳቢ ግሶች ተሳቢ ስም አያስፈልጋቸውም፣ ሀረግ የሚመሰርቱት ከተውሳከ ግስ ወይም ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር በመጣመር ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

1. በጣም ተደሰተ።

2. ከቤት ወጣች።

‘ተደሰተ’ ኢ-ሳቢ ግስ ነው። የሚገልፀው የመደሰትን ድርጊት ሲሆን ባለቤቱ በሌላ ላይ የሚፈጽመው ሳይሆን በራሱ ላይ ተከውኖ የሚያበቃ ነው(በውስጡ)፤ ድርጊቱ(ሁነቱ) ወደ ሌላ አይሻገርም። ድርጊቱ የሚፈፀመው በራሱ በተደሳቹ ሰው ላይ ነው። የመደሰቱ ስሜትም ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል። ይህም የሚገለፀው በተውሳከ ግሶች አማካይነት ነው። ተውሳከ ግሶቹ ከግሱ ቀድመው የሚገቡ ናቸው። ‘ወጣች’ የሚለው ግስም በተመሳሳይ ባለቤቷ(እሷ) ራሷ የከወነችው እና ወደ ሌላ ያልተሻገረ ድርጊትን የሚገልጽ በመሆኑ ኢ-ተሳቢ ግስ ነው።ግሱን ቀድሞ በመምጣት ከግሱ ጋር ሆኖ ግሳዊ ሀረጉን (ከቤት ወጣች) የመሰረተው ‘ከቤት’ የሚለው ሀረግም መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ስለሆነም ከኢ-ሳቢ ግስ ቀድሞ የሚመጡት መስተአምር ወይም መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ነው።

(ባየ ይማም 2010፡ 183)

## መልመጃ ሰባት

ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ግሶች ሳቢ ወይም ኢ-ሳቢ መሆናቸውን ለዩ።

1. መምህሩ ከተማሪዎቹ ሃሳብ <u>ተቀበለ</u>።
2. ይህ አመለካከቷ ከጓደኞቿ ጋር <u>አጣላት</u>።
3. ህጻኗ አምርራ <u>አለቀሰች</u>።
4. ህይወቷን ለልጆቿ አሳልፋ <u>ሰጠች</u>።
5. ቢራራ ተንሸራቶ <u>ወደቀ</u>።
6. ወላጆች በልጆቻቸው ስኬት <u>ይደሰታሉ</u>።

ለ. የሚከተሉትን ግሶች ተሻጋሪና ኢ-ተሻጋሪ መሆናቸውን በመለየት ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።

1. ተኛ
2. ፊነጨ
3. ነቃች
4. ደበደበ
5. ዘመረች
6. ነቀፈች
7. ፃፈ
8. ሞተ
9. ላከ
10. ወደደ
11. ተቀበለ
12. አረሰ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ‹‹ሀገር ማለት የኔ ልጅ›› በሚል ርዕስ የቀረበ ግጥም አዳምጣችሁ ማዳመጥን ተለማምዳችኋል። በማንበብ ክፍልም የሰፈሩ አድባር በተሰኘ ጽሑፍ በማበብ ማንበብን ማንበብን በተግባር ከውናችኋል፤ አንብቦ የመረዳት አቅማችሁን አጎልብታችኋል።

በጽህፈት ክፍልም ስለደብዳቤ ምንነትና አይነቶችተረድታችኋል። በመሆኑም ደብዳቤ ሰዎች ሃሳባቸውን በተሳካ መልኩ በጽሁፍ የሚለዋወጡበት ሲሆን የግል ወይም የሰላምታ እና የስራ ወይም የመስሪያ ቤት ደብዳቤ በመባል በሁለት እንደሚከፈል አይታችኋል። የስራ ደብዳቤ የራሱ ቅርጽ እነዳለው በምሳሌ አስደግፋችሁ ካያችሁ በኋላም ለማንኛውም ጉዳይ ማስፈጸሚያ የሚሆን የስራ ደብዳቤ መጻፍ መቻል እንዳለባችሁ አይታችኋል።

አብሮ ሂያጅ ቃላትን በማቀናጀት ሌሎች ተጨማሪ ትርጉም ያላቸው ቃላት መመስረት ችላችኋል። በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ተሻጋሪና ኢተሸጋሪ ግሶችን ምንነት ተምራችኋል። ተሸጋሪ ግሶች ከተሳቢ ስም ጋር እየተዋቀሩ ግሳዊ ሀረግ የሚመሰርቱ ግሶች ሲሆኑ ኢተሸጋሪ ግሶች ተሳቢ ስም እንደማያስፈልጋቸው ተምራችኋል። እነዚህን ግሶች ከዓረፍተ ነገሮች ውስጥም መለየት ችላችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ከምትቀርቧቸው ታላላቆቻችሁ መካከል ወደ አንዳቸው በመሄድ በመረጣችሁት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሃሳብ እንዲሰጧችሁ ጠይቋቸው። የነበራችሁን ቆይታም ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።
2. በትምህርት ቤታችሁ የተመለከታችሁትን አንድ ጉዳይ የሚመለከተው አካል እንዲፈታለችሁ በማሰብ የስራ ደብዳቤ ፃፉ።
3. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች ሳቢ ወይም ኢ-ሳቢ በማለት ፃፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ነቃች | ሐ. ገዛ | ሠ. ተደሰተ | ሰ. ጻፈች |
| ለ. ሰረቀ | መ. ሰጠ | ረ. አገኘች | ሸ. አለቀሰ |

4. ከላይ የቀረቡትን ግሶች እንደማሰሪያ አንቀጽ በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ።
5. በስራ ደብዳቤ ጊዜ አይቀሬ የሆኑ ነጥቦችን ዘርዝራችሁ አብራሩ።

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ ስር የቀረበላችሁን ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✔)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | |
|---|---|---|
| 1. | ንግግርን በማድመጥ የፅሁፉን ዋና ሀሳብ መተንተን እችላለሁ ። | |
| 2. | በክርክር በመሳተፍ ስርዓቱን የጠበቀ ክርክር ማቅረብና ምክንያታዊ ዳኝነት መስጠት እችላለሁ። | |
| 3. | ጽሁፍን በማንበብ ጭምቅ ሃሳቡን እንደገና መፃፍ እችላለሁ። | |
| 4. | የስራ ደብዳቤ ማካተት ያለበትን ነጥቦች | |
| 5. | አውቄያለሁ።ማመልከቻ ወይም የስራ ደብዳቤ እጽፋለሁ። | |
| 6. | ቃላትን በመገጣጠም ዓረፍተ ነገር መመስረት እችላለሁ። | |
| 7. | ተሸጋሪና ኢ-ተሸጋሪ ግሶችን መለየት እችላለሁ። | |
| 8. | ቅጥያዎችን በዋና ቃል ላይ በመጨመር ትርጉም ያለው ቃል መመስረት እችላለሁ። | |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዱ ቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ አንብቡ።

# ምዕራፍ ሰባት

## ረጅም ልቦለድ

### የሚጠበቁ ውጤቶች:-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ ታሪክ አዳምጣችሁ ጥያቄዎች ትመልሳላችሁ
- የረዥም ልቦለድንምንነት ታብራራላችሁ።
- የልቦለድ ክፍሎችን ትገልጻላችሁ።
- የቀረበ ጽሑፍን አንብባችሁ ጥያቄዎች ትመልሳላችሁ።
- በተገቢው መንገድ ማስታወሻ ትይዛላችሁ።
- ሙያዊ ቃላትን ለይታችሁ ትጠቀማላችሁ።
- የገቢር እና የተገብሮ ግሶ ትጠቀማላችሁ።

## ክፍል አንድ: ማዳመጥ

መምህራችሁ አንድ የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ ያነቡላችኋል። ወደ ማዳመጡ ተግባር ከመሄዳችሁ በፊት የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎቹን በጥሞና አንብቧቸው። ጽሁፉ ሲነበብላችሁም እያዳመጣችሁ ማስታወሻ ያዙ፤ በመጨረሻም ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።

## ከሞት የተረፈች ነፍስ

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ረጅም ልቦለድ ጽሑፎች አንብባችሁ ታውቃላችሁ? ባነበባችኋቸው ልቦለዶች ውስጥ የምታስታውሷቸውን ገጸባህሪያት ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. በልቦለዶቹ ውስጥ አይረሴ የሆኑባችሁን ድርጊቶች ወይም አባባሎች ተናገሩ።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ናትናኤል በምሽት ከቤቱ ወጥቶ የሄደበት ምክንያት ምን ነበር?
2. ናትናኤል ጓደኛው አብርሃምን ሊያገኘው የሚሄደው ወዴት ነው?

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

#### መልመጃ አንድ

1. "'ማነው? ምን ሆንክ?' አለች" የተባለችው ማን ናት?
2. ናትናኤል የሚለው ሲጠፋው ምን አደረገ?
3. በዝናቡ የተዘፈቀው አስፋልት የእሳት ጎርፍ የፈሰሰበት ደም የመሰለው ለምንድን ነው?
4. ናትናኤል ከተደገሰለት ሞት እዴት ሊተርፍ እንደቻለ አስረዱ።

እየተወያያችሁ ድርጊቶቹን በቅደም ተከተል ዘርዝሯቸው (መጀመሪያ…ቀጥሎ… ከዚያ…በመጨረሻም…)

# ክፍል ሁለት: መናገር

## ተግባር አንድ

በመናገር ትምህርት ክፍል ጅምር ታሪክ ማጠናቀቅን እና የምታውቁትን ልቦለድ ታሪክ መልሶ መናገርን በተመለከተ ንግግርን የምትለማመዱበት ተግባር ቀርቧል።ትዕዛዙን ተከትላችሁ ስሩ።

1. በማዳመጥ ክፍል ያዳመጣችሁት ታሪክ ናትናኤል የተባለው ገጸባህሪ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደተወሰደ ጠቁሞን ተቋጭቷል። በቡድን በቡድን ሁናችሁ የየራሳችሁን ፈጠራ በማከል ቀጥለው ምን ምን ድርጊቶች ሊከናወኑ እንደሚችሉ በመገመት ተነጋገሩባቸው። የተነጋገራችሁበትን ሀሳብም ለክፍሉ በቃል አጋሩ።
2. ስለፍቅር እስከመቃብር፣ ኦሮማይ ወይም ሌላ ያነበባችሁትን ረጅም ልቦለድ ታሪክ በተመለከተ የምታስታውሱትን በንግግር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

# ክፍል ሶስት: ማንበብ

በዚህ ትምህርት ክፍል ረዥም ልቦለድን የተመለከተ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ምንባቡም ልቦለድ ጽሑፍን በተመለከተ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ያስችላል። የቀረቡትን የመልመጃ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ መልሱ።

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ልቦለድ ጽሑፍ ከኢ-ልቦድ የሚለይባቸውን ነጥቦች በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. የልቦለድ አይነቶች ምን ምን እንደሚባሉ ታውቃላችሁ? የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ።
3. ልቦለድ የሚዋቀረው በአላባውያን ነው፤ እስኪ የምታውቋቸውን የልቦለድ አላባዊያን ጥቀሱ።

# ረዥም ልቦለድ

ልቦለድ ከተፈጸመና ሊፈጸም ከሚችል የግለሰብና የማህበረሰብ የህይወት ገጠመኝ ልዩ ልዩ ገጽታዎች የሚንጸባረቁበት፣ በቃላት አማካኝነት የሚቀርብ ምናባዊ የሆነ የፈጠራ ስራ ነው። ይህ የስነ ጽሁፍ ዘርፍ በእውኑ አለም የሚንቀሳቀሱትን ሰዎች አጠቃላይ ሰዋዊ ባህሪያትና ክንዋኔዎች እውነት አስመስሎ በገጸባህሪያት አማካኝነት የሚያቀርብ ነው። ስለዚህ የሰውን አጠቃላይ የህይወት መልኮች (ሀዘንና ደስታ፣ ምኞትና ፍላጎት፣ እድገትና ውድቀት ወዘተ.) በተመሳስሎ ለመቅረጽ የሚችል በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ የስነጽሁፍ አይነት ነው። በቁሙ እውነት አይደለም ሲባል የተተረከው የገጸባህሪያት ህይወት በእውኑ አለም በእርግጥ የተፈጸመ ወይም ታሪኩ በሚያቅፈው ዘመንና ቦት እንዳለ የታየ አይደለም ማለት ነው። ደራሲው በልቦለዱ ውስጥ ግን የዘመኑን ባህል፣ ማህበረሰባዊ እውነታና ቋንቋ በግልጽ ያሳየናል።

ልቦለድ የገሀዱን አለም እውነት ውበት ባለው ፈጠራዊ መንገድ በማቅረቡ ከሌሎች ጽሁፎች ይለያል። ሕይወት፣ እውነትና ውበት በተቀናጀ መልኩ መቅረቡ ጽሁፉን ተነባቢና ሳቢ ያደርገዋል። በልቦለድ ውስጥ የሚቀርቡ የህይወት ገጠመኞች በገሀዱ አለም ላይ የተከሰቱ ወይም ይከሰታሉ ተብለው የሚታሰቡ ናቸው። ገጸ ባህሪያቱም የገሃዱን አለም ሰዎች አጠቃላይ ሰዋዊ ማንነት ያንጸባርቃሉ። ደራሲው ሲጽፍም ከእውነታው አያፈነግጥም፤ ለማፈንገጥ ቢሞክር እንኳ በሰዎች ዘንድ ያለው ተቀባይነት አናሳ ይሆናል። ሌላው ጉዳይ ደራሲው ምናባዊ አስተውሎቱን ተጠቅሞ ሲጽፍ ቃላቱን በአግባቡ መርጦና ሳቢ የሃሳብ ፍሰትን ተከትሎ መሆን አለበት።

አንድ ልቦለድ የተዋጣለት እንዲሆን ሁሉንም የልቦለድ አላባዊያን ወይም ፍሬ ነገሮች መያዝ ይጠበቅበታል። አላባውያኑም ታሪክ፣ ትልም፣ ግጭት፣ ገጸባህርያት፣ መቼት፣ ጭብጥና አንጻር ናቸው።

ታሪክ በጊዜና ድርጊት ቅደም ተከተል የተከናወኑ ሁነቶች ትረካና የልቦለዱ መሠረት ወይም ቀዳሚ ነገር ነው። ታሪክ ምን ምን ሆነ?

ምን ምን ተረገ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ነው። የልቦለድ ታሪክ ሰው ምን አነበብክ ተብሎ ሲጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ወይም ለሌላ ሰው የሚያካፍለው ትረካ ነው። ስለሆነም የድረጊቶች አነሳስ፣ አፈጻጸምና የመጨረሻ ውጤት ተዓማኒነትና አጓጊነት እንዲኖረው ከሰው ልጅ እውነተኛ ገጠመን የተቀዳ መሆን ይጠበቅበታል።

ትልም (ሴራ) የልቦለድ መዋቅር ግንባታ ሲሆን የልቦለድ ቁልፍ ነገር ወይም አፅም በመባል ይታወቃል። ትልም በልቦለድ ውስጥ ያሉ ድርጊቶች በምክንያትና ውጤት መተሳሰራቸውን የሚያሳይ አላባ ሲሆን ምን ለምን ሆነ /ተደረገ/ ብለን በመጠየቅ የምናገኘው ምላሽ ነው። ትልም እንደ ታሪክ በጊዜና ድርጊት ቅደም ተከተል የተከናወኑ ሁነቶች ትረካ ቢሆንም ድርጊቱ ምክንያታዊ ነው። የአንድ ልቦለድ ልብ አንጠልጣይነት የሚመዘነውም በሴራው ነው። ትልቁን የልቦለድ ታሪክ የፈጠሩት በርካታ ሁነቶች አንዳቸው ከአንዳቸው እየተንሰላሰሉ ግጭት ይፈጥራሉ፣ ግጭቱም ሌላ ግጭት ሊያስከትል ይችላል። ሴራ ወይም አጽመ ታሪክ (ምሰሶ) በመባልም ይታወቃል። ሴራው ልል ወይም ጥብቅ፣ ነጠላ ወይም ድርብ ሊሆን ይችላል።

መቼት ገጸባህሪያት የሚንቀሳቀሱትና ታሪካቸውን የሚፈጽሙት ደራሲው በመረጠው የተወሰነ አካባቢና ወቅት ሲሆን የሚኖሩበትና ታሪካቸውን የሚፈጽሙበት ጊዜና ቦታ ያስፈልጋቸዋል። መቼት አገርን፣ ሀይማኖትን፣ ፖለቲካን፣ ባህላዊና መንፈሳዊ አኗኗርን፣ትምህርትን፣ ተዝናኖትን፣ የኑሮ ደረጃንና የመሳሰሉትን ሁሉ ይይዛል። ስለዚህ መቼት ታሪኩ የሚፈጸምበት ቦታና ጊዜ ከነጓዙ ሲሆን ደራሲው ይህን የመምረጥ ኃላፊነት አለበት። ጊዜ ገጸባህርያት የሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ሲሆን ጓዞቹም ወቅት፣ ዘመንና ሰዓት ሊሆኑ ይችላሉ። ቦታ ደግሞ ታሪኩ የሚፈጸምበት ወይም ገጸባህርያት የሚመላለሱበት መልክዓ ምድር ወይም አካባቢ ነው። ከመልከዓ ምድር ባሻገር ተጠቃሽ የቦታ ጓዞች መገልገያ ቁሳቁስ፣ አለባስ፣ ባህልና ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

ግጭት በገጸባህሪያት ዓላማና ፍላጎት አለመጣጣም ምክንያት የሚፈጠር አለመግባባት ወይም አለመስማማት ነው። ግጭት

ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው ድረስ የሚያልፍባቸው ደረጃዎች ተመጣጣኝ ተጻራሪ ኃይላት፣ ሰበበ ግጭት፣ ፍልሚያ፣ ጡዘት፣ ልቀትና ለውጥ ናቸው። ግጭት በባህሪው በበቂ መንስኤ ላይ የተመሰረተ፣ ተአማኒ የሆነ፣ ልብ ሰቀላ ያለውና ታሪኩን ወደፊት የሚያራምድ መሆን አለበት።

ግጭት የልቦለድ ታሪኩ የጀርባ አጥንት ሲሆን የግጭት ዓይነቶችም

## የማንበብ ጊዜ

አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው! ስንት የልቦለድ አላባውያንን እንዳሉ ተገነዘባችሁ? ቀጥሎ በቀረቡት አንቀጾችስ ምን ምን ነጥቦች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?

አራት ናቸው። እነሱም፡- ገጸባህሪ ከራሱ ጋር- ኅሊናዊ/ስነልቦናዊ/ ግጭት ፣ ገጸባህሪ ከሰው (ሌላ ገጸባህሪ) ወይም ከማህበረሰቡ ጋር ፣ገጸባህሪ ከፈጣሪው ጋርና ገጸባህሪ ከተረጥሮ ልዩ ልዩ ገጽታዎች ጋር ጋር(እንስሳትና አራዊት፣ ከአየር ጠባይ፣ እጽዋት፣ የውሀ አካላት...) ናቸው።

ገጸባህርይ ደራሲው በቀነበበላቸው የልቦለድ ዓለም ውስጥ ስጋ ለብሰው፣ ባህሪ ተጎናጽፈውና መጠሪያ ተሰጥቷቸው፣ መኖሪያ ተበጅቶላቸው የሚንቀሳቀሱ፣ የሚራቡ፣ የሚጠሙ፣ የሚፋቀሩ፣ የሚጣሉ፣ የሚሞቱ፣ የሚደሰቱ፣ የሚያዝኑና የዕውኑ ዓለም ሰዎች የሚፈጽሙትና አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ አምሳለ ሰብዕ ናቸው። ገጸባህሪያት ልቦለዱ ከተቀነበበበት ቦታና ዘመን ካሉ ሰዎች የፈለቁ ወኪሎች ሲሆኑ በዘመኑ የነበረውን አስተሳሰብ፣ ባህልና ማህበራዊ ልማድ፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሁኔታ ያንጸባርቃሉ። ስለዚህ ገጸባህሪያት ደራሲው በህይወት ገጠመኙ ካያቸውና ካወቃቸው የተለያዩ ሰዎች የቃረማቸውን ባህሪያት የሚያስቀምጥበት ምናባዊ ፍጡር ነው።

ጭብጥ የማህበረሰቡ የአኗኗር ስርዓትና ደረጃ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ነጸብራቅ ነው። ስለሆነም ጭብጥ ደራሲው በድርሰቱ ውስጥ

ለማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ወይም ይዞት የሚቀርበው ቁምነገር ነው። ጭብጥ የሰውን ልጅ መሰረታዊ ባህሪያት በማንጸባረቅ ዘላቂና ዘመን ተሸጋሪ መሆን ይጠበቅበታል። ልቦለድ በተለይም ረጅም ልቦለድ በውስጡ በርካታ ጭብጦችን ወይም ርእሰ ጉዳዮችን ይዞ ሊቀርብ ይችላል። ጭብጥን ለማግኘትም ገጸባህርያት የሚገቡበትን ኩነትና ንግግር መፈተሽ፣ የገጸባህርያትን መቼት መዳሰስ፣ የደራሲውን ገለጻ መመርመርና ገጸባህርያት የሚገቡበትን ግጭት መፈተሽ ያስፈልጋል።

የትረካ አንጻር በልቦለድ ውስጥ ታሪኩ የሚቀርብበት የትረካ አቅጣጫ ነው። ታሪኩን የሚተርከው ማን ነው፣ ከታሪኩ ጋርስ ያለው ግንኙነት ምንድን ነው፣ የተተረከውስ ከማን አኳያ ነው ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ነው። አንጻሩ ሦስተኛ መደብ (ሁሉን አወቅ ወይም ውስን ሁሉን አወቅ)፣ አንደኛ መደብ የትረካ አንጻር ወይም ተውኔታዊ የትረካ አንጻር / ተራኪው በገጸባህሪያቱ ድርጊትም ሆነ ሆነቶች ምንም አይነት አስተያየት የማይሰጥበትና ገጸባህሪያቱ ራሳቸው የሚያቀርቧቸው/ ሊሆን ይችላል።

ልቦለድ አጭርና ረጅም በመባል በሁለት ይከፈላል። አጭር ልቦለድ አንድ የትኩረት ነጥብ ያለው፣ የታመቀና ጥብቅ ትስስር ያለው አጭር የፈጠራ ስራ ነው። ረጅም ልቦለድ ደግሞ ከቅርጽና ይዘት አንጻር ሰፊና በርካታ ክልሎችንና ጉዳዮችን ያካትታል። መጠነ ርዕዩ ሰፊ በመሆኑ የሕይወትን ልዩ ልዩ መልኮች በጥልቀት ለአንባቢያን ያቀርባል። ከዚህም በተጨማሪ ሁሉንም የልቦለድ አላባውያን ሰፊ በሆነ መልኩ የማቅረብ እድል ያለው የፈጠራ ስራ ነው።

አጭርና ረጅም ልቦለድ ሁለቱም ዝርዋዊ የፈጠራዊ ድርሰቶች በመሆናቸው፣ የልቦለድን ፍሬ ነገሮችን /አላባዊያን/ እና ዘዴዎችን በመያዛቸው እንዲሁም የሕይወት መልኮችን በማንጸባረቃቸው ይመሳሰላሉ። ነገር ግን አጭር ልቦለድ ጥቂት ገጸባህርያት፣ አንድና ነጠላ ጭብጥ፣ ውስንና ጠባብ መቼት፣ ነጠላና ያልተወሰበሰበ ታሪክ፣ ትልምና ግጭት አለው፤ ጥድፊያ የጠበቀ አንድነትና በመጠኑ

አጭርነት ይታይበታል። ረጅም ልቦለድ አንድ ወይም ሁለት አብይ ጭብጥና በርካታ ንኡሳን ጭብጦችን ያቀርባል፤ በርካታ ገጸባህሪያት ስላሉት ውስብስብና የገጸባህርያቱን ሕይወት ከልደት እስከሞት ቀስብሎ እየተረከ የሚያቀርብ ረጅም ታሪክ አለው፤ አንድ ወይም ሁለት አብይ ገጸባህሪና በርካታ ንኡሳን ገጸባህርያትን በውስጡ ይይዛል፤ ሰፊ የጊዜና የቦታ ገለጻ ያቀርባል፤ በርካታና ውስብስብ የገጸባህሪያት ግጭት የታይበታል፤ትልሙም ውስብስብ ነው።

(ዘሪሁን አስፋው፣ 2002፣ 152-204)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ ካለው ምንባብ የወጡ ናቸው። በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በጽሁፍ መልሱ።

1. በልቦለድ ውስጥ የሚቀርቡ የህይወት ገጠመኞች በገሀዱ አለም ላይ የተከሰቱ ብቻ ናቸው።
2. የልቦለድ ታሪክ ተዓማኒነትና አኳኂነት እንዲኖረው ከሰው ልጅ እውነተኛ ገጠመኝ የተቀዳ መሆን ይጠበቅበታል።
3. ልቦለድ ተጨባጭ እውቀትን ለማስተላለፍ የሚጻፍ ዝርዋዊ ስራ ነው ማለት ይቻላል።
4. አጭርና ረጅም ልቦለድ ተመሳሳይ የልቦለድ አላባውያንና ዘዴዎችን ይጠቀማሉ።
5. አንድን ልቦለድ አንብበን በመልዕክትነት የምንወስደው የልቦለድ አላባ ጭብጥ ይባላል።
6. የልቦለድ ታሪክ በምክንያትና ውጤት መተሳሰሩን የሚያሳይ አላባ መቼት ይባላል።

**ለ. ቀጥሎ ከላይ ካለው ንባብ የወጡ የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል። ንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. ስለ ልቦለድ ገጸባህሪያት ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

    ሀ. ገጸባህሪያት በደራሲዎች የሚፈጠሩ የምናብ ሰዎች ናቸው።

    ለ. በልቦለድ ውስጥ የሚቀርበው ታሪክ የገጸባህሪያቱ ነው።

    ሐ. ገጸባህሪያትን በገሀዱ አለም ላይ ብንፈልጋቸው ልናገኛቸው እንችላለን።

    መ. በዘመኑ የነበረውን አስተሳሰብ፣ ባህል፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሁኔታ ያንጸባርቃሉ።

2. በልቦለድ ውስጥ መቼት __________________ነው።

    ሀ. የልቦለዱ ታሪክ የሚፈጽምበት ጊዜና ቦታ

    ለ. የልቦለዱ ታሪክ የያዘው ቁምነገር

    ሐ. ልቦለዱ የሚተረክበት አንጻር

    መ. በልቦለድ ውስጥ ያለ ግጭት/አለመግባባት/

3. ረጅም ልቦለድን የማይመለከተው አማራጭ የትኛው ነው?

    ሀ. ከሁለት በላይ አበይት እና በርካታ ንኡሳን ጭብጦችን ያቀርባል።

    ለ. የገጸባህርያቱን ሕይወት ከልደት እስከሞት ቀስ ብሎ እየተረከ ያቀርባል።

    ሐ. በውስን መቼት ላይ የሚንቀሳቀሱ ውስን ገጸባህሪያት ይኖሩታል።

    መ. በርካታና ውስብስብ የገጸባህሪያት ግጭት ይታይበታል።

4. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ልቦለድ ጽሁፍን በትክክል የሚገልጸው የትኛው ነው?

   ሀ. እውነተኛዎቹን የሰው ልጅ የህይወት ፈርጆች በጽሑፍ ቀርፆ ያሳያል።

   ለ. የገጸባህሪያቱ ህይወት በዕውኑ አለም ላይ በእርግጥ የተፈጸመ ነው።

   ሐ. ታሪኩ በሚያቅፈው ዘመንና ቦታ በእውን የታየና የተከሰተ ነው።

   መ. የሰውን ልጅ ህይወት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳስሎ ቀርፆ ያሳያል።

5. የልቦለድ አጽም ወይም ምሰሶ በመባል የሚታወቀው የልቦለድ አላባ የትኛው ነው?

   ሀ. ታሪክ   ለ. ትልም   ሐ. ግጭት   መ. ገፀባህሪ

## ሐ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. “ልቦለድ በቁሙ እውነት ያልሆነ የስነጽሁፍ አይነት ነው” ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ረጅም ልቦለድ ከአጭር ልቦለድ የሚለይባቸውን ነጥቦች ዘርዝሩ።
3. የልቦለድን ጭብጥ እንዴት ማግኘት እንደምንችል ምሳሌ በመጥቀስ አስረዱ
4. “በልቦለድ ሕይወት፣ እውነትና ውበት በተቀናጀ መልኩ ይቀርባል” የሚለውን ሀሳብ አብራሩ።
5. “ግጭት የልቦለድ የጀርባ አጥንት ነው” የተባለው ልምንድን ነው? አስረዱ።

# ክፍል አራት: መፃፍ

**በዚህ ክፍል ልብ ወለድን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል።የተሰጡትን ትእዛዛት ተከትላችሁ መልሷቸው።**

1. አንድ ልቦለድ መጽሐፍ ፈልጋችሁ በማንበብ ለእያንዳንዱ የልቦለድ አላባ ምሳሌ የሚሆኑትን ለይታችሁ በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ።
2. አንድ አጭር ልቦለድ መርጣችሁ አንብቡና ባህሪያቱን ለዩ። ይህንንም መነሻ በማድረግ የአጭር ልቦለድ ባህሪን ያሟላ ጽሑፍ ጻፉ።
3. የአንድ ልብ ወለድ ክፍል አንብቡና ለትወና እንዲሆን አድርጋችሁ አዘጋጁት።
4. ስታነቡ ከገጠማችሁ የልቦለድ አጻጻፍ ብልሃቶች በመነሳት የልቦለድ ዘዴዎች የሚባሉት ምን ምን ናቸው ብላችሁ ትገምታላችሁ? የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**የልቦለድ ዘዴዎች**

በልቦለድ ጽሁፍ ውስጥ አራት ዋና ዋና የአተራረክ ዘዴዎች ወይም ቴክኒኮች አሉ። እነሱም፡- ምልልስ፣ ምልሰት፣ ገለጻና ንግር ናቸው።ሀ. ምልልስ

በእውኑ ዓለም በልቦለድ ገጸባህሪያት መካከል የሚደረግ የሃሳብ ወይም የንግግር መለዋወጥ ምልልስ በመባል ይታወቃል። ምልልስ የገፀባህሪያቱን ማንነት፣ ችግር፣ ስሜት፣ ዓላማና ስነልቦናዊ መልክ ማሳያ ነው። ምልልስ ግልፅ፣ ማራኪ እንዲሁም ከታሪኩ ትልም ጋር ከተቀናጀ ለረጅም ልቦለድ ለዛ ከሚያጎናፅፉት ነገሮች መካከል አንዱ ይሆናል።

ለ. ገለጻ

ስለ ገጸባህሪያቱ ቁመና፣ መልክ፣ አለባበስ፣ ስሜት፣ አካባቢያቸው፣

ስለሚፈፅሟቸው ድርጊቶች ወዘተ ስዕላዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብበት ሲሆን ተደራሲያን ገፀባህሪያቱን በጥልቀት እንዲያውቁ ይረዳል። ከታሪኩና ከገጸባህሪያቱ ጋር የተያያዘ ዓላማ ያለውና የሚፈለገውን ነገር በግልፅ የሚያሳይ እንዲሁም የተመረጠና ከሌሎቹ የአተራረክ ዘዴዎች ጋር በውል ተጣምሮ ይቀርባል።

ሐ. ምልሰት

የገጸባህሪያቱን ገጠመኝ፣ አስተሳሰብ፣ ማንነትና የቀደመ ስሜት ወደኋላ በመመለስ ቀንጭቦ በማምጣት የአሁኑን የስብዕና መሰረታቸውን ለማሳየት የሚረዳ የአተራረክ ዘዴ ነው። በምልሰት በሚተረክበት ጊዜ ያለፈው ታሪክና አሁን የሚተረከው በጠበቀ ሁኔታ ተሳስረው ይቀርቡበታል።

መ. ንግር

ወደፊት ስለሚፈጸም አንዳች ድርጊት ጥቆማ በመስጠት አንባቢያን ታሪኩን በጉጉት እንዲያነቡት የሚያደርግ ነው። ንግር ጥበባዊ በሆነ መንገድ ስለትልሙ አካሄድ፣ ስለግጭቱ ሁኔታ፣ ስለገፀባህሪያቱ ማንነትና በታሪኩ ውስጥ ስለሚገጥማቸው አቢይ ነገር አስቀድሞ ለአንባቢ ፍንጭ ይሰጣል።

## ተግባር ሁለት

አንድ ልቦለድ በማንበብ የልቦለድ የአጻጻፍ ዘዴውን ለይታችሁ በማውጣት በምሳሌ አስደግፋችሁ የጽሑፍ ዘገባ አቅርቡ።

# ክፍል አምስት: ቃላት

በቃላት ትምህርት ክፍል ጠብቀውና ላልተው የተለያየ ፍቺ የሚሰጡ ቃላት ቀርበዋል። ማስታወሻውን በማንበብ ቀጥሎ የተሰጡትን መልመጃዎች ስሩ።

## የቃላት መጥበቅና መላላት

አንዳንድ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የትርጉም ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ። ከቃላቱ ውስጥ በመጥበቅና በመላላት የፍች ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ድምፆች በቃሉ መካከል ወይም መጨረሻ ላይ ሊገኙ ይችላሉ። በአማርኛ ቋንቋየቃል መጀመሪያ ድምጽ ጠብቆ አይነበብም። እንደ እነዚህ አይነት ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ በሚገቡበት ወቅት የፍቺ ልዩነት ሊያስከትሉ ይችላሉ። ሁኔታውን በዓረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ አስገብተን እንመልከት።

አባይ፡- ሀ. በአፍሪካ ረጅሙ ወንዝ አባይ ነው።

ለ. ልጁ በጠባዩ አባይ በመሆኑ ሰዎች ይጠሉታል።

የመጀመሪያው ምሳሌ የወንዝ ስምን የሚመለከት ሲሆን /ባ/ ጠብቆ የሚነበብበት ነው። በአንጻሩ ደግሞ በሁለተኛው ምሳሌ /ባ/ ላልቶ ስለሚነበብ ዋሾ የሚል ፍቺ እንዲይዝ አድርጎታል።

## መልመጃ ሦስት

1. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ በሚያስገኙት ፍቺ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

ምሳሌ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. የሚያርሰው | ሐ. ሽፍታ | ሠ. ይጣላል | ሰ. ሰባ |
| ለ. በራ | መ. ከዳኝ | ረ. አማች | ሸ. ቀላ |

2. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመሩባቸውን ቃላት የገቡበት ዓውድ በመጥበቅና ወይም በመላላት መሆኑን ጻፉ።

1. ጎበዟ ተማሪ የሰው ችግር በቀላሉ ይገባታል።
2. ሰነፉ ተማሪ በሰው ውጤት ቀና።
3. ከፋ ከቡና መገኛ ቦታዎች መካከል አንዱ ነው።
4. ተማሪዋን በስስት አያት።
5. የበዛብህ አማት ፊታውራሪ መሸሻ ቁጡ ናቸው።

3. ልቦለድ በሚለው ምንባብ ውስጥ በመጥበቅና በመላላት የፍቺ ልዩነት የሚያስከትሉ አምስት ቃላትን በመፈለግ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

# ክፍል ስድስት: ሰዋሰው

በሰዋስው ክፍል ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮችን የማስተካከል መልመጃ ቀርቧል። ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሩ።

## ሰዋስዋዊ ስህተት ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

በዓረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ ሰውስዋዊ ስህተቶች አሉ። ከነዚህም መካከል የቁጥር፣ የጾታ፣ የመደብ አለመስማማት፣ የተሳቢ አመልካች ካለቦታው መግባት ወይም መቅረት፣ የእምር አመልች መቅረት ወይም ያለቦታው መግባት፣ እንዲሁም የሀረግ አለመጣጣም ወዘተ... ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ስህተቶችን አስተካክለን እና ተጠንቅቀን ካልጻፍናቸው መልዕክቱ ሊፋለስ ወይም ሊደበዝዝ ይችላለል።

ለምሳሌ:- ትናንትና የመጣው ልጅ ዛሬ ተመለሰች።

በዚህ ዓረፍት ነገር ውስጥ የታየው ሰዋስዋዊ ችግር የጾታ አለመጣጣም ነው። በመሆኑም በሁለት መንገድ ሊስተካከል ይችላል። በወንድ ወይም በሴት አንቀጽ ማስተካል እንችላለን።

ሀ. ትናንትና የመጣው ልጅ ዛሬ ተመለሰ። ወይም

ለ. ትናንት የመጣችው ልጅ ዛሬ ተመለሰች።

## መልመጃ አራት

ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሰዋስው ችግር ያለባቸው ናቸው። ችግሮችን በመለየት (የመደብ የጾታ፣ የቁጥር፣ እምር አመልካች እንዲሁም የተሳቢ አመልካች ያለቦታው መግባት ወይም መቅረት) ዓረፍተ ነገሮቹን እንደገና አስተካላችሁ ጻፉ።

1. ገበሬው በሬው ሸጠ፡
2. ሰነፍ ተማሪ ዘወትር ይጨነቃሉ።
3. ኢትዮጵያ የተለያዩ የአትክልት አይነቶችን ያመርታል።
4. አካባቢን ማጽዳት ተላላፊ በሽታ ለመከላከል ይጠቅማል።
5. ፈጭ ልጅ በፍጥነት እየሮጠ መጣ።

ለ. በሚከተለው አጭር ጽሁፍ ውስጥ የሚታየውን ሰዋስዋዊ ስህተት እንደገና አስተካላችሁ ጻፉ።

መረን ለቀቅ ቋንቋ አጠቃቀመም ከማህበራዊ ገጽታ አንጻር ሲታይ አሉታዊ መልክ ኀልቶ ይታያል። ይህ ደግሞ ተግባቦትን ባያደናቅፍም ማሻከሩ የማይቀር ነው። ስለዚህ የቋንቋ አጠቃቀማ ላይ ሊስተካከል የሚገባ ነው። ወጣት አክብሮ ሰውን መጥራት ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃኑን ታላላቅ ለመልካም ቅርርባችን አንተ/ አንቺ እያለ መጥራት በቅድሚያ ይመርጣል።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ረጅም ልቦለድ ተምራችኋል። ስለሆነም የልቦለድን ምንነት፣ አላባውያን፣ አይነቶችና ዘዴዎች ተረድታችኋል። ልቦለድ የገሀዱን አለም አጠቃላይ እንቅስቃሴ በገፀባህሪያት አማካኝነት የሚያቀርብ የፈጠራ ስራ እንደሆነም ተምራችኋል። በመሆኑም ልቦለድ ታሪክ፣ ገፀባህሪያት፣ ግጭት፣ መቼት፣ ጭብጥ፣ ትልምና የትረካ አንፃር የተባሉ ፍሬ ነገሮችን ሲይዝ ማቅረቢያ ዘዴዎቹ ደግሞ ገለፃ፣ ምልሰት፣ ንግርና ምልልስ ናቸው። በዚህ መሰረትም የልቦለድ አላባዊያንና ዘዴዎችን በማስረጃ በማስደገፍ መግለጽ ችላችኋል፤ ከልቦለድ ውስጥም የልቦለድ አላባውያን ለይታችሁ አሳይታችኋል።

ልቦለድ የገሀዱን አለም እውነት ውበት ባለው ፈጠራዊ መንገድ በማቅረቡ ከሌሎች ጽሁፎች ይለያል። ሕይወት፣ እውነትና ውበት በተቀናጀ መልኩ መቅረቡ ጽሁፉን ተነባቢና ሳቢ እንደሚያደርገውም በማስረጃ በማስደገፍ አይታችኋል። ልቦለድ ረጅምና አጭር በመባል በሁለት እነደሚከፈልም ተምራችኋል። ስለሆነም በሁለቱ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት መጥቀስ ችላችኋል። አጭር ልቦለድ በሁሉም አላባዎቹ ቁጥብነት የሚታይበት ሲሆን ረጅም ልቦለድ ግን የገፀባህሪያቱን ህይወት ከልደት እስከ ሞት የሚተርክበት ረጅም ጊዜ ስላለው አላባውያኑም በሰፊው ይቀርባሉ።

በአማርኛ ቋንቋ አንዳንድ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ በቃልም ሆነ በአረፍተነገር ደረጃ የትርጉም ለውጥ ሊያመጡ እንደሚችሉም ተምራችኋል። በዓረፍተነገር ውስጥ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶች (የቁጥር፤ የጾታ፣ የመደብ አለመስማማት፣ የተሳቢ አመልካች ካለቦታ መግባት ወይም መቅረት፣ የእምር አመልች መቅረት ወይም ያለቦታ መግባት፣ እንዲሁም የሀረግ አለመጣጣም…) እንደሚያጋጥሙም ተረድታችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ከልቦለድ አላባውያን መካከል ትልምና ግጭት ለአንድ ልቦለድ መዋቅር ያለቸውን ጠቀሜታ በጽሁፍ ግለጹ።
2. ጠብቀውና ላልተው በመነበብ የትርጉም ለውጥ የሚያመጡ አምስት ቃላትን (መማሪያ መጽሀፋችሁ ውስጥ ከተጠቀሱ ቃላት ውጪ) በመፃፍ በዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።
3. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያለውን ሰዋስዋዊ ስህተት በመለየት ዓረፍተ ነገሮቹን እንደገና አስተካክላችሁ ፃፉ።

   ሀ. ጓደኛዬ የገዛችው ቀሚስ መልኩ አልወደድኩትም።

   ለ. ጎበዙ ልጅ ፈተና አለፈች።

   ሐ. ህፃን ልጅ ቃላትን አቀላጥፎ መናገር ችሏል።

   መ. ልጆች በእረፍት ሰዓታቸው መጫወት ይገባል።

   ሠ. የገዛሁት ላም ወተት እየታለበ ነው።

   ረ. በርትተን ካጠናን ፈተናው እናልፋለን።

4. ‹‹የልቦለድ ጭብጥ የሰውን ልጅ መሰረታዊ ባህሪያት በማንጸባረቅ ዘላቂና ዘመን ተሻጋሪ መሆን ይጠበቅበታል›› የሚለውን ሀሳብ ምሳሌ በመጥቀስ አብራሩ።
5. ከልቦለድ ዘዴዎች መካከል ገለፃ ምን እንደሆነ አብራርታችሁ ፃፉና ከአንድ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ገለፃን የሚያሳይ ምሳሌ ቀንጭባችሁ በጽሁፍ አቅርቡ።

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ ስር የቀረበላችሁን ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✔)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | |
|---|---|---|
| 1. | የልቦለድ ምንነትን ማብራራት እችላለሁ። | |
| 2. | የልቦለድ አላባዊያንና ዘዴዎችን ምንነት መግለጽ እችላለሁ። | |
| 3. | የልቦለድ ባህሪያትን መዘርዘር እችላለሁ። | |
| 4. | የረጅም ልቦለድና አጭር ልቦለድ አንድነትና ልዩነት መጥቀስ እችላለሁ። | |
| 5. | ለረጅምና አጭር ልበለድ የተለያዩ ምሳሌዎችን መስጠት እችላለሁ። | |
| 6. | በልቦለድ ውስጥ የሚገኙ አላባውያንን መለየትና ማስረዳት እችላለሁ። | |
| 7. | ሁሉንም የልቦለድ አላባውያንና ዘዴዎች ተጠቅሜ ልቦለድ መፃፍ እችላለሁ። | |
| 8. | የልቦለድ ጭብጥን መተንተን እችላለሁ። | |
| 9. | በመጥበቅና በመላላት የትርጉም ለውጥ የሚያመጡ ቃላትን መለየት እችላለሁ። | |
| 10. | በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን መለየት እችላለሁ። | |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዱ ቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ስምንት

## ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን

### የሚጠበቁ ውጤቶች:-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- በቃል የተላለፍን መልዕክት በጥሞና በማዳመጥ የማጠቃለያ ሀሳብ ትሰጣላችሁ።
- የተሰጣቸውን ንግግር አዳምጣችሁ ምክረ ሀሳብ (አስተያየት) መስጠት ትችላላችሁ።
- የፅሁፉን ዋና ፍሬ ሃሳብ በማንበብ ትለያላችሁ።
- ምክንያታዊ ቅደም ተከተልን በጠበቀ መልኩ አከራካሪ ድርሰት ትጽፋላችሁ።
- የፅሁፍን ዓውድ በመጠበቅ ተመሳሳይና ተቃራኒ የቃላት ፍቺዎችን ትጠቀማላችሁ።
- ጊዜ ገላጭ ግሶችን በትክክል ትለያላችሁ።

## ክፍል አንድ: ማዳመጥ

በማዳመጥ ትምህርት ክፍል ማህበራዊ መገናኛዎችን የተመለከተ ምንባብ ቀርቧል። ምንባቡን በጥሞና አዳምጡና ተያይዘው የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ማህበራዊ መገናኛዎችን ትጠቀማላችሁ? ልምዳችሁን ለጓደኞቻችሁ አጋሩ።
2. ማህበራዊ መገናኛዎች ምን አይነት ጥቅምና ጉዳት ያላቸው ይመስላችኋል? በቡድን ተወያዩና ምላሽ ስጡ።

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ሀ. በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን ‘እውነት’፣ ስህተት ያለባቸውን ድግሞ ‘ሐሰት’ በማለት መልሱ።

1. ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን በአብሮነት ተከባብሮ በሰላም ለመኖር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ የሚሆነው በሀላፊነት ስሜት ከተጠቀምናቸው ብቻ ነው።
2. በማህበራዊ መገናኛዎች የሚነዙ የሀሰተኛ መረጃዎችን ለመቆጣጠር ጠንከር ያሉ ህጎችን ማውጣት ብቻውን ሊመጡ ከሚችሉ አደጋዎች ይጠብቃል።
3. በማህበራዊ መገናኛ ብዙሐንን መገልገልን ሙሉ በሙሉ መከልከል የዜጎችን በነጻነት ሀሳብን የመግለጽ መብትን መጉዳት ይሆናል።
4. በዴሞክራሲ የጎለበቱ አገሮች በማህበራዊ ሚዲያዎች በሚተላለፉ የሀሰተኛ ዜናዎች ጉዳት ሊያደርሱባቸው አይችልም።
5. ዜጎች መረጃዎችን እያጠሩ በመውሰድና ሀሰተኛ ወሬዎችን በመጠየፍ ብሎም ለስርጭታቸው ተባባሪ ባለመሆን ቢሰሩ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ለ. ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃንን በተመለከተ ያዳመጣችሁትን ምንባብ አጠቃላይ ሀሳብ ጨምቃችሁ በቃል አቅርቡ።

ሐ. በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን የተላለፈ አንድ ንግግር አዳምጡና መቼና ስለምን እንዳዳመጣችሁ ለክፍላችሁ ቃላዊ ዘገባ አቅርቡ።

# ክፍል ሁለት: መናገር

በዚህ ክፍል በመደበኛ የክርክር ሂደት በመሳተፍ የንግግር ክሂላችሁን ታጎለብታላችሁ ተብሎ ይታሰባል። በመሆኑም ትዕዛዙን ተከትላችሁ ዝግጅት በማድረግ የቀረበው ተግባር ተሳታፊ ሁኑ።

## ተግባር አንድ

ቀጥሎ ከቀረቡላችሁ የመከራከሪያ ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ፣ መምህራችሁ በሚመሰርጡላችሁ ቡድን መሠረት ጳኛ መርጣችሁ ምክንያታዊ ሃሳብ በማመንጨት ክርክር አድርጉ።

1. የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ጥቅማቸው ወይስ ጉዳታቸው ያመዝናል? ለምን?
2. ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን የሰዎችን ማህበራዊ ግንኙነት አጠናክረዋል ወይስ አላጠናከሩም?

# ክፍል ሶስት: ማንበብ

በማንበብ ክፍል የቀረበውን ምንባብ በጥንቃቄ አንብቡና የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን ትዕዛዙን ተከትላችሁ ስሩ።

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

በቡድን በመወያየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. መገናኛ ብዙኀን ማለት ምን ማለት ነው?
2. የምታውቋቸውን የመገናኛ ብዙኀን አይነቶች ጥቀሱ።
3. በመገናኛ ብዙኀን እና በማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

# መገናኛ ብዙኀን

መገናኛ ብዙኀን መልዕክትን በተመሳሳይ ጊዜ ለብዙ አንባቢያን፣ አድማጮች ወይም ተመልካቾች የማሰራጫ መሳሪያ ነው። ዘዴው በዋነኛነት ህብረተሰብን ተደራሽ ያደረጉ መረጃዎች በተደራጀና በተቀናጀ አሰራር በተለያዩ  የግንኙነት አግባቦች የሚደርሱበት ተግባቦታዊ ሂደት ነው።

የመገናኛ ብዙኀን አይነቶች ሶስት ናቸው።  እነሱም፡- የህትመት የመገናኛ ብዙኀን፣ የብሮድካስት /ኤሌክትሮኒክስ/ መገናኛ ብዙኀንና የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ናቸው። የህትመት የመገናኛ ብዙኀን ጥንታዊው /ቀዳሚው/ ሲሆን በቃላትና በስዕል ወይም በዕይታ አማካኝነት መልዕክትን ያስተላልፋል።  ይህ የመገናኛ ዘዴ መማርን የሚጠይቅና እያየን ለማንበብ የሚያስችል ነው። ለምሳሌ በኢትዮጵያ በ፲፰፻፹፩ (1881) ዓ.ም 'አዕምሮ' ከተሰኘው የመጀመሪያ ጋዜጣ ጥቅም ላይ መዋል ጀምሮ እስከአሁን ያሉት በርካታ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ በራሪ ወረቀቶች ወዘተ በዚህ የመገናኛ ብዙኀን አይነት ስር የሚጠቃለሉ ናቸው።

የብሮድካስት መገናኛ ብዙኀን በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ሲሆኑ ዜና አስተላላፊዎቹ እየተናገሩ ወደ ተመልካቹ በጆሮና በአይን አማካኝነት መልዕክት የሚያደርሱባቸው ናቸው። እነዚህ ዘዴዎች በተንቀሳቃሽና በማይንቀሳቀሱ ፎቶ ግራፎችና ስዕሎች አማካኝነት በጥምረት ወይም በተናጠል ታግዘው መቅረብ የሚችሉ ሲሆኑ ቴሌቭዥንና ሬዲዮን እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል።

ማህበራዊ የመገናኛ ብዙኀን የሚባሉት ደግሞ እንደ የብሮድካስት መገናኛዎች በኤሌክትሪክ ሀይል የሚሰሩ ሲሆን በህትመትም ሆነ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ መተላለፍ የሚችሉትን ጽሁፎች፣ ንግግሮች እንዲሁም ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ፎቶግራፎችና ስዕሎችን አንድ ላይ አቀነባብረው ወይም ለያይተው ማቅረብ የሚችሉ ናቸው። ማህበራዊ የመገናኛ ብዙኀን ከህትመት መገናኛ ብዙኀንም ሆነ

ከኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኀን የሚወስዱት የጋራ ባህርይ አለ። የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን መተላለፊያቸው ኢንተርኔት ሲሆን መተግበሪያዎችን ወይም ድረ ገጾችን ይጠቀማሉ። የእጅ ስልኮቻችንና ኮምውተሮቻችንም ለመገልገያነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። እንደ ፌስቡክ፣ ዋትስአፕ፣ ቲዊተር፣ ቴሌግራም፣ ኢሞ፣ ኢንስታግራም፣ ዩቲዩብ፣ ቫይበር፣ ሜሴንጀር፣ ቲክቶክና ወዘተ. በማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ስር የሚካተቱ ናቸው።

ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን በመላው ዓለም በተለይም በወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ በጣም ተንሰራፍተው ይገኛሉ። ዓላማቸው ሰዎችን እርስ በእርስ ማገናኘትና ማግባባት ነው። አንዳንድ ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ተመሳሳይ ፍላጎቶች ያላቸውን ሰዎች እንዲያገናኙ ወይም ሃሳብ እንዲለዋወጡ ለማስቻል የተፈጠሩ ናቸው። ይህ ሲባል ግን ሁሉም ሰው ይጠቀምባቸዋል ማለት አይደለም።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የመገናኛ ብዙኀን አይነቶች ____________________ ናቸው።
2. በማዳመጥና በማየት መረጃ የሚያቀርብ የመገናኛ ብዙኀን አይነት ምን ይባላል?
3. ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው። ቀጥሎ የቀረቡት አንቀጾችስ ምን ላይ ያተኩራሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?

መገናኛ ብዙኀን የሚሰጧቸው ጠቀሜታዎች የሚባሉት ወቅታዊ ዜናዎችንና መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ማድረስ፣ የሀገር መልካም ገጽታ እንደ ባህል፣ ታሪክ፣ እድገት ወዘተ.. ለሌላው ዓለም ማጋራት፣ የተለያዩ የንግድ ተቋማትንና ድርጅቶችን ማስተዋወቅ፣ ወዳጅነትን መፍጠር በተጨማሪም ለመዝናኛነትና ለግለሰቦች መተዳደሪያ ወይም የገቢ ምንጭ ሆነው ማገልገል ወዘተ... ናቸው። በማህበራዊ በይነ መረብ አማካኝነትም

ተመሳሳይ ፍላጎት ካላቸው ሌሎች ሰዎች ጋር እንድንገናኝ ይረዱናል፤ ተጠቃሚዎች ለጓደኞቻቸው የሚያጋሯቸውን ነገሮች ሁሉ በቅጽበት እንዲመለከቱ ያስችሏቸዋል።

በአንጻሩ ደግሞ ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ከጓደኞቻቸው፣ ከሚያስደስቷቸው ዝነኞች እና ከሚከተሏቸው ሰዎች ጋር የሚያገናኙ ብቻ አይደሉም፤ የሚያዝናኑ ጨዋታዎችም ብቻ አይደሉም፤ ብዙዎቹ የተለመዱ ማህበራዊ መገናኛ መድረኮች ችግሮች አሉባቸው።

በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች ግለሰብን ከግለሰብ፣ ቡድንን ከቡድን፣ ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጩ መረጃዎች በአንድ ጊዜ ለበርካታ ሰዎች ሊሰራጩባቸው ይችላሉ። እነዚህ የሐሰት ዜናዎችንም ይጨምራሉ። በዚህም ንብረት እና የሰው ህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያመጣሉ። ይህም የሀገርን ደህንነት ስጋት ላይ ከመጣሉም በላይ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ቀውሶችም ተከትለውት እንዲመጡ ያደርጋል። በሌላም በኩል ማህበራዊ መገናኝ ብዙኀን በቀላሉ ለጠላፊዎች የተጋለጡ በመሆናቸው የግል ሚስጥሮቻችንንና የተለያዩ የይለፍ ቃሎቻችንን (ለምሳሌ የባንክ) የተመለከቱ መረጃዎችን ለመንታፊዎች ሊያጋልጡብን ይችላሉ። በዚህም ገንዘብ ነክ ኪሳራ ከማስከተላቸውም ባሻገር የስነልቦናና ሌሎች ጤና ነክ ተጽዕኖዎችን ሊያመጡብን ይችላሉ። ከዚህም ሌላ ትኩረታችንን በመቆጣጠር ጊዜያችን ያለአግባብ እንዲባክን ማድረጋቸውም ሌላኛው ተግዳሮታቸው ነው።

በአጠቃላይ ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ወቅቱን የጠበቁ ዜናዎችንና መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ማድረስ፣ የሀገርን እድገት፣ ባህል፣ ታሪክ ወዘተ ለሌሎች ማስተዋወቅ፤ የሀገርን ደህንነትና ሰላም ማስጠበቅ፤ የተለያዩ የንግድ ተቋማትንና ድርጅቶችን ማስተዋወቅ የገቢ ምንጭ ሆኖ ማገልገል ወዘተ የሚባሉት የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ጠቀሜታዎች ሲሆኑ ጉዳታቸው ደግሞ የባህል መበረዝን፣ በህብረተሰቡ ላይ ሽብር መፍጠርን፤ የገበያ አለመረጋጋት ማስከተልን፤ የወገናዊነት ስሜት ማንጸባረቅን፤ የአንድን ሀገር ሰላም የሚያደፈርሱ እና ከእውነታ የራቁ ዜናዎችን ማሰራጨትን፣ የግል ሚስጥሮችን መመንተፍን ወዘተ ማስከተላቸው ነው።

ስለሆነም እኛ የአሁኑ ዘመን ትውልዶች የሚጠቅሙንንና ለራሳችን ብሎም ለአገር እድገት ፋይዳ ያላቸውን የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀንን መርጠን የመጠቀም ትልቅ ኃላፊነት አለብን።

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባብ የወጡ ናቸው፡፡ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. የህትመት መገናኛ ብዙኀንና ማህበራዊ የመገናኛ ብዙኀን የሚባሉት መማርን የሚጠይቁ ናቸው።
2. ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን እንደኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ እያዳመጥን ወይም እያየን መልዕክት የምንቀበልባቸው ናቸው።
3. አዕምሮ የተሰኘው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጋዜጣ ከማህበራዊ የመገናኛ ብዙኀን መካከል የሚጠቀስ ነው።
4. ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ከሚተቹባቸው ነጥቦች መካከል አንዱ ወቅቱን የጠበቁ ዜናዎችንና መረጃዎችን ለህብረተሰቡ አለማድረሳቸው ነው።
5. መገናኛ ብዙኀን በተመሳሳይ ጊዜ ለብዙ አንባቢያንና አድማጮች መረጃ የማሰራጨት አቅማቸው ከፍተኛ ነው።

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት አድርጋችሁ ከተሰጡት አማራጮች መካከል መልስ የሚሆኑትን በመምረጥ ጻፉ።

1. መረጃ በተንቀሳቃሽ ፎቶ ግራፎችና ስዕሎች አማካኝነት ታግዞ የሚቀርብበት የመገናኛ ብዙኀን አይነት የትኛው ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ. ሬዲዮ | ሐ. መጽሔት |
| ለ. ቴሌብዥን | መ. ‘ለ’ እና ‘ሐ’ መልስ ናቸው |

2. ከሚከተሉት አንዱ ስለማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ትክክል ነው።

   ሀ. ወቅቱን የጠበቀ ዜናዎችን ማድረስ አለመቻላቸው

   ለ. የገበያ አለመረጋጋትን የሚያስከትሉ አለመሆናቸው

   ሐ. የወገናዊነት ስሜት የማይንጸባረቅባቸው መሆን

   መ. የሀገርን እድገት፣ ባህል፣ ታሪክ ማስተዋወቅ መቻላቸው

3. ከማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ስር የማይካተተው የመገናኛ ብዙኀን አይነት የትኛው ነው?

   ሀ. ፌስቡክ
   ለ. ቲክቶክ
   ሐ. ቴሌግራም
   መ. መልስ አልተሰጠም

4. ከሚከተሉት አንዱ መገናኛ ብዙኀንን በተመለከተ ስህተት ነው።

   ሀ. በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኀን የተጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው።

   ለ. ተንቀሳቃሽ ስልኮችና ኮምፒውተሮች መገናኛ ብዙኀንን ለመከታተል ያስችላሉ።

   ሐ. በአሁኑ ወቅት በብቸኝነት እያገለገሉ ካሉ የመገናኛ ብዙኀን አይነቶች አንዱ ጋዜጣ ነው።

   መ. ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን የግለሰቦችን ምስጢር ለመንታፊዎች ሊያጋልጡ ይችላሉ።

5. የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን የስነልቦናና ሌሎች ጤና ነክ ተጽዕኖዎችን ሊያመጡብን ይችላሉ ሲል ምን ማለቱ ነው?

   ሀ. የስሜት መቃወስን ሊያስከትሉ ይችላሉ ማለቱ ነው።

   ለ. የምጣኔ ሃብት ጉዳት ያስከትላሉ ማለቱ ነው።

   ሐ. አካላዊ ጉዳት ያመጣሉ ማለቱ ነው።

   መ. ጊዜን አለአግባብ እንድንጠቀም ያደርጋሉ ማለቱ ነው።

## መልመጃ ሦስት

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን ‹‹መገናኛ ብዙኀን›› በሚለው ምንባብ ውስጥ ስለመገናኛ ብዙኀን ጠቀሜታ የተነሱ ነጥቦችን በመለየትጀ ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ።

2. ስለማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ከዚህ በፊት የምታውቁትን በምንባቡ ውስጥ ከአገኛችሁት ሃሳብ ጋር በማነጻጸር በጽሁፍ አስተያየት/ሂስ/ ስጡበት።

# ክፍል አራት: መፃፍ

**በመጻፍ ትምህርት ክፍል ድርሰትን የተመለከተ ማስታወሻና ተግባራት ቀርበዋል። ትዕዛዛቱን ተከትላችሁ ተግባራቱን ስሯቸው።**

1. ድርሰት ምንድን ነው? ቀደም ሲል የተማራችሁትን በማስታወስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

2. የድርሰት አይነቶችን በመዘርዘር ልዩነታቸውን በጽሁፍ አስረዱ።

## የድርሰት አይነቶች

ድርሰት በስርዓት በተዋቀሩ ዓረፍተ ነገሮች ወይም አንቀጾች ሊመሰረት የሚችል የጽሁፍ አካል ነው። ድርሰት የተለያዩ አይነቶች አሉት። እነዚህም ተራኪ፣ አስረጅ፣ ገላጭና አመዛዛኝ ድርሰት ናቸው። በዚህ ክፍል አመዛዛኝና ገላጭ ድርሰትን እንመለከታለን።

### ሀ. ገላጭ ድርሰት

የአንድን ነገር ምንነት፣ አሰራር፣ ቅርፅ፣ መጠን ወዘተ. በግልፅ የሚያሳይ የድርሰት ዓይነት ነው። አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራ ወይንም እንደሚፈጸም የሚያመለክት ወይም የሚመራ ድርሰት ገላጭ ድርሰት ይባላል። ገላጭ ድርሰትን ለመገንዘብ ይረዳን ዘንድ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

ምሳሌ፡ ነፋስ በአይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ ሲነፍስ ስሜቱ ለፍጥረት

ሁሉ የሚሰማ ነው። ይህ በራሪ አየር ተለይተው ከታወቁት አየሮች ከኩሬና በሀይቅ፣ ከባህርና ከፏፏቴች በፀሀይ ሀይል ተነስቶ በአየር ውስጥ ከሚዛወረው እንፋሎት፣ ከአትክልት ርግፍጋፊ፣ ከአቧራ በአየር ውስጥ ከሚገኙት ከጥቃቅን ነገሮችና ከትናንሽ ተባዮች ይመሰረታል።

## ለ. አመዛዛኝ ድርሰት

አከራካሪ ስለሆኑ ጉደዮች የሚጽፍ፣ አድማጩን(አንባቢውን) የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ሀሰትነት ለማሳመን የሚጥር የድርሰት ዓይነት ነው። ስለሆነም ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሀሳቦችን በማመዛዘን ክፉም ሆነ ደግ የትኛው እንደሚበልጥ ወይም እንደሚሻል ወዘተ የሚያሳይ ነው። አንባቢን ይዞት ከነበረው አቋም የሚመልስ በመሆኑ ሰባኪ ድርሰት ነው።

ምሳሌ፡ መድሀኒት ቀማሚና ደራሲ የሚለያዩበት ነጥብ አለ። ቀማሚ በአይን የሚታዩትንና በእጅ የሚዳሰሱትን ነገሮች እያሰባሰበና በእጁ እየገለበጠ ስለሚቀምማቸው ነው። ደራሲ ግን በአእምሮ እየሰበሰበና እየቀረፀ ይፅፋል እንጂ እንደቀማሚ በእጁ አይዳስሳቸውም ባይኑም አያያቸውም። ከተጠቀሱት ምክንያቶች በስተቀር እየሰበሰቡ ቀምሞና አዘጋጅቶ ለህዝብ በመስጠት ግን ሁለቱም አንድ ናቸው።

## ሐ. ተራኪ ድርሰት

ተራኪ ድርሰት አንድን ያለፈ ወይም የተከናወነ ድርጊት በጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት የሚያትት የድርሰት (የጽሑፍ) አይነት ነው። በዚህም ነበር፣ ሆኗል፣ ተረድኳል ወዘተ የሚሉ ሀላፊ ግሶችን ይጠቀማል። ግሶቹ ሀላፊ በመሆናቸው ተከናውኖ ያለፈን ድርጊት ለመግለጽ ያግዙታል። ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የመጻፍና ያለመጻፉ ሁኔታ እንደ ደራሲው የግል የፈጠራ ጥበባዊ ስራ የሚለያይ ቢሆንም በዋናነት ግን ታሪኩ የሚነግረን ተከናውነው ስላለፉ ድርጊቶችና ሁነቶች ነው።

ስሙ እንደሚያመለክተው ተራኪ ድረሰት ሁኔታንና ድርጊትን (ወይም ሰንሰለታዊ ሁነቶችን) እንዲህ ሆነ፣ እንዲህ ተደረገ እያለ የሚነግረን ወይም የሚተርክልን ነው። ታሪኩ ራሱ ጸሐፊው ወይም ተራኪው የደረሰበትን

(የገጠመውን)፣ በልምድ ያገኘውን፣ በሀሳቡ ያውጠነጠነውን፣ ከሌላ ሰምቶ የሚያስታውሰውን ያህል አሳጥሮ ወይም አስፋፍቶ የሚያቀርበው ሊሆን ይችላል።

ተራኪ ድርሰት ሁለት አይነት ሲሆን፣ እውናዊ ተራኪና ልቦለዳዊ ተራኪ።

## ሀ. እውናዊ ተራኪ

እውናዊ ተራኪ ክስተትንና ድርጊትን ወይም ተከታታይ ሁነትን የሚዘረዝር በአብዛኛው አደራደሩ የተለመደ የጊዜን ቅደም ተከተል (ተከታታይ ሰዓትን፣ ቀንን፣ ወርን፣ አመትን ወዘተ) የሚከተል የአጻጻፍ አይነት ነው። ለምሳሌ በጋዜጦች የሚወጡ የትራፊክ አደጋ ዜናዎች፣ የአካባቢ ጉብኝት፣ ስለክብረ በዓላት ወዘተ የሚወጡ ጽሑፎች በዚህ የድርሰት አይነት ስር ይካተታሉ። በእውናዊ ተራኪ ድርሰት ውስጥ የሚነሱ ታሪኮች በእውኑ አለም በተጨባጭ የተከሰቱ ናቸው።

## ለ. ልቦለዳዊ ተራኪ

ልቦለዳዊ ተራኪ እንደ እውናዊ ተራኪ ሁሉ ሁነቶችን ወይም ድርጊቶችን በጊዜ ወይም በክስተት ቅደም ተከተል የሚተርክልን የትረካ አይነት ነው። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በትክክል የተፈጸመ ወይም የተረጋገጠ መሆን እና ያለመሆን ጉዳይ ነው። እውናዊ ትረካ ታሪኩ በእውን የተከሰተ በተባለው ጊዜና ቦታ ተፈጽሞ የሚገኝ ሲሆን፣ የልቦለዳዊ ተራኪ ታሪክ ግን በደራሲው ምናብ የተፈጠረና በእውኑ አለም በተጨባጭ ሊታይ የማይችል ነው፤ በይሆናል የሚጻፍ ነው። በእርግጥ ያንን ታሪክ የሚመስል ሌላ ታሪክ ፈልጎ በእውኑ አለም ማግኘት ይቻላል። ምክንያቱም ታረኩ የሚደረሰው የሰው ልጆችን ገጠመኞች መሰረት አድርጎ ስለሆነ ነው።

ትረካ ወይም ተራኪ ጽሑፍ የራስን ገጠመኝ ወይም ለአድማጫችን ወይም አንባቢያችን የምንነገረውን የሌላ ሰው ታሪክ ሊሆን ይችላል። ትረካውም ተከታታይነት ያላቸው እውነታዎች ወይም ሁነቶችን የያዘና እውነታዎቹንና ሁነቶቹን ደረጃ በደረጃ እያጋመደ የሚያቀርብ ነው። በሌላ በኩል ትረካው እያንዳንዱን ገቢር (ንዑስ ታሪክ) በድርጊትና ምልልስ እያዋቀረ የሚያሳይ ተውኔታዊ አቀራረብን የተከተለ ስራ ነው። የታሪክ

ፍሰቱ የጊዜ ወይም የድርጊት ቅደም ተከተሉን በጥብቅ የተከተለ ወይም በምልሰት ስልት እየተቀናጀ የሚቀርብ ሊሆን ይችላል።

### መ. አስረጅ ድርሰት

አስረጅ ድርሰት ስለአንድ ሰው፣ ቦታ፣ ነገር ወይም ሁነት የሚያስረዳ የጽሕፈት አይነት ነው። የዚህ ድርሰት አይነት ጸሐፊ አላማ የአንድን ነገረ መልክ መግለጽ ሳይሆን ነገሩ ምን ማለት እንደሆነ እውነታውን፣ ማብራሪያውን፣ የግል ሀሳቦቹን መስጠት ነው። አስረጅ ድርሰት ትኩረቱን በአብዛኛው የሚያደርገው አንድን ባህሪ ወይም ሁኔታ መተንተን፣ አቅጣጫ መስጠት፣ መበየን እና ስለነገሩ ሌሎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ግልጽ ማብራሪያ ማቅረብ ወይም ማስረዳት ላይ ነው።

ለምሳሌ ስለቡና የሚጻፍ አስረጅ ድርሰት ቡና ምን አይነት የአየር ንብረት እንደሚያስፈልገው፣ ከየትኞቹ ዕጽዋት ተርታ እንደሚሰለፍ ስለሳይንሳዊና የወል መጠሪያው፣ መቼ መቼ እንደሚያፈራ፣ ከችግኝ እስከ ፍሬ ለቀማ ምን አይነት እንክብካቤ እንደሚያስፈልገው የሚያትት ይሆናል።

## መልመጃ አራት

1. የሚከተሉት አንቀጾች በየትኛው ድርሰት አይነት እንደሚመደቡ በየግላችሁ ካጤናችሁ በኋላ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ ምክንያቶቻችሁን በጽሁፍ አስፍሩ።

ሀ. እውነት ጠቢያ እጅግ ያማረች፣ እጅግ የታጠበች እጅግ የተደነቀች ላያት ሁሉ የምታነሆልል የምታዘናጋ ነበረች። ዓይኗን አስቀድሞ የብር አሎሎ መስሎ ካጥቢያ ኮከብ የተፎካከረ ነበር። በዚህ ላይ ግማሽ ሽፋሽፍቷ እንደ በልግ ሳር ተጨብጦ የሚታጨድ ይመስል ነበር። አፍንጨዋ ቀጥ ያለ፣ ከንፈሯ መፈንዳት የጀመረ የማለዳ ፅጌረዳ ይመስል ነበር። እንደ ወንድ የተቆረጠችው ጠጉርዋ እንደ ሰኔ ቡቃያ ወይም እንዳዲስ መሬት ጤፍ እየጋሸበ የሀር ነዶ መሰለ በፀሐይና በውርጭ የተጎሳቆለውና የጠቀረው ፊቷ እያሸለተ ሀጫ በረዶ ከመሰለው ጥርሷ ጋር ገና ከርቀ እየጠቀሰ ከተሸሸገበት ሴትነቷን ያሳጣባት ጀመር።

(አፍወርቅ ገብረየሱስ 1958፡64)

ለ. በሀረር አካባቢ የተወለዱት አቶ መንግስቱ ለማ በልጅነታቸው የዜማና የቅኔ ትምህርት ቀስመዋል፤ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሀረር፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ከተማ ተከታትለዋል። ከዚያም ወደ ውጪ ሀገር በመሄድ ከፍተኛ ትምህርት የተከታተሉ ሲሆን ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ በልዩ ልዩ መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል።

ሐ. ማንጠግቦሽ በዚህ ሙያዋ ሳውቃት ጥቂት ወራት አልፈውኛል። የድምጧ ቅላጼዋ የምታወርደው ግጥም ዘወትር ይማርከኛል። ያን ትንሽ ጠጅ ቤትም ማዘውተር የጀመርኩት ለእርሷ ስል ነው። ከድምጧ በተጨማሪ ሰው አክባሪነቷ እና ትህትናዋ በእንደኔ ያለ ሰው ተወዳጅ አድርጓታል።

መ. ኢትዮጵያ ከድህነት ለመውጣት የሚበጇት ዜጎች በራሳቸው መፍትሔ ሲፈልጉ ነው። ባዕድ በቀየሰው መንገድ መጓዝ ሀገሪቱን ፈጹም አይጠቅማትም፤ ህዝቡ የራሱን እደ ጥበብና ፈጠራ እንዲሁም የስራ ፍቅር ማሳደግ አለበት። ይህ ከሆነ ኢትዮጵያ ከድህነት ልትላቀቅ ትችላለች። በእርግጥ ኢትዮጵያ ከኋላቀርነት ለመውጣት የተሻለ አማራጭ የሚሆናት ከውጭ ሀገራት ጋር መልካም ግንኙነት መመስረትና ጥሩ ብድርና እርዳታ የምታገኝበትን መንገድ መቀየስ ነው። ሌሎች ሀገራት ያለቸውን ያህል ዕምቅ ማዕድን የሌላት ሀገር ድህነትን በራሷ ተፍጨርጭራ ታሸንፋለች ማለት ዘበት ነው የሚሉ ወገኖች አሉ። ይህ አስተሳሰብ በራሱ ኋላቀር አስተሳሰብ ነው።

የጥገኝነት አስሳሰብ ሰዎች በራሳቸው መተማመን እንዳይኖራቸው ኋላፊነትን የሚቀበሉና የሚወጡ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ነው። ሰዎች የችገራቸውንና የጎደላቸውን ከሌሎች መቀባለቸው ያለ ቢሆንም የጠባቂነትና የተረጅነት መንፈስን የሚያዳብር በመሆኑ ፍጹም የሚደገፍ አይደለም። ጉዳዩን ወደሀገር ሰፋ አድርገን ስንመለከተውም ተመሳሳይ መደምደሚያ ላይ እንደርሳለን። ደሀ የሚባሉ ሀገራት ከድህነት ለመውጣት ብቸኛ አማራጫቸው በራሳቸው ሀብትና ህዝብ መጠቀም ነው።

2. በሚከተሉት ርዕሶች አመዛዛኝና ገላጭ ድርሰት ጻፉ።

ሀ. ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ከሚያስከትሉት ጉዳት ይልቅ ጠቀሜታቸው ያመዝናል። (አመዛዛኝ)

ለ. የትምህርት ቤታችሁን አጠቃላይ ገጽታ በገላጭ ድርሰት ስልት ጻፉ።

3. የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን አጠቃቀምን በተመለከተ (ገጠመኛችሁን መሰረት አድርጋችሁ) ምክንያታዊ ቅደም ተከትልን በጠበቀ መልኩ የተሟላ አከራካሪ ድርሰት ጻፉ።

# ክፍል አምስት: ቃላት

በቃላት ትምህርት የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። የተሰጡትን ትዕዛዞች ተከትላችሁ ስሯችሁ።

## መልመጃ አምስት

ሀ. በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

1. የሀሰት ወሬዎችን ስርጭት <u>መግታት</u> የሚቻለው በጋራ በሚደረግ ጥረት ነው።

2. የማህበራዊ መገኛኛ ዘዴዎች መበራከት ሰዎች ተግባቦታቸውን <u>እንዲያሳልጡ</u> ረድተዋል።

3. መገናኛ ብዙሃን <u>ዘርፈ ብዙ</u> ጠቀሜታዎች ስላላቸው ልንከባከባቸው ይገባል።

4. በርካታ ወጣቶች <u>ህልሞቻቸውን</u> ለማሳካት ቀን ከሌት ሳይሰለቹ ጠንክረው ይሰራሉ።

5. ከማህበረሰቡ <u>እሴቶች</u> ያፈነገጡ ተግባራት በየትኛውም መንገድ ተቀባይነት የላቸውም።

6. የሰው ልጅ <u>እምቅ</u> የፈጠራ ችሎታዎቹን እየተጠቀመ ልዩ ልዩ ተግባራትን ይከውናል።

7. መገናኛ ብዙሃን ያሉባቸውን ተግዳሮቶች በጥናትና ምርምር እየታገዙ መቅረፍ ይቻልል።

8. ማህበራዊ መገናኛዎች ማህበራዊ እሴቶቻችንን እንዳይሸረሽሩ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

ለ. የሚከተሉት ቃላት መገናኛ ብዙኃን ከሚለው ምንባብ የወጡ ናቸው። ለቃላቱ ተመሳሳይና ተቃራኒ የሚሆኑ ሌሎች ቃላትን ፈልጋችሁ ጻፉ።

1. በመጣመር
2. የሚያመናምኑ
3. ያገባኛል
4. ተከባብሮ
5. መፍትሔ
6. ሚዛናዊነት
7. የሚያጋጩ
8. ጎልብቶባቸዋል
9. በሬ ወለደ
10. አወንታዊ

# ክፍል ስድስት: ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ክፍል ሰዋስዋዊ ጊዜን የተመለከተ ጽንሰ ሀሳብ እና መልመጃ ቀርቧል። ማስታወሻውን በማንበብና ትዕዛዞቹን በመከተል መልመጃውን ስሩት።

1. የግስ ጊዜ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. የምታውቋቸውን የግስ ጊዜዎች ጥቀሱ።

## የግስ ጊዜ

ጊዜ አንድ ድርጊት መቼ እንደተፈጸመ ወይም መቼ እንደሚፈፀም የሚገልፅ የግስ ባህሪ ነው። ጊዜ በሶስት ሊከፈል ይችላል። እነሱም፡ - የአሁን ጊዜ ፣ ሀላፊ ጊዜ እና የትንቢት ጊዜ ናቸው።

ሀ. የአሁን ጊዜ

አንድ በአሁኑ ጊዜ የሚፈፀም ወይም በመፈፀም ላይ ያለ ድርጊትን ወይም ሁነትን የሚገልፅ የጊዜ ዓይነት ነው። የአሁን ጊዜ የሆነ ግስ "እየ-" የሚል ምዕላድ ሊያስቀድምና "-ነው" የሚል ረዳት ግስ

ሊያስከትል ይችላል።

ምሳሌ፡ ሀ. ትህትና ቁርስ እየ-ሰራች ነው።

ለ. ጉርሜሳ እራቱን እየ-በላ ነው።

ሐ. መሐመድ አስ-ተማሪ ነው።

ለ. የኃላፊ ጊዜ

አንድ ድርጊት ከአሁን በፊት ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን የሚገልፅ የጊዜ ዓይነት ነው።

ምሳሌ፡ ሀ. ሀሊማ ትናንት ሁለት በግ ሸጠች።

ለ. ዘርትሁን አንድ ፎቅ ሰራች።

ሐ. የትንቢት ጊዜ

አንድ ድርጊት ገና ያልተፈፀመና ወደፊት የሚፈፀም መሆኑንይገልፃል። የሚገለፀውም በጊዜ ተውሳከ ግስና ‹‹-አል›› በሚለው ረዳት ግስ አማካኝነት ነው።

ምሳሌ፡ ሀ. ደራርቱ ነገ ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለች። (ትሄድ-አለች)

ለ. ኡቦንግ ከሳምንት በኋላ ወደ ሀገር ቤት ይመለሳል።

(ይ-መለስ-አል)

## መልመጃ ስድስት

1. በቡድን በመሆን የሚከተሉትን ግሶች የኃላፊ፣ የአሁን ወይም የትንቢት ጊዜያት መሆናቸውን ለዩ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ትመጣለች | ሠ. ደረሰች |
| ለ. ፈራ | ረ. አለፈ |
| ሐ. ይሰበሰባል | ሰ. ይሸፍን |
| መ. ነበር | ሸ. እየጸዳ ነው |

2. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ግሶችን የኃላፊ፣ የአሁን እና የትንቢት ጊዜ መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ።

1. ጥሩነሽ እየሮጠች መጣች።
2. የጓመናውን መጥቆር ለተመለከተው ዛሬ ይዘንባል።
3. መምህራችን የቤት ስራ ሰጥተውን ነበር።
4. ጎበዙ ተማሪ በሰራው ስራ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ተደስተዋል።
5. ቃሉን ጠብቆ እየኖረ ነው።

3. ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በቡድን በመሆን ምሳሌውን መሰረት አድርጋችሁ ቅጥያዎችን በመጨመር የኃላፊ፣ የአሁን እና የትንቢት ግሶችን በመመስረት አሟሉት።

| ተ.ቁ | የኃላፊ ጊዜ | የአሁን ጊዜ | የትንቢት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| | አመሰገነ | እያመሰገነ ነው | ያመስግናል |
| 1. | | እየተኛ ነው | |
| 2. | ጻፈች | | |
| 3. | | | ይዘፍናል |
| 4. | | እየሰበረ ነው | |
| 5. | ገሰጸ | | |
| 6. | | | ይገኛል |

አንዳንድ ግሶች የኃላፊ እና የአሁን ጊዜ ግሶች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ረዳት ግስ ያስፈልጋቸዋል።

ምሳሌ: ልጁ እየበላ ነው። በ ‹‹እየ-- ነው›› የሚለው የአሁን ጊዜ መሆኑን ሲያመለክት፣ ልጁ እየበላ ነበር። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ደግሞ ‹‹እየ --- ነበር›› ድርጊቱ በኃላፊ ጊዜ የተከናወነ መሆኑን ያመለክተናል። በሁለቱም ዓረፍተነገሮች ድርጊቱ ያልተቋረጠና በሂደት ላይ ያለ (የመጀመሪያው አረፍተ ነገር )ወይም በሂደት ላይ የነበረ (ሁለተኛው አረፍተ ነገር) መሆኑን እንረዳለን።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስለማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ተምራችኋል። በተለይም ስለ መገናኛ ብዙኀን ምንነት፣ ዓይነቶችና የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ጥቅምና ጉዳት የሚሉትን ተረድታችኋል።

የድርሰት አይነቶች በስርዓት የተዋቀሩ ዓረፍተ ነገሮች ወይም አንቀጾች ሊመሰርቱት የሚችሉ ጽሁፍ እንደሆነ ተረድታችኋል። በመቀጠል ከድርሰት ዓይነቶች መካከል አመዛዛኝ /አከራካሪ/ ስለሆኑ ጉደዮች የሚጽፍ፣ አድማጬን(አንባቢን) የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ሀሰትነት ለማሳመን የሚጥር ድርሰት እንደሆነ ተረድታችኋል። ገላጭ ድርሰት ደግሞ የአንድን ነገር ምንነት፣ አሰራር፣ ቅርፅ፣ መጠን ወዘተ. በግልፅ የሚያሳይ የድርሰት ዓይነት ነው። አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራ ወይንም እንደሚፈጸም የሚያመለክት ወይም የሚመራ ድርሰት እንደሆነ ተረድታችኋል። በመቀጠል በተሰጣችሁ የድርሰት ርዕስ የራሳችሁን ድርሰት ጽፋችኋል።

ከዚህም በተጨማሪ ስለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ፣ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገር መስርታችኋል። የግስ ጊዜ በተለይም የኃላፊ፣ የአሁንና የትንቢት ጊዜን ለይ ለማመልከት የሚረዱ ግሶችን እየተጠቀማችሁ ዓረፍተ ነገር መስርታችኋል። በአጠቃላይ ሰዋስዋዊ ጊዜን ለይታችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የመገናኛ ብዙኀን የሚባሉትን በመዘርዘርና ምሳሌዎቻውን በመጥቀስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አስረዱ።

2. የህትመት የመገናኛ ብዙኀንንና የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀንን በተመለከተ አጭር አመዛዛኝ ድርሰት በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

3. የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን በሚያሳይ መልኩ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።

ሀ. ነፋስ　　　　ሐ. ቆቅ

ለ. ዶማ　　　　መ. ጨለማ

4. በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ለሚገኙ ቃላት በምሳሌው መሰረት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ።

| ተ.ቁ | ቃል | ተመሳሳይ ፍቺ | ተቃራኒ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| | በደምሳሳው | በጥቅሉ | በነጠላው |
| | መናድ | ማፍረስ | መደርደር |
| 1. | ቆንቋና | | |
| 2. | ገሀድ | | |
| 3. | ጨቀነ፣ | | |
| 4. | ምርቃት | | |
| 5. | አዋቀረ | | |
| 6. | አውሸለሸለ | | |

4.የግስ ጊዜን (የኃላፊ፣ የአሁን እና የትንቢት ጊዜ) የሚያሳዩ ሁለት ሁለት ዓረፍተ ነገሮችን ለእያንዳንዳቸው መስርቱ፡፡

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ ስር የቀረበላችሁን ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁት የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✔)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | |
|---|---|---|
| 1. | የመገናኛ ብዙኀን አይነቶችን ተረድቼ መዘርዘር እችላለሁ። | |
| 2. | የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ጥቅምና ጉዳት ለይቻለሁ። | |
| 3. | በቃል የተለያየን መልዕክት በጥሞና በማዳመጥ ማጠቃለያ ሀሳብ እሰጣለሁ ። | |
| 4. | በተለያዩ የመገናኛ ብዙኀን ላይ የሚተላለፉ አወዛጋቢ ንግግሮች ላይ ጠቃሚ የሆኑ ሂሶች መስጠት እችለላሁ። | |
| 5. | የተለያዩ የማንበብ ስልቶችን በመተግበር ዋናውን ሀሳብ መለየት እችላለሁ። | |
| 6. | ምክንያታዊ ቅደም ተከተልን በጠበቀ መልኩ ሙለ በሙለ አከራካሪና ገላጭ ድርሰት እጽፋለሁ። | |
| 7. | የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠት እችላለሁ። | |
| 8. | ለተለተያዩ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ በመስጠት በዓረፍተ ነገር ውስጥ መርጬ እጠቀማለሁ። | |
| 9 | በንግግር እና በጽሁፍ ውስጥ ሁሉንም የግዜ ግሶችን በትክክል በመጠቀም ለፈለጉት ውጤት መጠቀም እችላለሁ። | |
| 10 | የግስ ጊዜያትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መመስረት እችላለሁ። | |

ከዚህ በላይ ባለው በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዱቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ሥራ ፈጠራ

## የሚጠበቁ ውጤቶች:-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- አዳምጣችሁ በማስረጃ መስማማታችሁንና አለመስማማታችሁን ታሳያላችሁ።
- ሀሳባችሁን በምክንያት በማስደገፍ በቃል ትገልጻላችሁ።
- ፅሁፍ በማንበብ ለማን እንደ ተጻፈ ትለያላችሁ።
- የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከፅሁፍ አውድ በመነሳት ትሰጣላችሁ።
- በዓርፍተነገር ውስጥ ተሻጋሪ እና ኢ-ተሻጋሪ ግሶችን ትጠቀማላችሁ፡

## ክፍል አንድ: ማዳመጥ

በማዳመጥ ትምህርት ክፍል የሥራ ፈጠራ ሃሳብ መገኛ ምንጮች የሚል ምንባብ ቀርቧል።ከምንባቡ በፊትና በኋላም የተለያዩ ጥያቄዎች ተሰጥተዋል። ትዕዛዞቹን ተከትላችሁ ጥያቄዎቹን ስሯቸው።

### የሥራ ፈጠራ ሃሳብ መገኛ ምንጮች

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. አዲስ ሥራ ለመፍጠር ምን ምን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባችኋል?
2. በየትኞቹ የስራ ዘርፎች ብትሰማሩ ደስተኛ የምትሆኑ ይመስላችኋል? ለምን?

## የማዳመጥ ጊዜ

ከዚህ ቀጥሎ መምህራችሁ ‹‹የሥራ ፈጠራ ሃሳብ መገኛ ምንጮች›› የተሰኘ ምንባብ ያነቡላችኋል። የምትስማሙባቸውንም ሆነ የማትስማሙባቸውን ነጥቦች ማስታወሻ ደብተሮቻችሁ ላይ በማስፈር ማዳመጡ ሲጠናቀቅ ከጓደኞቻችሁ ጋር በነጥቦቹ ዙሪያ ተወያዩ።

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

1. የሚከተሉት ቃላት ካዳመጣችሁት ምንባብ የወጡ ናቸው። አውዳዊ ፍቺ ስጧቸው።

| | |
|---|---|
| እርካታ | ምርምር |
| ደንበኞች | አማራጮች |
| ማመንጨት | ዘርፍ |
| ተቋማት | መቃኘት |

2. የሥራ ፈጠራ ሃሳቦች መገኛ ምንጮችን ዘርዝሩ።
3. አዲስ የንግድ ስራ ለመጀመር ቀድሞ በየትኛው መስክ መሰማራት እንዳለብን መምረጥ የሚያስፈልገው ለምን ይመስላችኋል?
4. ‘ደንበኞች የሥራ ፈጠራ ሃሳብ መገኛ ምንጮች ይሆናሉ’ የሚለውን ሀሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም ምክንያታዊ የሆነ ገለጻ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

# ክፍል ሁለት: መናገር

## ተግባር አንድ

**በመናገር ትምህርት ክፍል ስራ ፈጠራን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን መሰረት በማድረግ ንግግርን በክፍል ውስጥ ተለማመዱ።**

1. የስራ ፈጠራን አስፈላጊነት በተመለከተ አሳማኝ ምክንያት በማቅረብ በቡድን ሆናችሁ ውይይት አድርጉና የደረሳችሁበትን ለክፍሉ አጋሩ።

2. ስራ ለመፍጠር የሚያስችሉ ብልሃቶችን ከተለያዩ ምንጮች በመፈለግ ቃላዊ ዘገባ አቅርቡ።

# ክፍል ሶስት: ማንበብ

**በዚህ ምዕራፍ የማንባብ ክፍል 'ስራ ወዳዱ የጥበብ ባለሙያ' በሚል ርዕስ ሠዓሊ ለማ ጉያን የተመለከተ ምንባብ ቀርቧል። ምንባቡን በጥሞና አንብቡና ተከትለው የመጡ ጥያቄዎችን መልሱ።**

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስራ ፈጠራ ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ ጥንድ ጥንድ ሁናችሁ በወያየት ሀሳባችሁን ለክፍሉ አጋሩ።

2. ኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂ ከሆኑ ሰዓሊያን መካከል እነማንን ታውቃላችሁ?

3. ስለ አርቲስት ለማ ጉያ የምታውቁትን ተናገሩ።

# ስራ ወዳዱ የጥበብ ባለሙያ



የክብር ዶክተር ሎሬት አርቲስት ሻንበል ለማ ጉያ ከአባታቸው ጉያ ገመዳና ከእናታቸው ማሬ ጎበና በቀድሞው ምስራቅ ሸዋ አድአ ሊበን ወረዳ ደሎ በሚባል ቀበሌ ውስጥ ነሐሴ 12 ቀን 1921 ዓ.ም ተወለዱ። በልጅነታቸው እናታቸው የእጅ ስራ አዋቂና ባለሙያ ነበሩና ለማ እንደማንኛውም የየአካባቢው ሕፃናት ሁሉ የህፃንነት እድሜያቸውን ተጫውተውና ተሯሩጠው ከማሳለፍ ይልቅ የእናታቸውን ፈለግ በመከተል የቅርፃ ቅርፅ ሥራን አጥብቀው ይወዱና አዘውትረውም ይሰሩ እንደነበር ይነገራል።

በዚህም ለሙያው በነበራቸው ከፍተኛ ፍቅርና በሸክላ ውጤቶች በሚሰሯቸው የሰው፣ የእንስሳትና የቁሳቁስ ቅርፆች ቤተሰባቸውንም ሆነ የአካባቢውን ሰዎች በማስደነቃቸውና ትኩረትን በመሳባቸው በአካባቢው ማህበረሰብ ጫና ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት እንዲገቡ እድሉ ተመቻቸላቸው። በአስራ አምስት አመታቸውም ከሚኖሩበት ቀበሌ በአስር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው በቀድሞው አጠራር አፄ ልብነ ድንግል ትምህርት ቤት በመግባት ትምህርታቸውን ጀመሩ። በጊዜውም እስከ ሰባተኛ ክፍል ድረስ ይሰጥ የነበረውን ዘመናዊ ትምህርት በ1943 አጠናቀው ቶሎ ሥራ በመያዝ ቤተሰባቸውን ለመርዳት በነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ አዳማ በድሮ ስሙ ዓፄ ገላውዴዮስ ተብሎ በሚጠራው የመምህራን ተቋም በመግባት በመምህርነት ሠልጥነው ሥራ ጀመሩ። ነገር ግን መልሰው

ሥራቸውን በማቋረጥ ወደ ትውልድ ቀያቸው ተመለሱ።

የዚያን ጊዜው ብርቱ ወጣት ለማ ጉያ ታዲያ ከሕፃንነታቸው አንስቶ በልባቸው የሰረፀውን የዕደ-ጥበብ እና የሥነ-ሥዕል ሙያ ለማሳደግ ብሎም ስለሙያው ጠለቅ ያለና በቴክኖሎጂ የታገዘን እውቀት ለመገብየት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሲያሰላስሉ ቆይተው አንድ መላ በህሊናቸው ብልጭ ይልላቸዋል። ይኸውም ከእንጨት በመስራት በቀለማት ያስዋቡትን የአውሮፕላን ሞዴል በየሳምንቱ መጨረሻ ወደ ቢሾፍቱ ለሚመጡት ንጉስ ኃይለሥላሴ ማሳየትና ትኩረታቸውን መሳብ ነበር። ሃሳባቸውም ተሳክቶላቸው በአንድ ወቅት ንጉሱ ለጉብኝት ወደ ቢሾፍቱ በሄዱበት ጉዜ ከንጉሱ ፊት ቀረቡ። ንጉሱም የለማን ሥራ አይተው እጅግ በመደነቃቸው ምን እንዲደረግላቸው እንደሚፈልጉ ይጠይቋቸዋል። እርሳቸውም አየር ሃይል ገብተው መማር እንደሚፈልጉ ነገሯቸው። ንጉሱም ፍላጎታቸው እንዲፈጸምላቸው አዘዙላቸው።

የንጉሱን ይሁንታ ያገኙት ለማ ጉያም የአየር ሃይል ማሰልጠኛ ተቋምን ተቀላቅለው በአውሮፕላን መካኒክነት ሙያ ስልጠናን ጀመሩ። በአየር ሃይል ማሰልጠኛ ተቋሙ የሚሰጠውን ስልጠና ካጠናቀቁና ለሁለት አመታት በማሰልጠኛው ካገለገሉ በኋላ በ1945 በወጣት ዕጩ የፖሊስ ኃይል ሰልጣኝነት /ካዴት/ የሚሰጠውን ስልጠና በማጠናቀቅ በ1950 በከፍተኛ ውጤት ተመረቁ። በምርቃታቸው እለትም አፄ ኃይለስላሴ አቪዬ የተሰኘ የወርቅ ሰዓት ከተሟላ የስዕል መሳያ ቁሳቁሶች ጋር በስጦታ መልክ አበርክተውላቸዋል። ከምርቃታቸው በኋላም አስመራ ከተማ በሚገኘው የአየር ሃይል ጣቢያ በመምህርነት እንዲሁም በጦር መሀንዲስነት ሙያቸው በቅንነት አገልግለዋል።

## የሠዓሊ ለማ የሥነ-ሥዕል ጉዞ

የክብር ዶክተር ሎሬት አርቲስት ሻንበል ለማ ጉያ እናት ማሬ ጎበና ከሚሰሩት የሸክላ ሥራ በተጨማሪ፣ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን የአፈር አይነቶች በመደባለቅ የተለያዩ የሰዎችንና የእንስሳቶችን ሥዕሎች በቤታቸው ግድግዳ ላይ ይስሉና ለቤቱም ልዩ የሆነ ውበትና ድምቀትን ይፈጥሩ እንደነበር ይነገራል። ይህንንም እየተመለከቱ ያደጉት ለማ

ለሥዕል ያላቸው ፍቅር እለት ከእለት እየጨመረና የእናታቸውን የቀለማት ውህደት እና የአሳሳል ዘይቤ በጥልቀት በመመልከት የሰው፣ የእንስሳት እንዲሁም የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን በመሳል፣ በህፃንነት እድሜያቸው የሥዕል ሥራቸውን አህዱ ብለው ጀመሩ። ቀስ በቀስም በትምህርትና በተለያዩ ስልጠናዎች ችሎታቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሻሻል በሀገራችን የሥነ-ጥበብ ታሪክ ላይ የራሳቸውን ደማቅ ዱካ ማሳረፍ የቻሉ ታዋቂና ዝነኛ የሥዕል ባለሙያ ለመሆን በቅተዋል።

ተፈጥሮአዊ የአሳሳል ዘይቤን የሚያዘወትሩት ሠዓሊ ለማ ጉያ በአገራችን ዘመናዊ የምስል ቴክኖሎጂ ባልተስፋፋበት ወቅት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦችን የአለባበስና የአኗኗር ዘይቤን የሚገልፁ፣ በተለይም የኦሮሞን ህዝብ ትውፊትና ባህልን የሚያጎሉ ሥዕልች በመሳልና በማሳተም በመላው አገሪቱ እንዲዳረሱ በማድረጋቸው ይታወቃሉ። በይበልጥ ግን ላለፉት 65 ዓመታት በፍየል ቆዳ ላይ የሳሏቸውና በቁጥርም ከ10 ሺህ በላይ እንደሚሆኑ የሚነገርላቸው የሥዕል ሥራዎቻቸው ከፍተኛ የሆነ አድናቆትና ዝናን አትርፈውላቸዋል። ከእርሳቸው ቀደም ብሎ በቆዳና በብራና ላይ የተሰሩ በርካታ የፈጠራ ሥራዎች ቢኖሩም እርሳቸው ግን የፍየል ቆዳ ሙሉ ለሙሉ ፀጉሩ ሳይነሳ ተፈጥሯዊ ወዝና ውበቱን እንደጠበቀ የፊትን ገፅ በላዩ ላይ በቀለም በመስራት ብዙዎችን አስደምመዋል። ከእነዚህም ሥዕሎች ውስጥ በዋናነት የኢትዮጵያና የአፍሪካ መሪዎች፣ ዲፕሎማቶች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ ብሄር ብሄረሰቦች አኗኗር፣ ወግና ባህል እንዲሁም የተለያዩ የአገራችንን ገፀ ምድሮችና የተፈጥሮ ሐብቶች የሚያሳዩ ተወዳጅ ሥራዎች ይገኙበታል። ‹‹የሸክላ ገበያ››፣ ‹‹የደንከል ልጃገረድ››፣ ‹‹ቋንጣ››፣ ‹‹አቦል ቡና››፣ ‹‹እሬቻ››፣ ‹‹ዋርካ››... የሚል መጠሪያ የተሰጣቸው ስራዎቻቸውም በአብነት ይጠቀሳሉ።

በ1968 ከአየር ሃይል በጡረታ የተገለሉት አርቲስት ለማ ጉያ ቀሪ ህይወታቸውን ለሥነ-ጥበብ በማዋልና በተለይም በአገራችን የሥነ ጥበብ ማሳያ ጋለሪዎችን በስፋት አለመኖራቸውን በማስተዋል ከ30 በላይ የውጭ አገራት ዲፕሎማቶችን ጋብዘው ሥራዎቻቸውን በማሳየት የሥዕል ማሳያ ማዕከል እንዲመሠረት አድርገዋል። ይህም ‹‹የአፍሪካ አርት ጋለሪ›› የሚል

መጠሪያ የተሰጠውና በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኘው የአርቲስት ለማ ጉያ





የሥዕል ሥራዎች ማሳያ ማዕከል መታሰቢያነቱን ለኔልሰን ማዴላ በማድረጉ በግቢው ውስጥ ሀውልት ተሰርቶ የቆመላቸው ሲሆን አራት የማሳያ ቤቶችን በመገንባት ማሳያዎቹ ምንጊዜም ለተመልካች ክፍት ሆነው በለማ ጉያ የሥዕል ሥራዎች ቀጣዩ ትውልድ እንዲማር እየተደረገ ይገኛል።

የክብር ዶክተር ሎሬት አርቲስት ሻንበል ለማ ጉያ ቢሾፍቱ ከተማ ባቋቋሙት‹‹የአፍሪካ አርት ጋለሪ›› ግቢ ውስጥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመክፈት አገራዊ ግዴታቸውን ሲወጡም ቆይተዋል። በአገራችን ታሪክና በሥዕሉ ዘርፍ የመጀመሪያ የሆነውን ‹‹የሥዕል ያለአስተማሪ መጽሐፍ››ም ተርጉመው በመላው አገሪቱ ባሉ ትምህርት ቤቶች እንዲሰራጭ በማድረጋቸውም ታሪክ ምንጊዜም ሲያስታውሳቸው ይኖራል።

ለማ ጉያ በሥራቸው በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ አገራት መሪዎች ልዩ ልዩ ሽልማቶችን የተቀበሉ ሲሆን፣ የጅማ ዩኒቨርሲቲም በስነጥበብ ዘርፍ የክብር ዶክተሬት ዲግሪ አበርክቶላቸዋል። ሠዓሊ ለማ ጉያ ተመሳሳይ ሙያ ካላቸው ልጆቻቸው እና ወንድሞቻቸው ጋር በመሆን በተለያዩ የአለም አቀፍ እና የአገር ውስጥ መድረኮች ላይ ሥራዎቻቸውን አቅርበዋል። ከአገር ውጪ በአሜሪካ፣ ስዊዲን፣ እንግሊዝ፣ ኬንያ፣ ናይጄሪያ ሴኔጋልና ሌሌች አገራት ውስጥ ያሳዩ ሲሆን ሦስት ትውልድ የተናገሩ የጥበብ ሥራዎች በሚል በሰሜን አሜሪካ የውስጥ ቅርስ ማህበር ተሸላሚም

ሆነዋል።

(አዲስ ማለዳ፤ ቅጽ 2 ቁጥር 104 ጥቅምት 21 2013፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት ለማስተማሪያነት የቀረበ)

## የአንብቦመረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ ተገቢ ምላሽ ስጡ።

1. ካነበባችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ?
2. ለሰዓሊ ለማ ጉያ የሥዕል ስራ መነሻ የሆኗቸው ማን ናቸው?
3. ሰዓሊ ለማ ጉያ ለሀገራቸው ያበረከቷቸውን አስተዋጽዖዎች ዘርዝሩ።
4. የወደዱትን ሥራ መስራት ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ የሰዓሊ ለማ ጉያን ህይወት በማሳያነት በመጥቀስ አስረዱ።
5. የሰዓሊ ለማ ጉያን ሥራዎች ከሌሎች ሰዓሊያን ልዩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

**ለ. በምንባቡ መሰረት የተነሱትን አበይት ነጥቦች ከሚገናኙባቸው አንቀጾች ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የፍየል ቆዳ ጸጉሩ ሳይነሳ የቀለም ስዕል የሚስሉበት ስለመሆኑ | ሀ. አንቀጽ 1 |
| 2. ስለወላጆች እና የትውልድ ስፍራ | ለ. አንቀጽ 2 |
| 3. ስዕል ያለአስተማሪ መጽሐፍ ስለመተርጎማቸው | ሐ. አንቀጽ 3 |
| 4. ሞዴል አውሮፕላን ለንጉሱ ስለማሳየታቸው | መ. አንቀጽ 4 |
| 5. የእናታቸውን የአሳሳል ጥበብ ስለመከተላቸው | ሠ. አንቀጽ 5 |
| 6. ዕጩ ፖሊስ ሆነው ስለመመረቃቸውና ስለመሸለማቸው | ረ. አንቀጽ 6 |
| 7. በተለያዩ መድረኮች ስዕሎቻቸውን ስለማቅረባቸው | ሰ. አንቀጽ 7 |
| 8. ትምህርት ቤት ስለመግባት | ሸ. አንቀጽ 8 |
| 9. የአፍሪካ አርት ጋለሪ ስለማቋቋማቸው | ቀ. አንቀጽ 9 |

# ክፍል አራት: መጻፍ

በመጻፍ ትምህርት ክፍል ማስታወሻ አያያዝን የተመለከተ ማስታወሻና ተግባራት ቀርበውላችኋል። ማስታወሻውን ከጻፋችሁት በኋላ ተግባራቱን ስሩ።

‹‹በቃል ያለ ይረሳል በጽሁፍ ያለ ይወረሳል።›› ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? አባባሉ ምን ማለት ይመስላችኋል?

## የማስታወሻ አያያዝ መመሪያ

ማስታወሻ ስለምንፈልገው ርዕሰ ጉዳይ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች በመፈለግ በጽሁፍ መዝግበን የምንይዝበት መንገድ ነው።

1. ማስታወሻ የየምንይዝባቸው አጋጣሚዎች፡-
   - በምናዳምጥበት ጊዜ
   - ጉብኝት በምናደርግበት ጊዜ
   - በግል በምናነብበት ጊዜ ወዘተ.
2. ማስታወሻ ከመውሰዳችን በፊት ትኩረት የምንሰጣቸው ነጥቦች
   - ማስታወሻ ወረቀትና ብዕር ወይም እርሳስ ሊኖር ይገባል።
   - ማስታወሻ የምንይዝበት ዓላማ ማወቅ
3. ማስታወሻ በምንይዝበት ጊዜ
   - ዋና ዋና ሃሳቦቹን በመለየት መጻፍ፤
   - በቃላት፣ በሀረግ፣ በዓረፍተ ነገር፣ በስዕል፣ በግራፍ፣ በሰንጠረዥ ሃሳብን ማስፈር

4. ማስታወሻውን ከያዝን በኃላ

- የሃሳብ አወራረዱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ
- የተጻፈውን ረቂቅ ሳይረሳ መከለስ /ማስተካከል/
- መረጃ ያገኘንበትን ምንጭ በተገቢው መንገድ መጻፍ
- ማስታወሻውን ለተገቢው ዓላማ ማዋል። ወዘተ … ተጠቃሽ ናቸው።

### ተግባር ሁለት

በተማራችሁት የማስታወሻ አያያዝ ስልት መሰረት በአካባቢያችሁ በሥራ ፈጠራ ስኬታማ የሆኑ ሰዎችን በማነጋገርና ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻሁ አቅርቡ።

### ተግባር ሦስት

ወደ ቤተመጽሐፍ ሄዳችሁ አንድ አጭር ልቦለድ አንብቡና የማስታወሻ አያያዝ ስልትን በመጠቀም ማስታወሻ ያዙ። በመቀጠልም የያዛችሁትን ማስታወሻ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

# ክፍል አምስት: ቃላት

በዚህ ትምህርት ክፍል ሞያዊ ቃላት መጠቀምን እና የቃላት ፍቺን ከአውድ መረዳት የሚያስችሉ መልመጃዎች ቀርበዋል። ትዕዛዛቱን በመከተል ስሯቸው።

## መልመጃ ሦስት

ሀ. በተለያዩ ሶስት ሙያዎች የምንጠቀምባቸውን ዘጠኝ ሙያዊ ቃላት ምረጡና ፍቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻሁ በቃል አስረዱ።

ለ. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍቺ

ስጡ።

1. አዳዲስ ስራዎችን እየፈጠረ ህይወቱን በተሻለ ጎዳና የሚመራው የሰው ልጅ ነው።
2. አክስቴ ሁለተኛ ልጇን በሰላም ተገላገለች።
3. በምትወደው የስራ መስክ በመሰማራቷ እጅግ ደስተኛ ናት።
4. ውጤታማ ለመሆን እንቁም፣ እናስብ፣ እንተልም፣ እንተግብር።
5. የፊትን ገፅ በፍየል ቆዳ ላይ በቀለም በመስራት ብዙዎችን አስደምመዋል።

## መልመጃ አራት

የሚከተሉት ቃላት ስራ ወዳዱ የጥበብ ባለሙያ ከሚለው ምንባብ የወጡ ናቸው።ቃላቱን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮች መስርቱና ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

ሀ. ቀስ በቀስ
ለ. ደማቅ ዱካ
ሐ. አገልግለዋል
መ. ይሁንታ
ሠ. ብርቱ
ረ. ፈለግ
ሠ. የአኗኗር ዘይቤ
ሰ. ታዋቂ
ሸ. ባቋቋሙት
ቀ. አበርክቶላቸዋል

# ክፍል ስድስት: ሰዋስው

በሰዋስው ትምህርት ክፍል ገቢር እና የተገብሮ ግሶችን የተመለከተ ማስታወሻና መልመጃ ቀርቧል። ትዕዛዛቱን ተከትላችሁ መልመጃውን ስሩት።

## መልመጃ አምስት

1. ገቢርና ተገቢሮ ግስ ሲባል ምን ይመስላችኋል? በቡድን ተወያዩና ምላሻችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## የግስ ጠባይ

የግሶችን ጠባይ በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል።

- ✓ ገቢር (አድራጊ) ግሶች
- ✓ ተገብሮ (ተደራጊ) ግሶች

ሀ. ገቢር (አድራጊ) ግሶች

እነዚህ ግሶች ተግባር መፈፀምን ወይም አንድ ነገር ማድረግ አለማድረግን የሚያመለክቱ ግሶች ሲሆኑ ተሻጋሪም ኢተሻጋሪም ሊሆኑ ይችላሉ።

ተሻጋሪ ግሶች የሚባሉት ተሳቢ የሚፈልጉ ግሶች ሲሆኑ እንደ ገዛ፣ ተቀበለ፣ ወሰደ፣ በላ፣ ላከ... ወዘተ ያሉ ግሶች የዚህ ምሳሌ ናቸው።

ምሳሌ፡ ልጁ ስልክ ገዛ።

ኢተሻጋሪ ግሶች የሚባሉት ድርጊቱ ወደ ሌላ ሰው ያልተሸጋገረ የሚመለክቱ ሲሆን እንደ ቆመ፣ ተኛ፣ ናቀ፣ ወረደ፣ ወጣ ወዘተ ያሉ ግሶች በዚህ ስር የሚካተቱ ናቸው።

ምሳሌ፡ ሰውዬው ከመኪና ላይ ወረደ።

ለ. ተገብሮ (ተደራጊ) ግሶች

እነዚህ ግሶች ደግሞ ድርጊት ተቀባይነትን ወይም ተደረገ

አልተደረገም የሚለውን የሚያመለክቱ ሲሆኑ ‹‹ተ›› የተሰኘውን የተደራጊነት መነሻ ቅጥያ የሚቀበሉ ናቸው። ለአብነት ያህል ተጻፈ፣ ተነበበ፣ ተገዛ፣ ተለወጠ ወዘተ ያሉት ምሳሌ የሚሆኑ ግሶች ናቸው።

ምሳሌ፡- ለማስተማሪያ የሚሆን አዲስ መጽሐፍ ተዘጋጀ።

2. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ግሶችን ገቢር/ አድራጊ/ ወይም ተገብሮ /ተደራጊ/ በማለት ለዩ።

ሀ. እውቁ የማስታወቂያ ባለሙያ የኢትዮጵያን ዘመን አቆጣጠር በጥሩ ሁኔታ <u>አስተዋወቀ</u>።

ለ. ዘሪቱ ክፍለ ሀገር ያሉ ዘመዶቿን ትናንት <u>ተዋወቀች</u>።

ሐ. የሞኝነት ዘመናችን ተቋጭቶ በህዳሴው ብርሃን <u>ደምቀናል</u>።

መ. አዛውንቱ በልጆች መጥፎ ተግባር <u>ተቆጡ</u>።

ሠ. ሀገሬ ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ <u>ኮራች</u>።

3. የሚከተሉትን ገቢር ግሶች ወደ ተገብሮ ተገብሮዎችን ደግሞ ወደ ገቢር ግስ ለውጣችሁ ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

ሀ. ሰራ

ለ. መረቀ

ሐ. አጠናቀቀ

መ. አደሰች

ሠ. ቀማ

ረ. ሸለመች

4. ገቢርና ተገብሮን የሚሳዩ ከስድስት ያላነሱ ግሶችን መርጣችሁ ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

5. የሚከተለውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ከታች የቀረቡትን ቃላት ወደ ሂደታዊ ድርጊት በመቀየር ዓረፍተ ነገር ጻፉባቸው።

ምሳሌ፡ ሮጠች

- ሰርካዓለም ወደ ትምህርት ቤት እየሮጠች ነው።

ሀ. በላ

ሐ. ወለወለ

ሠ. አደገች

ለ. ቀመመ

መ. ተደሰተች

ረ. አመሰገነ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስለስራ ፈጠራ የአንድ ሰው ታሪክ በማንሳት ተምራችኋል። ማዳመጥና መናገር በሚለው ክፍል ‹‹የስራ ፈጠራ ሀሳብ መገኛ ምንጮች›› የሚል ምንባብ አዳምጣችሁ የምትስማሙበትንና የማትስማሙበት ሃሳብ እያነሳችሁ ተወያይታችኋል። በተጨማሪም ስራ ፈጠራን በተመለከተ ውይይት አድርጋችኋል። በመቀጠልም የቀረበላችሁን ታሪክና ምሳሌ መሰረት በማድረግ አቋማችሁን በማስረጃ አስደግፋችሁ ተናግራችኋል። “ስራ ፈጣሪው የጥበብ ባለሙያ” በሚል ርዕስ የማንበብ ክሂላችሁን ተጠቅማችሁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሰርታችኋል። ይህንንም ለማጠናከር የአሰሳ ንባብ እና ጥልቅ ንባብ በመከተል የተለያዩ ጽሁፎችን አንብባቸው ሃሳብ ወስዳችኋል። የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የማስታወሻ አያያዝ በሚል የቀረበውን ሃሳብ መሰረት አድርጋችሁ ማስታወሻ በመያዝ የያዛችሁትን ለጓደኞቻችሁ አቅርባችኋል።

በተጨማሪም የተለያዩ ቃላትን አውዳዊ ፍችና ሙያዊ ቃላትን በማንሳት በቃላት ክፍል ተምራችኋል። ለቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን የሚያሳይ ዓረፍተ ነገርም መስርታችኋል።

በሰዋስው ክፍልም ገቢርና ተገብሮ ግሶችን ተመልክታችኋል፡ ገቢር ግሶች ተግባር መፈፀምን ወይም አደረገንና አላደረገም የሚያመለክቱ ሲሆኑ ተገብሮ የሚባሉት ግሶች ደግሞ ድርጊት ተቀባይነትን ወይም ተደረገ አልተደረገም የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህን ግሶች ተጠቅማችሁ ዓረፍተ ነገር መመስረት ተለማምዳችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በስራ ፈጠራ ዓለም የምታደንቋቸውን ሰዎች በማንሳት ያደነቃችሁባቸውን ምክንያት ተናገሩ።
2. ከኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ አንድ ታሪክ በጥልቅ የንባብ ስልት በማንበብና ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓኞቻችሁ አስረዱ።
3. ገቢርና ተገብሮ ቃላት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ዓረፍ ነገር በመመስረት ልዩነታቸውን አስረዱ።
4. በሚከተሉት ቃላት ገቢርና ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱባቸው።

| | |
|---|---|
| ሀ. ሰራ | መ. ተከናወነ |
| ለ. ተጓዘ | ሠ. ወጣ |
| ሐ. መራች | ረ. አስመጣ |

5. የተለያዩ ግጥሞችን በማንበብ የሙያ ቃላት፣ እንግዳ /ያልተለመዱ/ ቃላትን ወዘተ... ፈልጋችሁ ፍቻውን የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

በ ‹‹ሀ›› ረድፍ ለሚገኙት ቃላት በ‹‹ለ›› ረድፍ ከሚገኙት ቃላት በፍቺ የሚመስሏቸውን በማዛመድ ዓረፍተ ነገር ጻፉባቸው።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ነዋይ | ሀ. ገንዘብ |
| 2. ድንገት | ለ. መንታ |
| 3. ሽሙጥ | ሐ. ማፌዝ |
| 4. ጥንድ | መ. መከለል |
| 5. ግርዶሽ | ሠ. ሳይታሰብ |
| | ረ. ፍቃደኛነት |

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(□)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | |
|---|---|---|
| 1. | አዳምጣጩ በማስረጃ መስማማቱንና አለመስማማቱን መግለጽ እችላሁ። | |
| 2. | ሀሳባችሁን በምክንያት በማስደገፍ ግላዊ እይታ በቃል እገልጻለሁ። | |
| 3. | ፅሁፍን በማንበብ ለማን እንደተጻፈ መለይት እችላለሁ። | |
| 4. | አንድን ጽሁፍ ለተለያየ ዓላማ በለሆሳስና በጥልቅ የማንበብ ስልትን መጠቀም እችላለሁ | |
| 5. | የተለያዩ አይነት የማስታወሻ አያያዝ ስልቶችን መጠቀም ማስታወሻ ፤ ዋና ሀሳብን እና የተብራራ ሀሳብን መያዝ እችላለሁ። | |
| 6. | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያዳመጥኩትን ንግግር ጠቃሚውን ለይቼ ማስታወሻ መያዝ እችላለሁ። | |
| 7. | ከፅሁፍ አውድ ውስጥ የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም እሰጣለሁ። | |
| 8. | በዓርፍተነገር ውስጥ ተሻጋሪ እና ኢተሻጋሪ ግሶችን ትጠቀማላችሁ። | |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ዋቢ ጽሑፎች

ሀዲስ አለማየሁ።(1996)። ፍቅር እስከ መቃብር። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚዎች ድርጅት።

መንግስቱ ለማ። (1955)። የግጥም ጉባኤ ። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

መንግስቱ ታደሰ። (2012)። ሜጋ የአማርኛ ሰውስው አጋዥ መጽሐፍ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር።

ማንኩሳ አታሚና አሳታሚ። (2009)። የጳውሎስ ኞኞ ስብስብ ስራዎች። አዲስ አበባ፣ መላ ማተሚያ ድርጅት።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ። (2007)። ቁጥር 5 ቅጽ 11

በዓለ ግርማ። (2010)። ከአድማስ በአሻገር። አዲስ አበባ፤ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት።

በዳግማይ ነቅዓጥበብ። (2007)። አዲስ ፲፰፻፹፱:: አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ።

በድሉ ዋቅጅራ። (2007)። ቋንቋን በሥነጽሁፍ ማስተማር። አዲስ አበባ፣

ባዬ ይማም። (2002) ። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

ብርሃኑ ለማ።(ዓ.ም ያልተጠቀሰ)። የታዋቂ የኢትዮጵያ ሴቶች የፖለቲካና የፍቅር ታሪክ። አዲስ አበባ፣ ፋርኢ ስትትሬዲን ኃ/የ/የግልማህበር።

ብርሃኑ ገ/ጻዲቅ። (2012)። አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምሪያ። አዲሰ አበባ፣ በረከት ማተሚያ ኃላ/የተ/የግ/ማ።

ብርሃኑ ገበየሁ።(2003)። የአማርኛ ሥነግጥም። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

ነብይ መኮንን ። (2006)። ስውር ስፌት ። አዲስ አበባ፣ ስውር ስፌት ሕትመት። አከፋፋይ ኃ/የተ/የግ/ማህበር።

አያልነህ ሙላቱ። (1984)። ማን ይሆን የበላ። አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

አፈወርቅ ገብረየሱስ። (1958)። ጦቢያ። አስመራ፣

ከበደ ሚካኤል። (1994)። የቅኔ ውበት ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ከበደ ሚካኤል። (1999)። ታሪክና ምሳሌ 1ኛ መጽሐፍ። አዲሰ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ

________________ ::(1999)። ታሪክና ምሳሌ 2ኛ መጽሐፍ። አዲሰ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ

ወረታው በዛብህ (ዶ/ር)። (2008)። ለራስ ማን እንደራስ የስኬታማነት የግል መርህ መውጫ ቁጥር አንድ። አዲሰ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች ኃ.የተ. የግ.ማህበር።

ዘሪሁን አስፋው። (2002)። የስነጽሁፍ መሰረታውያን። አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ። (2012) ። ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር 20፣ አዲስ አበባ፣ መጋቢት 16/2012ዓ.ም። አዋጅ ቁጥር 1176/2012ዓ.ም።

ደረጀ ገብሬ። (1996)። ተግባራዊ የጽህፈት ማስተማሪያ። አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት።

ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ። (2012)። አማርኛ ከ9 እና10 ክፍል። አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

ደበበ ሰይፉ። (1980)። የብርሃን ፍቅር። አዲስ አበባ፣ ኩራዝ ዘሳታሚ ድርጅት።

ዳኛቸው ወርቁ። (1962) ። አደፍርስ። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ጌታሁን አማረ። (1989) ። ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀለላል አቀራረብ። አዲሰ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች።

ጌታቸው በለጠ። (2004)።የጥበባት ጉባኤ።አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

ጳውሎስ ኞኞ። (1955)። በአንድነት ለአንድ ዓላማ እንሰለፍ ። አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ድምፅ። ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የግ. ማህበር።

ፍጹም ወ/ማርያም። (2005)። ያልተዘመረላቸው፣ ቅፅ2:: አዲስአበባ፣ ፋርኢ. ስትትሬዲን ኃ/የ/የግልማህበር።

## ሙዳየ ቃላት

| ቃል | ፍቺ |
|---|---|
| ሀመልማል አረንጓዴነት | ልምላሜ፣ |
| ሁዳድ ቦታ | ሠፊ፣ የእርሻ |
| ህላዌ | በህይወት መኖር |
| ህቡዕ | ስውር፣ ድብቅ |
| ለዛ | ውበት፣ ወዝ |
| ልጨኛ | ቁም ነገረኛ |
| መረን | ልቅ፣ ስድ፣ ባለጌ |
| መርህ | መመሪያ |
| መቋደሻ ብልት | ቁርስ፣ የዶሮ |
| መግነጢስ | የስበት ኃይል |
| ምንዝር ሰራተኛ | አለቃ ያልሆነ፣ የበታች |
| ሸፈጠ | ከዳ፣ ካደ፣ ዋሸ |
| ቁርሾ | ቂም |
| ባይተዋር | እንግዳ |
| ባድማ ቦታ | ጠፍ፣ ወና፣ ባዶ |
| ነቁጥ ምልክት | ነጥብ (አንድ ነጥብ)፣ |

| | |
|---|---|
| ነቂስ | ሁሉ /በሙሉ/ |
| ነውጥ | ሁከት፣ ብጥብጥ፣ ሽብር |
| ነጸብራቅ | ብልጭልጭታ፣ አንድን |
| ሁኔታ | |
| አሜኬላ | እሾህ |
| አምበልጋ | ፈሪ፣ ቡከን |
| ወርች | ጡንቻ፣ የፊት እግር እጅ |
| ዚቀኛ | ተረበኛ፣ ተረብ አዋቂ |
| ዝሃ | ድር |
| ጓጓ | ተመኘ |
| ጥሪት | ሀብት |
| ጦስ | ሰበብ፣ ምክንያት |

## ናሙና ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው

| | |
|---|---|
| ሁሉ አማረሽ የምትከጅል | ያየችውን ሁሉ |
| ሂያጅ | አመንዝራ |
| ሐረግ መዘዘ | ዘር ቆጠረ |
| ልበ ሙት | ሰነፍ |
| ልጓም አጥባቂ | ፈሪ፣ ቡከን፣ አምበል |
| መሬት ላሰ | ተለማመጠ |
| ሰኔና ሰኞ | ድንገተኛ አጋጣሚ |
| ሰው ሆነ | ራሱን ቻለ |
| ስመ ጥሩ | ዝነኛ |
| ቅቤ አንጓች አስመሳይ | እወደድ ባይ፣ |
| ቆርጠ ቀጥል | ቀጣፊ |
| በደረቁ ላጨ | አታለለ |
| ባዝራ | ሴት ፈረስ |
| ብው አለ | ተናደደ |
| አመድ አፋሽ | ሰጥቶ የማይመሰገን |
| አሚን ሚስት | የህግ ሚስት |
| አራስ ነብር | ኃይለኛ ሰው፣ ቁጡ |
| አርቆ አሳቢ | አስተዋይ |
| አናዘዘው | በግድ አናገረው |
| አንገተ ሰባራ | ዓይናፋር |
| አድሮ ቃሪያ | የማይሻሻል |

| | |
|---|---|
| አጉራ ዘለል | ባለጌ |
| አጉራ ጠናኝ | ጭብጥህ ጠነከረብኝ |
| አግድም አደግ | ያልተቀጣ፣ ባለጌ |
| እንባ ጠባቂ | ተቆርቋሪ |
| እንቶፈንቶ | ሞኝ ሰው |
| እግረ ነጭ | ገደቢስ |
| ወረተኛ ወዳጅ | ጊዜ አይቶ የሚከዳ፣የጊዜ |
| የቀለም ቀንድ | ሊቅ፣ አዋቂ፣ |
| የአህያ ምላስ | ተንኮለኛ፣ ሞገደኛ |
| የአዞ እንባ | የውሸት ሀዘን |
| የዛር በቅሎ | ቀዥቃዣ |
| የግንባር ስጋ | ግልፅ |
| የጥርስ ስጋ | ነዝናዛ፣ ጨቅጫቃ |
| ጅራቱን ይቆላል | ይለማመጣል |
| ግድ የለሽ | ቸልተኛ |
| ጥቁር እንግዳ | መጥቶ የማያውቅ ወዳጅ |